አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3523 | ቅዳሜ ግንቦት 30 ቀን 2017 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# “ለሀገራችን ሰላም በዱዓና በተግባር ዘብ ልንሆን ይገባል”

**የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሸይኽ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ለሀገራችን ሰላም በዱዓና በተግባር ዘብ ልንሆን ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሸይኽ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ ተናገሩ፡፡

ሸይኽ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ ይህንን ያሉት 1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓልን ምክንያት በማድረግ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት ሲሆን ሰላም የጋራችን በመሆኑ በጋራ ለሰላም ዘብ ሆነን እንስራ ወደ ጦርነት የሚጋብዙን አካላትን እየመከርን ሀገራችን ወደተሟላ ሰላም እንድትመለስ በተለይም የኃይማኖት አባቶች አበክረን እንስራ ብለዋል፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ለሀገር ሰላምና ለሕዝቦች አንድነት ዱዓ እንዲያደርግም ፕሬዝዳንቱ ጥሪ አቅርበዋል።

ሸይኽ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ የአረፋ በዓል የአንድነት፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ በዓል በመሆኑ የተቸገሩ ወገኖቻችንን መርዳት የታረዙትን ማልበስና የታመሙትን መጠየቅ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ኢድ አል አድሃ (አረፋ) በታላቁ ዙል ሒጃ ወር በዘጠነኛው ቀን ከመላው ዓለም የሐጅ ፀሎታቸውን

ወደ ገጽ 3 ዞሯል


ፎቶ- ከገፀ ድር
የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሸይኽ ሀጅ ኢብራሂም ቱፋ

## የባህር በር አጠቃቀምና ዓለም አቀፍ አሰራር

4


ፎቶ- ከገፀ ድር
በርካታ ሀገራት የባህር በራቸውን በጋራ በመጠቀም ማደግ ችለዋል

## ዲጂታሉ የመረጃ መስኮት

21


ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በቅርብ የተሰሩ ዘመናዊ የመረጃ ማስራጫ ስክሪኖች

## የመታዘዝ ከፍታ - በመንዙማና ነሺዳ

16


ፎቶ- ከገፀ ድር
በነሺዳ ስራ የሚታወቀው አሚር መሀመድ

# “ሪፎርሙ በእኛ ልክ የተሰፋ ነው”

**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

- **ኢትዮጵያ ዘንድሮ ከወጪ ንግድ ከ8 ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ ታገኛለች**


ፎቶ- ከገፀ ድር
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በስንታየሁ ምትኩ**

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሰባት ዓመታት የመንግስት እንቅስቃሴን፣ የኢኮኖሚ እድገትን፣ ወቅታዊ ፈተናዎችንና ቀጣይ አቅጣጫዎችን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ጋር ሰፋ ያለ ቆይታ አድርገዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያነሷቸውን ዋና ዋና ነጥቦችም አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል፡፡

በቅድሚያ የቀረበላቸው ጥያቄ ከኢትዮጵያዊነት ብያኔ ጋር ይያያዛል። “የኢትዮጵያዊነት ምንነት ላይ መግባባት ሳንፈጥር ቀጥሎ በሚመጡት ሀሳቦች ላይ መነጋገር ያስቸግራል” በማለት ቃለ ምልልሳቸውን የጀመሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ “ለእኔ ኢትዮጵያዊነት የጋራ እጣ ፈንታ ነው፡፡ እንደ ህዝብ ማናቸውንም ትልም ማሳካት የሚቻለው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል




# የዘመናት ቋጠሮ መፍቻው - ምክክር

**በስንታየሁ ምትኩ**

“ነብዩ ኢብራሂም ልጃቸውን እስማኤልን ያገኙት በስተርጅና ዘመናቸው ነበር፡፡ ከመሸ ያገኙትን አንድዬ ልጃቸውን እንዲሰው ህልም ይታያቸዋል። ለልጃቸውም ‘በህልሜ የማርድህ ሆኜ አይቻለሁ’ አሉት። ልጃቸው እስማኤልም፣ ‘አባቴ ሆይ የታዘዝከውን ፈፅም!’ በማለት ትዕዛዙን ለመቀበል ፈቃደኝነቱን አሳየ” ሲሉ የእስልምና ሃይማኖት አባት የሆኑት ሼህ አብዱልመናን ሁሴን ያስረዳሉ፡፡

ነብዩ ኢብራሂም ነብይ ቢሆኑም ሰውም ናቸው። ልጅን ያህል ነገር ለመስዋዕትነት ማዘጋጀት ከባድ ፈተና ቢሆንም፤ ከፈጣሪ ትእዛዝ አይበልጥም ብለው ለመፈፀም ሲዘጋጁ ከሰማይ በግ መጥቶላቸው በልጃቸው ምትክ በጉን አረዱ፡፡ በኢድ አል አድሃም እርድ ይፈፀማል፡፡ ይህም ነብዩ ኢብራሂምን መነሻ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## ሀገር በምትሻን ቦታ ሁሉ በታዛዥነት እናገልግላት!

ኢትዮጵያ የብዙ ሃብቶች ባለቤት ነች፡፡ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ መስህቦቿ ውበትን የሚቸሩ፣ ከድህነት ማላቀቅ የሀገርን ገጽታም በበጎ ማስተዋወቅ የሚችሉ ናቸው፡፡ ሀይማኖታዊ እና ህዝባዊ በዓላት ደግሞ የብዝሃነት ጌጥ፣ የአንድነታችን እርሾዎች ናቸው፡፡ በውስጣቸው የያዟቸው እሴቶች መረዳዳትን፣ ታዛዥነትን፣ መከባበርን የሚያንጸባርቁ፤ የሀገር ሰላም እና የህዝብ ደህንነት የሚሰበከባቸው ናቸው፡፡ እነዚህን እና መሰል ሃብቶች በልኩ ተረድቶ፣ ለሀገር እና ህዝብ በሚበጅ መልኩ አሟጦ መጠቀም ላይ ሳንካዎች መኖራቸው እሙን ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የሚያጋጥሙን ፈተናዎች ደግሞ የተግባር አስረጂዎች ናቸው፡፡

በትናንትናው ዕለት 1446ኛው የዒድ አል አድሃ(አረፋ) በዓል በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ተከብሮ ውሏል፡፡ የእምነቱ አስተምህሮ እንደሚያስረዳው፣ ነብዩ ኢብራሂም የፈጣሪ ትዕዛዝን በመቀበል በማምሻ እድሜ ያገኙትን ልጃቸውን ለመሰዋት ተዘጋጁ፡፡ ትዕዛዙን ለመፈጸም የታየውን የቀናኢነት እና ቁርጠኝነት ጥግ በልኩ መረዳት፣ ጊዜው በሚጠይቀውና ለሀገር በሚበጅ መልኩ ትምህርት መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከማይደራደሩባቸውና የህይወት መስዋዕትነት ያለስስት ከሚከፍሉባቸው ጉዳዮች መካከል ሀገር ቀዳሚዋ ናት፡፡ ለዛም ነው ሉዓላዊነትን የሚዳፈሩ የውጭ ወረራዎች ሲከሰቱ ሀገር ባወጀቻቸው የክተት ጥሪዎች ላይ ‘ጨርቄን፣ ማቄን’ ሳይሉ ከአራቱም ማዕዘናት በመትመም በጋራ የተዋደቁት፣ ጠላትንም አሳፍረው መመለስ የቻሉት፡፡ እኛም ሀገርን የማጽናት የአባቶቻችንና እናቶቻችን አደራ አለብን፡፡ በተለያዩ ጊዜያት እየተፈጠሩ የመጡ ሽንቁሮች እየሰፉ መጥተው ዘላቂ መፍትሔ መስጠትን ግድ የሚልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ ሀገራዊ ምክክር ለማካሄድም የምክክር ኮሚሽን ከማቋቋም ጀምሮ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፤ በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ ስኬቱ ምክክሩ በሚያስገኘው ውጤት የሚለካ እንደመሆኑ መጠን ኢትዮጵያውያን አይተኬ ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከሌላው ዓለም ሀገራት ጋር እኩል ለመራመድ ትላልቅ ርዕዮችን መሰነቅ፣ ለተፈጻሚነታቸውም መትጋት ያስፈልጋል። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከሀገር አልፎ ጎረቤቶቻችንን የሚጠቅም፣ ኢትዮጵያን ደግሞ ከድህነት ማቅ ለማስወጣት ቁልፍ ሚና የሚጫወት ፕሮጀክት ነው፡፡ ግድቡ በወርሃ መስከረም ተጠናቅቆ እንደሚመረቅ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መናገራቸው ይታወሳል፡፡ ይህ የሆነው መንገዱ አልጋ በአልጋ፣ ጫናውም የቀለለ ሆኖ አይደለም። ይህም ሀገር የምትሻውን በገንዘብ፣ በእውቀትና በሀሳብ የበኩላችንን ዐሻራ ማሳረፍ መቻላችን ያመጣው ውጤት ነው። ‘የባህር በር ጥያቄያችን በሰላማዊ እና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ መልስ ያግኝ’ የሚለውም ሀገር እያነሳችው ያለ በሀገራት መካከል ሊፈጠር የሚገባው የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጉዳይ ነው፡፡ አረንጓዴ ዐሻራ የዓለም ፈተና የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል የሚያስችልና ባህል ልናደርገው የሚገባ ተግባር ነው፡፡

ሀገር የምትሻው ሌላኛው ጉዳይ የአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚስተዋለው ስብራት እንዲጠገን ነው፡፡ ችግሩ ለመኖሩ እውቅና መስጠቱ፣ በፌደራል ደረጃ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መጀመሩ እና ቴክኖሎጂ የሚሰጠውን እድል ለመጠቀም የሚደረገው ጥረት ጥሩ ነው፡፡ ሆኖም በቅንነትና በታዛዥነት በማገልገል የህዝብን ቅሬታ መፍታት፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት ምንጭነቱን ማድረቅ ከአገልጋዩም ከተገልጋዩም የሚጠበቅ የዜግነት ኃላፊነት ነው፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሀገርን በኢኮኖሚ የምናግዝበት፣ ለተቸገሩ ወገኖቻችን አጋርነታችንን የምናሳይበት፣ በየእምነታችን በረከት የምናገኝበት፣ ህሊናችንም እርካታ የሚጎናጸፍበት ነው፡፡ በጥቅሉ በድሀ ሀገር እንደሚኖር ህዝብ የሚጎድሉን ብዙ ናቸው፡፡ ይህን መሙላት የሚቻለው ደግሞ በጋራ መቆም፣ ሳንታክት መስራት ስንችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሀገር መሻት ነው የሚለውን ተረድቶ በታዛዥነት ማገልገልን ይጠይቃል፡፡

# የእኔ እይታ

## ለወንዞቻችን ጤንነት ዘላቂ መፍትሔ ላይ እናተኩር

**በሐብታሙ ደበሌ**

ከተማነት፤ በውበት፣ በፅዳት፣ በምቹነት እና መሰል የአኗኗርን ሁኔታ በሚያሻሽሉ መስፈርቶች በተግባር ይገለጣል፡፡ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ የሚኖርባቸው እና የሚንቀሳቀስባቸው በመሆናቸው፤ የከተማነትን መመዘኛዎች እንዲያሟሉ ያልተቋረጠ ሥራዎችን መሥራት ግድ ይላል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም አሁን ላይ እየታየ ያለው የልማት ሥራ እና በየዘመናቱ ሲከናወኑ የነበሩ ተግባራት ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

በዚህ አጭር ጽሑፍ ልመለከት የወደድኩት የከተማነትን መመዘኛዎች ከሚወስኑ በርካታ ጉዳዮች መካከል ከጽዳት ጋር በተለይም፤ ወንዞቻችን ላይ አተኩራለሁ፡፡ የእነ ቀበና፣ ግንፍሌ አቃቂ እና ሌሎችም ... ወንዞች መገማሸሪያ የሆነችው አዲስ አበባ የገፀ ምድር ውሃ ሀብትን ተፈጥሮ በደግነት ቸራታለች፡፡ የተሰጠንን ተፈጥሯዊ ሀብት በአግባቡ ጠብቆ እና ተንከባክቦ ማቆየት ደግሞ ብልህነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፤ አዲስ አበባ ወንዞቿ ቆሽሸው፣ ለዓይንም ለአፍንጫም ከብደው፣ ብክለታቸው ለጤና ጎጂ እስከሚሆኑበት ደርሶ እንደነበር የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡

በሰው ሠራሽ ምክንያቶች ለአደጋ የተጋለጡትን ወንዞች ለማከም እና ተፈጥሯዊ ገጽታቸው ላይ ለመመለስ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች የሚበረታቱ ናቸው። በመሬት ላይ የሚሠሩት የወንዝ ዳርቻ ልማቶች እና ተያያዥ ተግባራት የወንዞቹን መፃኢ ሁኔታ የሚያሻሽሉ ናቸው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ወንዞችን ሊበክሉ የሚችሉ ፍሳሾችን እና ደረቅ ቆሻሻዎችን ወደ ወንዞቹ የሚጨምሩ ግለሰቦች፣ ተቋማት እና ድርጅቶች አስተማሪ የሆነ ቅጣት የሚቀጡበትን አሠራር ያሰፈነ ሕግ ወጥቶ መተግበሩ ተገቢ ነው፡፡

በእኔ እይታ እነዚህ ጅምር ሥራዎች ለከተማዋ ነዋሪ የእስትንፋስን ያክል ወሳኝ የሆኑ ወንዞች ወደ ተፈጥሯዊ ገፅታቸው እንዲመለሱ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው አምናለሁ። ከግለሰብ ቤት እስከ ትላልቅ ተቋማት የሚወጡ የተበከሉ እና መርዛማ ፍሳሾችን የመቀበል ኃላፊነት ተጥሎባቸው የቆዩት ወንዞች እረፍት ያገኛሉ፡፡ ከሕመማቸው እንዲያገግሙ ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡ እንደ እሬንጅ የጠቆረ መልካቸው እንዲፈካ፣ ከሩቅ የሚጋፋው ጠረናቸው እንዲተን፣ በውስጣቸው እና በዙሪያቸው የሚታየው የፕላስቲክ እና መሰል የደረቅ ቆሻሻ ክምር እንዲወገድ ጥሩ አጋጣሚን ያስገኛል፡፡

በተለያየ ጊዜ የወንዞችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣውን ሕግ የሚጥስ ተግባር በፈፀሙ ግለሰቦች፣ ተቋማት እና ድርጅቶች ላይ የገንዘብ ቅጣት እርምጃ እንደተወሰደባቸው የሚገልፁ መረጃዎችን እየሰማን ነው። በመሆኑም ለወንዞቻችን ጽዳት፣ ውበት፣ ጤናማነት እና ተያያዥ ጉዳዮች ውጤታማነት መምጣት እንደ ከተማ አስተዳደር የተጀመረውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ ማስኬድ፣ ቅጣቱን እና የማስተማር ሥራውን ዘላቂ እና ውጤታማነትን ባማከለ መልኩ አቀናጅቶ መፈፀም ተገቢ ነው እላለሁ።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
አብርሃም ገብሬ
ሄለን ጥላሁን
ሰገነት አስማማው
ፋንታነሽ ተፈራ
ለይላ መሀመድ
ይግለጡ ጓዴ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለሰ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# “ለእኛ የመገናኛ መንገዳችን ሀገራዊ ምክክር ነው”

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በመለሰ ተሰጋ**

ለእኛ የመገናኛ መንገዳችን ሀገራዊ ምክክር ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ያሉት የአረፋ(ዒድ አል አድሃ) በዓል አስመልክቶ ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸው ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው አረፋ “ወአረፍተኒ ወአረፍቱ” “አወቅሺኝ፤ ዐወቅኩህ” የተባለበት በዓል ነው፡፡ አደምና ሐዋ ከጀነት ከወጡ በኋላ ለረዥም ዘመን ተለያይተው ኖረዋል። የተገናኙት በአረፋ ዕለት ነው፡፡ አረፋ የተለያዩ የሚገናኙበት በዓል ነው፡፡ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ አሳዛኙ ነገር መለያየቱ ሳይሆን፣ ተለያይቶ መቅረት ነው፡፡ ሐሳብ፣ አመለካከት፣ ቅሬታ እና ያለፈ ታሪክ በአንድም በሌላም መንገድ አለያይተውን ይሆናል፡፡ ነገር ግን የአንድ ሀገር ልጆች እንደመሆናችን መጠን ተለያይቶ መቅረት ሳይሆን እንደ አደምና ሐዋ የመገናኛ መንገድ ያስፈልገናል ብለዋል፡፡

ለእኛ የመገናኛ መንገዳችን ሀገራዊ ምክክር ነው፡፡ ሀገራዊ ምክክር ሐሳቦቻችን እና ፍላጎቶቻችን የሚገናኙበት መድረክ ነው፡፡ አንዱ ሌላውን የሚረዳበት፣ አንዱ ሌላውን የሚያስረዳበት፣ አንዱ በሌላው ጫማ የሚቆምበት፣ አንዱ የሌላውን ሕመም የሚታመምበት፤ በመገናኘት “ዐወቅሺኝ፣ ዐወቅኩህ” የምንባባልበት ሰላማዊ መድረክ ነው፡፡

በመሆኑም የአረፋን በዓል ስናከብር ለሀገርና ለነገ ትውልድ የምንከፍለውን መሥዋዕትነት እያሰብን፤ በሀገራዊ ምክክሩም የምንገናኝበትን መድረክ ይበልጥ እያጠናከርን እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

በአረፋ በዓል ወቅት የሚታወሱ ሁለት ዕሴቶች፣ ለምንገነባት የበለጸገች ኢትዮጵያ እጅግ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የአረፋ በዓል መሥዋዕትነት የሚታሰብበት በዓል ነው። ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸው ኢስማኤልን በፈቃዳቸው ለፈጣሪ መሥዋዕት ለማድረግ ፍጹም ቆራጥነታቸውን ያሳዩበት በዓል ነው - አረፋ፡፡ ልጅን ለፈጣሪ መሥዋዕት ከማድረግ በላይ መታዘዝም፣ መሰጠትም የለም፡፡

ሀገር የምትጸናው በመሥዋዕትነት ነው፡፡ ያውም የምንወደውን ነገር መሥዋዕት በማድረግ፡፡ ሀገር ማለት ቀዳሚው ትውልድ ለተተኪው ትውልድ ሲል መሥዋዕትነት የሚከፍልባት ናት፡፡

ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸውን ለመሥዋዕትነት በማዘጋጀታቸው በምትኩ የሚሠዋ በግ ከአላህ አግኝተዋል፡፡ ሌላ መሥዋዕት ለማግኘት ራስን መሥዋዕትነት ማድረግ ይገባል፡፡ በኢብራሂም ልቡና እስማኤል ተሠዉቷል፡፡ ለሀገሩ የሚሠዋን ትውልድ የሚፈጥረው ለሀገሩ ቀድሞ የተሠዋ ትውልድ ነው ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው እናቶቻችንና አባቶቻችን ለሀገራቸው ነጻነትና ሉዓላዊነት መሥዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡ በዚያ መሥዋዕትነታቸው ሰማያዊና ታሪካዊ ዋጋ ያገኙበታል። ተመጣጣኝ ምድራዊ ምንዳ ግን አያገኙም፡፡ ለሕይወት የሚመጥን ምንም ዓይነት ምንዳ ስለሌለ፡፡ የእነርሱን ምንዳ የምንቀበለው እኛ ነን፡፡ የእኛንም ምንዳ ተተኪው ትውልድ ይመነዳዋል ብለዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

## “ለሀገራችን ... 

ከገጽ 1 የዞረ

ለማድረስ በአረፋ ላይ የሚገናኙበትን ፈጣሪያቸውን አሏህ የሚማፀኑበት ሐጅ ማድረግ እድል ያላገኙ ምዕመናን ደግም በፆም የሚያሳልፉበት ቀን ማግስት የሚከበር ታላቅ በዓል እንደሆነ ፕሬዝዳንቱ ተናግረዋል።

ከበዓሉ በኋላም ቢሆን ኢባዳና ዱዓን ማጠናከር፣ ምስኪኖችን መርዳት፣ የተፈናቀሉትን፣ በማረሚያ ያሉ ዜጎችንና የታመሙ ወገኖቻችንን መዘየር ይገባል፡፡ እስላም ክርስትያን ሳንል ያለምንም ልዩነት ጉርብትናችንን ማጠናከር ይጠበቅብናል። ያለንን ተካፍለን እየተጠቀምን አብሮነታችንን በተግባር ማሳየትና ተሳስረንና ተከባብረን ሀገራችንን መጠበቅ አለብን ሲሉም አሳስበዋል፡፡

በትላንትናው ዕለትም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና የዑለማ ጉባዔ ሰብሳቢ ሼይኽ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋና የጠቅላይ ምክር ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የዒድ አል አድሃ ሰላት ለመስገድ በአዲስ አበባ ስታዲየም ተገኝተዋል። የከተማዋ ሕዝበ መስሊምም በመስገጃ ቦታው ማልዶ ተገኝቶ በዓሉን አክብሯል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ስታዲየም የተከበረው 1446ኛው የኢድ-አል አድሃ (አረፋ) በዓል ከፊል ገፅታ

# የባህር በር አጠቃቀምና ዓለም አቀፍ አሰራር

**በሳህሉ ብርሃኑ**

“የባህር በር ባለቤት ከሆንክ ዓለምን ታገለግላለህ፤ ባህር በርና ወደብ አልባ ከሆንክ ግን ለጎረቤቶችህ እንኳን የምትሰጠው ጥቅም እንዳለ እርግጠኛ መሆን አይቻልም።” ይህንን ያሉት በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ፖል ኮሊየር ናቸው፡፡

‹The Bottom Billion› መጽሐፍ ደራሲው በዚሁ መጽሐፋቸው ላይ በተለይ ድህነት ባጠላበት ቀጠና እየኖሩ ወደብ አልባ መሆን ሀገር ስኬታማ የልማት ጉዞ እንዳይኖራት ወደ ኋላ ከሚመልሱ የልማት “ወጥመዶች” መካከል ዋነኛ ስለመሆኑም ያስረዳሉ። “የባህር በር ባለቤት ከሆንክ ዓለምን ታገለግላለህ” የሚለው ሀሳብ ምን ማለት እንደሆነ ሲያብራሩም የባህር መዳረሻ ለዓለም አቀፍ ትስስር እና ንግድ ወሳኝ መሆኑን ለማሳየት ስለመሆኑ ይገልጻሉ፡፡

ወደብ ለሌላቸው ሀገሮች ከሌላው ዓለም ጋር በሚያደርጉት የንግድ እንቅስቃሴ ላይ የተገደበ በመሆኑ ተፅዕኖው ጠንካራ ነው። የባህር በር የሌላቸው በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በባህር ዳርቻ ከሚገኙ አቻ ሀገራት ጋር ሲነፃፀሩ ለዓለም አቀፍ የሸቀጥ ትራንስፖርት ከፍተኛ ወጪ አለባቸው። ከባህር የራቁ ሀገራት ታሪክም የሚያሳየው ይህንኑ ነው። በአጠቃላይ የባህር መዳረሻ ማጣት ለአንድ ሀገር በፖለቲካ፣ በወታደራዊ እና በኢኮኖሚ ትልቅ ኪሳራ ስለመሆኑም ፖል ኮሊየር ያስረዳሉ።

ሰፊው ክፍሏ በባሕሮች እና በውቅያኖሶች በተሸፈነው ዓለም ላይ ከሚገኙት ወደ ሁለት መቶ ከሚጠጉ ሉዓላዊ ሀገራት መካከል 44ቱ የባሕር በር የላቸውም ይላል የዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት ይፋ ያደረገው መረጃ። ከእነዚህ ውስጥ 31 ያህሉ ደግሞ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ካዛኪስታን በቆዳ ስፋቷ ትልቅ ሆና ወደብ የሌላት ሀገር ስትሆን ኢትዮጵያ ደግሞ ትልቅ የሕዝብ ብዛት እና ሠፊ ግዛት ይዛ የባሕር በር ከሌላቸው የዓለም ሀገራት ዋነኛዋ ናት።

ወሳኙ ጥያቄ ታዲያ ዓለም እነዚህን ወደብ አልባ ሀገራት በምን መልኩ ልታስተናግዳቸው አሰራር ዘረጋች የሚለው ይሆናል፡፡ ወደ 169 የዓለም ሀገሮች የፈረሙበትና እ.ኤ.አ. በ1982 የወጣው ዓለም አቀፍ የባህር ሕግ (United Nations Convention on the Law of the Sea/UNCLOS)፣ የዓለም ሀገሮች የባህር ክልልና ወሰንን በምን መንገድ መጠቀም እንደሚገባቸው መሠረታዊ መርሆዎችን አስቀምጧል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1994 ወደ ሥራ የገባው ሕጉ የጠረፍንና የዓለም አቀፍ ውኃ ክልልን ምንነትና አጠቃቀም፣ እንዲሁም በባህር ወሰኖች የሚነሱ ውዝግቦችና የችግር አፈታት ሒደቶችን በዝርዝር አስፍሯል፡፡



ፎቶ ከገፀ ድር
በርካታ ሀገራት የባህር በራቸውን በጋራ በመጠቀም ማደግ ችለዋል

የአንድ ሀገር የውኃ ክልል ከባህር ጠረፍ እስከ 22 ኪሎ ሜትር ድረስ ያለውን የውኃ አካል ያጠቃልላል ይላል ይህ ሕግ፡፡ በዚህ የአንድ ሉዓላዊ የሀገሮች የባህር ክልል ላይ የትኛውም ሀገር ለሰላማዊ ጉዳይ እስከሆነ መተላለፊያ ሊከለከል እንደማይችል ተመልክቷል። ከአንድ ሀገር የየብስ ወይም የባህር ጠረፍ ተነስቶ እስከ 370 ኪሎ ሜትር በሚረዝመው የባህር አካል ላይ ደግሞ፣ አንድ የባህር በር ያለው ሀገር የራሱን የኢኮኖሚ ዞን (exclusive economic zone-EEZ) መመሥረት እንደሚችል ተገልጿል፡፡

የባህር በር ያላቸው ሀገሮች መብትና ዓለም አቀፍ ግዴታን በግልጽ የሚያስቀምጠው ይህ ሕግ በተለይ ከአንቀጽ 24 እስከ 26 ባለው ክፍል የባህር በር ባለቤት ነኝ በሚል ብቻ ሀገሮች እንዳሻቸው የመሆንና የማድረግ መብት እንደሌላቸው በቀጥታ ያብራራል፡፡ የባህር ወሰናቸውን ለሰላማዊ እንቅስቃሴ እስከሆነ ድረስ ለሌሎች ሀገሮች ዝግ ማድረግ በፍጹም እንደሚከለከሉ ያትታል፡፡ የባህር ክልላቸው ለባህር እንቅስቃሴ ሰላማዊና ምቹ ስለመሆኑ ለመላው ዓለም መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸውም ይላል፡፡

በሌላ በኩል በባህር ድንበራቸው ላይ ነዳጅ መሙላትን ጨምሮ የወደብና የትራንዚት አገልግሎት ለሚፈልግ መርከብ ያለ ልዩነትና ያለ አድልኦ ባወጡት ተመን ምክንያታዊ ክፍያ በመሰብሰብ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ ይፈቅዳል፡፡ በአጠቃላይ ሀገሮች የባህር በር አለን በሚል ብቻ በሌሎች ሀገሮች ላይ ጫና እንዳያሳድሩ ሕጉ ልጓም አበጅቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ እንደ ቀይ ባህር ስላሉ ጠባብ የባህር መተላለፊያዎች፣ የሀገሮች ትብብርና የውኃ አጠቃቀም የሚመለከት ነው፡፡ በጥቅሉም የባህር በር የሌላቸው ሀገሮች መብቶች፣ እንዲሁም የባህር በር ካላቸው ሀገሮች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነቶች በዝርዝር ሰፍሮ ይገኛል፡፡

እ.ኤ.አ. በ1963 በተቋቋመው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (OAU) ወይም በአፍሪካ ህብረት (AU) ቻርተር መግቢያ ላይ በግልፅ እንደሰፈረው የአፍሪካ ሀገራት የባህር በር የሌላቸውን ጨምሮ የባህር ላይ ተጠቃሚ የመሆን መብት እንዲኖራቸው በተለይ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በባህር ላይ የመጠቀም መብታቸው እንዲጠበቅ እውቅና ይሰጣል፡፡

እነዚህን የዓለም አቀፍ ህግጋት መሰረት በማድረግና በተጨማሪ አንዳንድ ሀገራት በስትራቴጂክ ወዳጅነት እና በዲፕሎማሲያዊ ጥረት ችግሮቻቸውን ማቃለል ችለዋል፡፡ በዓለም ላይ ያሉ በርካታ ሀገራት ወደብ ከሌላቸው መንግስታት ጋር ድንበር ይጋራሉ። የንግድ ስምምነቶች፣ የፖለቲካ ድርድርና ውይይት አማራጮችንም ተጠቅመው ለችግሮቻቸው እልባት ሰጥተዋል፡፡ የተወሰኑትን በማሳያነት እናቅርብ፡፡

መነሻችንን ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እናድርግ፡፡ የቬርሳይ ስምምነትን የአውሮፓ ሀገሮች ሲፈራረሙ ፖላንድ ወደብ አልባ ነበረች፡፡ እናም ከጀርመን መተላለፊያ (ኮሪዶር) ተሰጥቷት ወደብ እንድታገኝ ተደረገ፡፡ በቬርሳይ ውል፣ “የፖላንድ ኮሪደር” ተብሎ የተሰየመው የጀርመን ክፍል ለሁለተኛው የፖላንድ ሪፐብሊክ ወደ ባልቲክ ባህር ለመግባት የቻለችውም በዚሁ ስምምነት ነበር፡፡

እ.ኤ.አ. በ 2005 ከዩክሬን ጋር በተደረገው የመሬት ልውውጥ ምክንያት ሞልዶቫ 600 ሜትር (650 ያርድ) ርዝመት ያለው በዳኑቤ መዳረሻ ተቀብላለች። ዳኑቤ ዓለም አቀፍ የውሃ መንገድ ሲሆን ስለዚህም ወደብ አልባዎቹ ኦስትሪያ፣ ሃንጋሪ፣ ሞልዶቫ፣ ሰርቢያ እና ስሎቫኪያ ወደ ጥቁር ባህር አስተማማኝ መዳረሻ አላቸው።

> **የባህር በር የሌላቸው በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በባህር ዳርቻ ከሚገኙ አቻ ሀገራት ጋር ሲነፃፀሩ ለዓለም አቀፍ የሸቀጥ ትራንስፖርት ከፍተኛ ወጪ አለባቸው**

ለአብነትም በመካከለኛው አውሮፓ የምትገኘው ጀርመን ኦስትሪያን፣ ስዊዘርላንድን እና ሉክሰምበርግን ጨምሮ ከበርካታ ወደብ ከሌላቸው ሀገራት ጋር ድንበር ትጋራለች። ምንም እንኳን ጀርመን የራሷ የሰሜን ባህር እና የባልቲክ ባህር መዳረሻ ቢኖራትም ወደብ የሌላቸው ጎረቤቶቿ ዓለም አቀፍ የንግድ መስመሮችን ለማግኘት በወደቦቿ እና በመሠረተ ልማት አውታሮች እንዲጠቀሙ ታደርጋለች።

የአውሮፓ ህብረት እ.ኤ.አ 2020 ይፋ ያደረገው መረጃ መሰረት ስዊዘርላንድ ምንም እንኳን ወደብ አልባ ብትሆንም በጀርመን ወደቦች እንደ ሃምበርግ እና ብሬመን የመሳሰሉትን ወደቦች ለዕቃ ማጓጓዣ ትጠቀምባቸዋለች። በተመሳሳይ፣ ኦስትሪያ የጀርመን ወደቦችን ለዓለም አቀፍ ንግዷ በተለይም በራይን-ዳኑብ ኮሪደር በኩል ለመጓጓዣ ቁልፍ የሆነውን የውሃ መንገድ ትጠቀማለች። በመሆኑም ጀርመን እና ወደብ አልባ ጎረቤቶቿ በአውሮፓ ህብረት እና በአውሮፓ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ውስጥ በሚደረጉ ስምምነቶች ውስጥ በመሳተፍ ወደብን በጋራ ይጠቀማሉ፡፡

የንግድ ስምምነቶችንም እንደ አማራጭ በመጠቀም በጎረቤት ሀገራት በነፃ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማቅረብ ሀገራት ስምምነቶችን ይፈጽማሉ፡፡ የቬርሳይ ስምምነት ጀርመን ቼኮዝሎቫኪያን በሃምቡርግ እና ስቴቲን የሚገኙትን የወደብ ክፍሎች ለ99 ዓመታት የሊዝ ውል እንድታቀርብ ያስገድድ ነበር፣ ይህም በኤልቤ እና ኦደር

ወደ ገጽ 27 ዞሯል

# ከከተማ ወደ ገጠር የፈነጠቀው ብርሃን

- በመዲናዋ የተጀመረው የኮሪደር ልማት የገጠሩንም ውበት እየገለጠ ነው

**በመለሰ ተሰጋ**

"እምዬ ኢትዮጵያ" በሚለው የቴዎድሮስ ታደሰ ዘመን ተሻጋሪ የዘፈን ግጥም ውስጥ እልፍ ቁምነገሮች አሉ፡፡

"እምዬ ኢትዮጵያ ይመርልሽ ሰብሉ

አውድማው ጎተራዉ ይሁንልሽ ሙሉ

በቸር ዉሎ ይደር ጋራ ሸንተረርሽ ወንዛ ወንዝሽ ሁሉ፡፡" ይላታል ድምፃዊው፤ አዎ! ሀገራችን ከራስ ፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ድረስ ሰላም ትሁን፡፡ ግን ደግሞ የጎተራው ባለቤት፣ የልማቱ ጌታ፣ የገጠሩ ነዋሪ ያ! የሁላችን ምንጭ፣ አርሶና አርብቶ አደሩ ኑሮው ለዘመናት ችላ የተባለ ነው፡፡ ከእንስሳቱ ጋር አብሮ እያደረ ከዓመት እስከ ዓመት ከተሜውን እየመገበ እርሱ ግን ሁሉ እያለው፣ ሁሉንም እየሰጠን ተጎሳቅሎ ውሎ፤ ተጎሳቅሎ ያድራል፡፡

"በማጀትሽ ወተት በጤፍሽ እንጀራ

በማር በወለላሽ በጓሮሽ ሸንኮራ" እንዳለው፣ የገጠሩ ነዋሪ ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ ነው፡፡ እንግዳ ሲቀበል፣ ሲደግስ፣ ሲለግስ ስስትን አያውቅም፡፡ ዋናው ቁምነገር "ብድር አለብኝ ልክፈልና ልኩራ" እሚለው ስንኝ ላይ ነው፡፡ ያ! ያበቀለንን ምድር፣ ያሳደገንን የገጠሩ ነዋሪን ምን ያህል ብድሩን ከፍለነዋል?!



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሌሞ ወረዳ ዱባንቾ ቀበሌ የገጠር ኮሪደር መርሃ ግብርን ባስጀመሩበት ወቅት

ያበቀለንን ቀዬ፣ ያበብንበትን ምድር፤ በአካልም ያሸትንበትን፣ ሜዳና መስኩን፣ ከዚህ አለፍ ሲልም ሳይማር ያስተማረንን የገጠሩን ወገናችንን ውለታ ምን ያህል መልሰናል? የሚለው ነጥብ ሁሌም የማንቂያ ደውል ሆኖ በአርበ ልቦናችን እያቃጨለ ኖሯል፤ ይኖራል፡፡

"ለሁሉም ጊዜ አለው" እንዲል መፅሐፉ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሀሳብ አመንጭነትና የቅርብ ክትትል በአዲስ አበባ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ለሌሎች የሀገራችን ከተሞች ብቻ ሳይሆን ለገጠሩ ክፍልም የልማት ብርሃኑን እየፈነጠቀ ነው፡፡ በድምፃዊው ጠቆም የተደረገው "ብድር አለብኝ ልክፈልና ልኩራ" የሚለው ሀሳብ በተግባር እየተገለጠ ስለመሆኑ ምስክር አያሻም፡፡

ከሰሞኑም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሃዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ ዱባንቾ ቀበሌ በገጠር ኮሪደር ሞዴል የአርሶ አደሮች መኖሪያ መንደር የማስጀመሪያ መርሃ ግብር አከናውነዋል፡፡ እነዚህ ማሳያ መንደሮች መገንባታቸው አርሶ አደሩ የግብርና ስራ እያከናወነ የተሻለ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችሉ ስለመሆናቸውም ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የገጠሩን ኑሮ ሌላኛውን መጋረጃ በሚገባ ገልጠው የተጎሳቆለውን ኑሮ አስተውለን እንድናይ ከማድረጋቸው በፊት ፣

ወተቱ ከማጀት እሸቱ ከጓሮ፣

በጣም ያስደንቃል የገጠሩ ኑሮ...።" እያልን በስንኝ ቋጠሮ እንሸፋፍነው ነበር፡፡

እውቁ እንግሊዛዊ መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሮበርት ጀን ሃይሎክ "Rural Development: Putting the Last First" ወይም ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት የተዘነጋውን አሊያም "የመጨረሻውን ማስቀደም" የተሰኘ ድንቅ መፅሐፍ አላቸው፡፡ በዚህ የምርምር ስራቸው እንደገለፁት የገጠር ድህነት፣ ኑሮና ሁኔታ ብዙውን ጊዜ በውጭ ሰዎች በወጉ የማይታይ ወይም የተዛባ ግምት የተሰጠው ነው። ይህም በመሆኑ የገጠር አካባቢዎች በቀላሉ ሊስተካከሉ በሚችሉ ችግሮች ወይም አስተሳሰቦች ምክንያት የድህነት መገለጫ ሆነዋል ይላሉ፡፡

እንደ ኢትዮጵያም ገጠሩን መሰረት ያደረጉ በርካታ ስራዎች በየዘመናቱ የተከናወኑ መሆናቸውን የታሪክ ድርሳናት የሚያትቱ ቢሆኑም ገጠሩ ካለበት ችግር ወጥቶ ባለው ሀብትና ፀጋ ልክ የሚኖርበት ሁኔታ አለመፈጠሩ ግን ለብዙዎቻችን እንቆቅልሽና የሚያስቆጭም ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተሟላ ብልፅግናን ማረጋገጥ እንዲቻል ሕይወትን በቤተሰብ ደረጃ መቀየር የሚያስችሉ ማዕቀፎችን ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል፡፡ ለአብነት አረንጓዴ አሻራ፣ በምግብ እህል እራስን መቻል፣ የሌማት ትሩፋት፣ የኮሪደር ልማት እና መሰል የልማት መርሃ ግብሮች ወደ ተግባራዊ ምዕራፍ ተሸጋግረው ከቤተሰብ ተጠቃሚነት አለፍ ያለ ውጤትም እያስመዘገቡ ነው፡፡ የእነዚህ ስራዎች አላማም ሰብአዊ ልዕልናን ማረጋገጥ እንደሆነ መንግስት ይፋ ማድረጉ አይዘነጋም፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የገጠር ኮሪደርን አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክታቸው፣ የገጠር ኮሪደር ማለት የእያንዳንዱን አርሶ አደር ቤት የአኗኗር ዘዬ መቀየር ማለት ነው፡፡ የዚህ መርሃ ግብር ዋናው አላማ በቤተሰብ ደረጃ የአርሶ አደሩን ሕይወት መቀየር ነው፡፡ ምክንያቱም የገጠሩ ነዋሪን የአኗኗር ዘዬው ካልተቀየረ በስተቀር በሀገር ደረጃ የምናስበውን ብልፅግና አናረጋግጥም፡፡ የለማ ሀገር መፍጠር የሚቻለው ከቤተሰብ የሚጀምር ሁለንተናዊ ልማትን ማረጋገጥ ሲቻል እንደሆነም መግለፃቸው አይዘነጋም፡፡

ይህንን አስመልክቶ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ጀማ ሐጂ፣ በገጠሩ ክፍል በደንብ ገባ ብሎና ያላቸውን ሀብት ተረድቶ በቤተሰብ ደረጃ መስራት ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ወደ ገጠሩ የማህበረሰብ ክፍል ቀረብ ብሎ ያላቸውን ሀብት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የመሬት ስፋት፣ የቤተሰቡ አቅም እና መሰል ነገሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህንን ሀብታቸውን ምን ላይ ቢያውሉ የተሻለ ምርታማ ይሆናሉ፣ ባላቸው ሀብት ልክስ እንዴት ሊኖሩ ይገባል፣ የሚለውን ማመቻቸትና መንግስትም ደከም በሚሉበት ቦታ ድጋፍ ከሰጠ ምርታማነት ያድጋል፤ ይህ ማለት ደግሞ የሀገር ዕድገት በአስተማማኝ መልኩ እንዲረጋገጥ ያግዛል ብለዋል፡፡

አክለውም ስልጠና በመስጠትም የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የተሻለ ምርታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ከእርሻም ወጣ ያሉ ነገሮችንም እንዲሰሩ ማበረታታት ያስፈልጋል ያሉት ፕሮፌሰሩ በትክክል ከተሰራበትም የገጠር ኮሪደር ልማቱ ሀገርን ለመለወጥ የሚያስችል እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

የስነ ልቦና አማካሪ አቶ ማህደር ሳላይህ እንደሚሉት እንደ ሀገር በቤተሰብ ላይ የሰራናቸው ተግባራት በብዙ መልኩ ክፍተት ያሉባቸው ናቸው፡፡ በተለይም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊም ሆነ በተለያዩ ዘርፎች ንቁ የሆኑ የቤተሰብ አባላትን በመፍጠር ምቹና ጤናማ ሕይወትን የሚመራ፣ ለሀገር ዕድገት ባለው አቅምና ልክ የሚተጋ ትውልድን ከመፍጠር አንፃር የበለጠ መስራት ይኖርብናል። በሌላ በኩልም በዛ ያለው የገጠሩ የህብረተሰብ ክፍል የተመጣጠነ ምግብ፣ ልብስና መኖሪያ የማገኘት ዕድል እንኳ ቢኖረው ባለው ሀብት ልክ ያለመኖር ክፍተት ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ ከግንዛቤ ክፍተት የሚመጣ ነው፡፡

በሌላ በኩልም ከመኖሪያ ቤቱ እራቅ ብሎ ያለውን እርሻውን እንጅ በጓሮው የተለያዩ ልማቶችን ማከናወን እንደሚችል በሚገባ የመረዳትና በዚያው ልክ የመስራትም ክፍተት ይስተዋላል። ስለሆነም የገጠር ኮሪዶርን በመሳሰሉ ልማቶች በቤተሰብ ላይ በሁሉም ዘርፍ በመስራት ለለውጥ የሚተጋ ማህበረሰብን መፍጠር እንደሚያስፈልግም መክረዋል።

አክለውም በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረውና በአስደናቂ ለውጥ የታጀበው የኮሪደር ልማት የሀገሪቱን ሌሎች ከተሞች ከማነቃቃት አልፎ ለገጠሩ ክፍልም ትልቅ ተምሳሌትና የልማት ስንቅ እየሆነ ነው፡፡ ይህም ከተማዋ በተለወጠች ቁጥር እንደሀገር ተምሳሌትነቷ ከፍ ይላል፡፡ ይህም በቀላሉ ሌሎች የሀገራችንን ክፍል ማልማት እንድንችል ስንቅና ጉልበት ይሆነናል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በሀገሪቱ ከተሞች እና በገጠሩ ክፍል እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማት ስራዎች ለዚህ ማሳያ እንደሆኑም አመላክተዋል፡፡

የገጠር አካባቢዎች እየዘመኑ እና እየበለጸጉ ሲሄዱ፣ የአኗኗር ዘይቤያቸው ይቀየራሉ፡፡ ይህንንም ተከትሎ የተሻለ ሀብትን የሚያፈሩበት ዕድል ይፈጠራል፣ ነዋሪዎች በተሻለ የመኖሪያ ቤት እንዲኖሩ ያደርጋል፣ በትምህርት፣ በጤና እና መሰል ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋልም፡፡ ይህም ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገትን ከማረጋገጡም በላይ ሁለንተናዊ ደህንነቱ የተረጋገጠ ማህበረሰብንም ለመፍጠር እንደሚያግዝም ጠቁመዋል፡፡

በኮሪደር ልማት እንደ አዲስ አበባ፣ ውበቱ እንዲፈካ፣ አርሶና አርብቶ አደሩ ውሎና አዳሩ እንዲያምር፣ በአቅሙና በሚገባው ልክ ደስ ብሎት እንዲኖር በምንችለው ሁሉ እንደግፈው ዘንድ ኑ! ገጠር እንሂድ፡፡

# ኢትዮጵያውያን ሀጃጆች ‘በምህረት ተራራው’

በሳህሉ ብርሃኑ

መካ፣ ሚናና አረፋ የሚሰኙ ስፍራዎች አቅሙ የፈቀደለት አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ቢያንስ አንድ ጊዜ እንዲሄድ የሚገደድባቸው ቅዱስ ስፍራዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ስፍራዎችን ለመጎብኘት ታዲያ የኢኮኖሚ አቅም ብቻ በቂ አይደለም፡፡

እጅግ አስቸጋሪና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ፣ አናት የሚበሳውን ፀሐይ፣ ከባዱን ሀሩር ተቋቁሞ ማለፍም የግድ ነው፡፡ መዳረሻው ደግሞ ቅዱሱ ስፍራ (Mount of Mercy) “አረቦች ጀበል አል ራህማ (የምህረት ተራራ)” በማለት የሚጠሩት የአረፋ ተራራ ነው፡፡

የእስልምና እምነት መነሻ የሆነችውን መካን መጎብኘት የሙስሊም ሁሉ ግዴታ ነው፡፡ በሙስሊሞች ላይ የተጣለው መካን የመጎብኘት ግዴታ የተግባሩን ትልቅነት በሚያሳይ “ሀጅ” የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ሀጅ ማድረግ ደግሞ የአንሷር መስጅድ ኢማም ሼህ ሙሀመድ ሳሊህ እንደሚሉት ከአምስቱ የእስልምና ማዕዘናት መካከል አንዱ ነውና ማንኛውም አቅም ያለው ሙስሊም በህይወት ዘመኑ ቢያንስ አንድ ጊዜ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

በእስልምና እምነት አስተምህሮ ሀጅ የዕድሜ ልክ ኢባዳ (ፈጣሪ የሚወደው ስራ) ነው ይላሉ የዕምነቱ ተከታዮች፡፡ በእርግጥ ሀጅ በምዕመናኑ ዘንድ ግዴታ የማሟላት ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ በፍቅር የሚያደርጉት፣ አቅሙ የሌላቸው ደግሞ ሀጅ ሳያደርጉ እንዳይሞቱ ለፈጣሪ ፀሎት የሚያደርሱበት የውዴታ ግዴታ ነው፡፡ ከመካ በስተምሥራቅ 20 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘውን ቅዱስ ተራራ መመልከትና ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓቶችን በዚያው መፈጸም እንደሚገባም የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ ያዛል።

በሀጅ ወቅት አማኙ ምን እንደሚፈጽም የሚያስረዱት አየር ጤና አካባቢ የአንሷር መስጅድ ኢማም ሼህ ሙሀመድ ሳሊህ ጀማል ሀጅ፣ የሚያደርግ ሰው ከያለበት ተሰባስቦ መካ ያርፋል፡፡ ስንቁን አዘጋጅቶ ጉዞውን ይጀመራል፡፡ ሀጅ እስከሚያልቅ ዝክር፣ ውዳሴ፣ ቁርአን መቅራት ሰላትና ዱአ በማድረግ ፈጣሪውን ያመሰግናል፡፡

ይህም በእስልምና ሐይማኖት የመጨረሻው መልዕክተኛ ናቸው ተብለው የሚታመኑት ነቢዩ መሀመድ(ሰ ዐ. ወ) የመጨረሻ ጸሎት እስካደረጉበት ቦታ አረፋ ድረስ ይቀጥላል። ሀጃጆችም በሀጅ ጸሎታቸው የነቢዩን ተምሳሌት በመከተል በአረፋት ኮረብታ ዙሪያ በነሚራ መስጅድና በምህረት ተራራ “ጀበል አረፋ” ላይ ሙሉ ቀን ጸሎት ሲያደርጉ ይውላሉ፡፡

የአረፋ በዓል የእምነቱ ተከታዮች ቋንቋ ሳይገድባቸው፣ የቆዳ ቀለም ሳይለያቸው፣ ስፍራና ማንነት ሳያግዳቸው በአንድ አይነት አለባበስ በአንድነት በቅድስቲቱ ምድር መካ በመሰባሰብ ጥያቄያቸውን ለፈጣሪ የሚያቀርቡበትም ስለመሆኑም ሼህ ሙሀመድ ሳሊህ ያስረዳሉ።

ሼህ ሙሀመድ እንደሚሉት የአረፋ በዓል በሁለት አይነት መልኩ ይከበራል፣ አንደኛው ሃይማኖታዊ መስፈርቶችን ጠብቆ ወደ መካ በመሄድ የሚደረግ የጸሎት ሥነሥርዓት ሲሆን የሀጂ ተጓዦች ከሚከውኗቸው አበይት ሃይማኖታዊ ተግባራት አንዱና ዋንኛው የአረፋ ተራራን መውጣት ሌላኛው ነው። የጤናና የገንዘብ አቅማቸው የፈቀደላቸው የሀይማኖቱ ተከታዮች ቢያንስ በሕይወት ዘመናቸው አንድ ጊዜ ቅድስቲቱን ምድር መካን በሀጅ ሥርዓት መካፈል ይጠበቅባቸዋል።

በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል ከአምስቱ የእስልምና መሰረቶች አንዱ የሆነው የሀጅ ሥነ-ሥርዓት የሚከወንበት ታላቅ በዓል ነው የሚሉት የአብደላ ኢብኑ አባስ መስጂድ ኢማም ሸይኽ ሙሀመድ ሲራጅ የሀጅ ዋጅብ (ግዴታዎች) ናቸው ያሏቸውን ጉዳዮች ያብራራሉ፡፡ ፀሐይ እስክትጠልቅ አረፋ ላይ መቆም፣ የአያመል ተሽሪቅ ሌሊቶችን ሚና ማደር፣ ጀመራት ላይ ጠጠር መወርወር፣ ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር፣ የመሰናበቻ ጠዋፍ ማድረግ ከግዴታዎቹ መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የበዓሉ ስም የእስልምና ትልቅ ቦታ ካለው እና በመካ አካባቢ ከሚገኘው የአረፋ ተራራ ጋር የተሳሰረ መሆኑን የሚያነሱት ኢማሙ፣ ህዝበ ሙስሊሙ ለ9 ቀናት ከበዓሉ አስቀድሞ እንደሚጾም ይናገራሉ፡፡ በአረፋ ወቅት ከሚከናወኑ ሃይማኖታዊ ተግባራት አንዱ የሀጅ ሥነ-ሥርዓት፣ ካእባን መዘየር እና ጠዋፍ መጠወፍ እንዲሁም የእርድ ሥነ-ሥርዓት መሆናቸውን ጨምረው ገልጸዋል።

እንደዚሁም የአላህን ቤት ይዞራሉ፣ ጠጠር ይወረውራሉ፣ ሌሎችም ተምሳሌታዊ ተግባራትን ያከናውናሉ። በምድረ በዳ ላይ ለእስማኤል ከፈለቀለት ዘምዘም ውሃ ይጎነጫሉ። ሀጃጆች በቆይታቸው እኩልነታቸውን እንዲያንፀባርቅ “ኢህራም” የሚባለውን ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ይደረጋል፡፡ ይህ ነጭ ልብስ እኩልነትን ብቻ ሳይሆን ሰዎች በፈጣሪ ፊት ሲቀርቡ ምንም ሳይዙ መሆኑንም የሚያሳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን የእስልምና ዕምነት ተከታዮችም በስፍራው ተገኝተው በዓመታዊው የሀጅ ጉዞ ፍጻሜው የአላህን ይቅርታ፣ ሰላምና ምህረት ለማግኘት እጃቸውን ዘርግተው ይለምናሉ፡፡ ሀጃጆች “ጥሪህን ተቀብለን መጥተናል” የሚለው ልዩ የሀጀ ጸሎት በህብረት ይዘምራሉ፡፡

መካ ከደረሱም በኋላ ንጋት (የፈጅር ጸሎት) ድረስ ሚና ላይ ጸሎት ከውነው ወደ አረፋ ያቀናሉ፡፡ ወግፍ አረፋ በሚባለው የአረፋ ተራራና ኮረብቶች ተሰብስበው ፊታቸውን ወደ ፈጣሪ በማቅናት በጥልቅ ስሜት ጸሎተ ምህላ ያደርጋሉ፡፡ ነጭ ካባ ለብሰው ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻ ስብከታቸውን ያደረጉበትን የአረፋትን ሜዳ የሚቆጣጠረውን ዓለታማውን የምህረት ተራራ በመውጣት በዓሉን ማክበርም ለዓመታት ሲከወን የቆየ አይማኖታዊ ኢባዳ ነው፡፡

እንደ ሼህ ሙሀመድ አስተያየት እንደ ዛሬው በአውሮፕላን በረው ወይም ዱሩን በመኪና አቋርጠው፣ ባህሩን በመርከብ ገስግሰው በሰዓታት በሚደርሱበት የሚከውኑት ጉዞ አልነበረም፡፡ በወቅቱ በነበረው የመጓጓዣ ዘዴ ተጠቅመው ነበር የእምነቱ ተከታዮች ከያሉበት መካ ላይ የሚሰባሰቡት፡፡ ግመልና ፈረሶች ብቸኛ መጓጓዣ በነበሩበት በዚያ ዘመን የነበሩ እንኳ መካ እስኪደርሱ ወራትን ፈጅተው ከአድካሚ ጉዞ በኋላ ነበር መካ የሚደርሱት፡፡

በእግርና በግመል ተጭነው መካ የገቡ ኢትዮጵያውያንም እንዳሉ የሚነገር ሲሆን ከዚህም ባሻገር ሀጅ የማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ነገር ግን አቅሙም ጉልበቱም የሌላቸው ኢትዮጵያዊ ዓሊሞች ባልታወቀ ተዓምር መካ ደርሰው እንደታዩም በታሪክ ይነገራል፡፡

ሀጃጆች በከፍተኛው ሙቀት ረዥም ርቀት በእግራቸው ይጓዛሉ። በበጋ ወቅት አንድ ሀጅ በቀን ወደ 15 ኪሎ ሜትር በእግር ሊጓዝ ይችላል። ይህም ለከፍተኛ ሙቀት፣ ድካም እና ለውሃ እጥረት ያጋልጣቸዋል። ለተጓዦች በተዘጋጁ መጠለያዎች ውስጥ እስከ 51 ነጥብ 8 ዲግሪ ሴልሺየስ የሚደርስ ሙቀት ውስጥ መገኘት ግድ ይላል፡፡ ሀጃጆች ብዙም ባለመዱት ሙቀት፣ በአድካሚ የእግር ጉዞ፣ መተፋፈግና በላብ መዘፈቅ ባስ ሲልም በሀጅ ወቅት በከፍተኛ ሙቀት ሳቢያ የሚከሰት ሞት አዲስ አይደለም። እዚህ ጋር ከአመት በፊት የተከሰተን ሁነት አስታውሰን እንለፍ፡፡

በዓለማችን በርካታ ሕዝብ ከሚታደምባቸው ሁነቶች ውስጥ አንዱ በሆነው የሀጅ ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ሳዑዲ አረቢያ ይጓዛሉ። ከአንድ ዓመት በፊት የሀጅ ጉዞ የተጠናቀቀው ግን በአሳዛኝ ሁኔታ ነበር። አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ይፋ ባደረገው አሃዝ የ10 ሀገራት ዜግነት ያላቸው ከ1 ሺህ በላይ ሀጃጆች ህይወታቸው ማለፉ ተረጋግጧል። የአብዛኞቹ ሞት ምክንያትም ከከፍተኛ ሙቀት ጋር የተያያዘ ነው ተብሏል።

ሀጅ ጉዞን በተመለከተ ከወደ ኢንዶነዢያ የተሰማውን እጅግ አስገራሚ ተግባር አቅርበን ጉዳያችንን ወደመቋጨቱ እንለፍ፡፡ በፅዳት ሰራተኝነት የሚተዳደሩ ባልና ሚስቶች ሀጅ ሊያደርጉ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ያቀኑት ለ40 ዓመታት በመቆጠብ ነበር።

ሀጅ ለማድረግ ሳዑዲ አረቢያ የገቡት ኢንዶነዢያዊ ባልና ሚስቶች እንደገለፁት ሀጅ ለማድረግ በህይወት ዘመናቸው በሙሉ ሲመኙት የነበረና ለዚያም ለሀጅ ብቻ በሚል ለ40 ዓመታት ሲቆጠቡ እንደነበር በማንሳት “አላህ በዚህ ዓመት እንድንሄድ ስላደረገን አልሀምዱሊላህ” በማለት ምስጋናቸውን አቅርበዋል። በዓለም ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሀጃጆችን በመላክ ኢንዶኖዢያ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የምትመደብ ሲሆን ዘንድሮም ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ሀጃጆች ወደ ሳዑዲ አረብያ እንደሚያቀኑ ተገልጿል።

በአጠቃላይ የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በእስልምና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት አንዱ ነው። በዓሉ በእምነቱ አስተምህሮ መሠረት ነብዩ ኢብራሂም የአላህ ትዕዛዝን ለመፈጸም በፍጹም ትህትና እና ታዛዥነት ልጃቸው እስማኤልን ለመስዋዕትነት ያቀረቡበት ስለመሆኑም የዕምነቱ አስተምሮ ይነግረናል፡፡ በበዓሉም ወቅት የሀጅ ስነ ስርዓት የሚከናወን ሲሆን በየዓመቱም እስከ 3 ሚሊዮን የሚጠጋ ሙስሊም ከመላው ዓለም ወደ ሳውዲ አረቢያ በማቅናት ሥርዓቱን ይታደማል፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችም የዚሁ አካል ናቸው።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በ1 ሺህ 446ኛው ዓመተ ሒጅራ ከስድስት ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን አረፋት ተራራ ላይ የሀጅ ስርዓት አከናውነዋል

## “ሪፎርሙ ... ከገጽ 1 የዞረ

በኢትዮጵያዊነት ትልቅ ማንነት ማዕቀፍ ውስጥ ነው” ብለዋል፡፡

ማንነትን የምንረዳበትን መንገድ መፈተሽ እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስተዋል፡፡ አንደኛውን ማንነት በማጉላት፤ ሌላውን የምናኮስስ ከሆነ የኢትዮጵያዊነት ምንነትና ትርጉም ሚዛኑን ይስታል፡፡ ኢትዮጵያዊ ማንነት ሰብሰብና ተለቅ ያለ ነው፡፡ ከኢትዮጵያዊነት በታች ማንነቶች አሉ። ነገር ግን ወደሚያሰባስብ፣ የሚያፀና፣ የሚያዛልቅ ማንነት መሰብሰብ ይገባል ብለዋል፡፡

“ስንኖር ኢትዮጵያዊ፤ ስንሞት ኢትዮጵያ” የሚለው ንግግራቸውም ለመጪው ትውልድ የፀናች፣ የለማች፣ የማትለምን ሀገር እንዴት እናቆያለን ከሚለው ሀሳብ ጋር ተሰናስሎ መታየት እንዳለበት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አስገንዝበዋል፡፡

“ሀገር የትውልድ ቅብብሎሽ ውጤት ናት፡፡ ትውልድና ነገን እያሰብን መስራት ይኖርብናል፡፡” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ነገን ስናስብ ግን ትናንትንም በማየት መሆን እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ መንግስት ትናንትን “አከብራለሁና እጠብቃለሁ” ሲልም በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባርም እያሳየ እንደሚገኝ አንስተዋል፡፡ በቅርብ ዓመታት የላል ይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን፣ የፋሲል ቤተ መንግስትን፣ የአባ ጅፋር ቤተ መንግስትን እና የምኒልክ ቤተ መንግስትን ልጠግን ያለ መንግስት ተሰምቶ አይታወቅም፡፡ ሌላው ቀርቶ የሉሲ ቅሪተ አካል መገኛ፣ አንድ ለእናቱ የሆነው ብሔራዊ ሙዚየም በውስጡ ብርቅና ድንቅ የሆኑ ቅርሶችን ቢይዝም ዞሮ የሚያየው ባለመኖሩ ለመጎብኘት ምቹ እንዳልነበረ አብራርተዋል፡፡

“ትናንትን ብቻ በመጠገንም ነገን መስራት አይቻልም” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ ለምሳሌ አንድነት ፓርክ ወይም ብሔራዊ ቤተ መንግስትን ብቻ በመስራት ነገን መስራት አይቻልም፡፡ መሀከል ላይ አገናኝ መንገድ፣ ወዳጅነት ፓርክ፣ ሳይንስ ሙዚየም መስራትን ያስፈልግ ነበር። ዛሬ ሊሟላ የሚገባው ክፍተት ሲሟላ፤ ትናንትን መቆየት ሲችል፤ ነገ ያማረ ነገር ማየት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያዊነት ሲመቸን፣ ጥቅም ስናገኝበት የምናዜመው፤ ሲከፉን፣ ሳይመቸን ሲቀር፣ ህልሞቻችን ሲጨነጋገፉ የምንተወው የወረት ጉዳይ አይደለም። በከፍታም በዝቅታም፤ ሲመቸንም ሳይመቸንም የምንኖረው ነው ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የፖለቲካ ሀይሎች በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ፣ ከውጭ እንዲገቡ መደረጉ፣ የፖለቲካ እስረኞች መፈታትና ሌሎችም የተወሰዱ እርምጃዎች ላይ የሚሰጡ የተለያዩ አስተያየቶችን በተመለከተም ምላሽ ሲሰጡ በወቅቱ ኢትዮጵያ የነበረችበትን ሁኔታ ዞር ብሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡ የለውጡ ሀይል የተረከባት ኢትዮጵያ 59 በመቶ የሚሆነው የሀገር ውስጥ ምርቷን የሚሸፍን ዕዳ የነበረባት፣ አበዳሪዎችና




ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ባለሀብቶች ዕዳው ካልተከፈለ ብድር መስጠትም ሆነ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ ያቆሙበት ጊዜ ነበር፡፡

ሁለተኛ በርካታ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ቆመዋል፡፡ ለምሳሌ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታው በመጓተቱ ተቋራጩ እንደገና ለመጀመር ‘ስራውን እንዳልሰራ አዘግይታችሁኛል፤ በጊዜ አልከፈላችሁኝም፤ ኪሳራ ደርሶብኛል’ በሚል አንድ ቢሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፈለው ጠይቆ እንደነበር አንስተዋል፡፡

ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት ሀገር መሆኗ ሌላው ፈተና እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡ ከተቋማት ግንባታ አኳያም የነበሩት ተቋማት የተሰጣቸውን ተልዕኮ መወጣት የማይችሉ፣ ከመንግስት፣ ፓርቲ፣ ዘር፣ ሰፈር፣ ኃይማኖት ለመለየት የሚያስቸግሩ ድቀት ያለባቸው ነበሩ፡፡ አሳሪ ህጎችም ነበሩ፡፡ ከዚህ ባሻገር ከፋፋይና በታኝ ትርክት፣ የፖለቲካና የመገናኛ ብዙሃን አውዱም የተሳከረ ነበር ሲሉ የነበሩ ችግሮችን አብራርተዋል፡፡

መዋቅራዊ ችግሮቹን ለመሻገር ጠንከር ያለ ውሳኔ ማሳለፍን ይጠይቅ ስለነበር፣ ተቃዋሚ ሀይሎች ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ፣ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱና ሌሎች የፖለቲካ ምህዳሩን የሚያሰፉ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በወቅቱ እስረኞች እንደ ጥፋታቸው በትክክል እየተመዘኑ ይፈቱ ቢባል የተቋም ስብራት ስለነበር ያንን ማድረግ የሚቻልበት ዕድል እንዳልነበረ ገልፀዋል፡፡

ለውጡን ተከትሎ የተወሰዱ እርምጃዎች ጥቅም አስገኝተዋል፤ ውስብስብ ችግሮችንም ፈጥረዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ መንግስት በተቻለ መጠን ጥቅሙን የማሳደግ፣ ጉዳቱ ደግሞ እንዲቀንስ ጥረት ማድረጉን አስረድተዋል፡፡

### በፈተና ውስጥ የተገኙ ስኬቶች

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፣ በኢትዮጵያ ባለፉት ሰባት ዓመታት በርካታ ፈተናዎች ቢያጋጥሙም ለማመን የሚከብዱ ተአምራዊ የሚባሉ ድሎች ተመዝግበዋል፡፡ ለምሳሌ የጸጥታ ማስከበር ተቋማት (መከላከያ፣ ደህንነት ...) ከለውጡ በፊትና ዛሬ ያላቸውን ብቃት ማወዳደር አይቻልም፡፡ አሁን ላይ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና አንድነት በተሟላ መንገድ መጠበቅ የሚያስችል አቅም ተገንብቷል፡፡

የኮቪድ 19 ወረርሽኝም ሌላው ፈተና እንደነበር ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ “አንድም መሬት ፆም ማደር የለበትም” በሚል ባዶ የነበሩ መሬቶችን ለእርሻ በማዋል፣ ወቅቱ እንቅስቃሴዎች የተገደቡበት ቢሆንም የኢትዮጵያ አየር መንገድ አገልግሎቱን ወደ ጭነት በመቀየር፣ ያለ መንግስት ድጎማ ዓለምን በማገናኘት ከፍተኛ እድገት ማስመዝገቡ ፈተናን የመወጣት ማሳያዎች እንደሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

ሌላው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጠየቁት የፕሮጀክቶች ግንባታ ሲከናወን በአካል በመገኘት የሚያደርጉት የቅርብ ክትትል ከምን መነጨ? የሚለው ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም (ዶ/ር) ጠንካራ ተቋማት በሌሉበት ሀገር ህልም ያላቸው ሰዎች፤ ህልማቸው እውን ሆኖ ለማየት ተጨማሪ ቁርጠኝነት በመያዝ ይሰራሉ። በታሪክም የተለያዩ ሀገራት መሪዎች ሀገራቸውን ለመገንባት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጉ እንደነበር አንስተዋል፡፡

በኢትዮጵያም የአንድነት ፓርክን ለመገንባት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደ ፕሮጀክት ማናጀር በመሆን ስራውን መምራታቸውንና ከዚያ በኋላ ግን በሚሰሩ ፕሮጀክቶች ሀሳቡን የተጋሩ፣ ልምድ፣ እውቀትና ክህሎት ያላቸው አመራሮች እንዲፈጠሩ ማስቻሉን አብራርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የግንባታ ሂደትም የሁለተኛው ዙር የውሃ ሙሊት እስከሚከናወንበት ጊዜ ድረስ በየቀኑ ክትትል ያደርጉ እንደነበር ተናግረዋል። በተለመደው አሰራር በጀት ከመመደብ ባሻገር መሪዎች ከቢሮ ወጥተው ስራዎችን ስለማይመለከቱ የውሸት ሪፖርቶች ይቀርባሉ፡፡ በአካል ተገኝቶ ስራዎችን ማየት ክፍተቶችን ለማስተካከል የሚረዳ በመሆኑ በየትኛውም ቦታ አመራሮች ስራን ወርደው ማየት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

### ኢኮኖሚውን በተመለከተ

ሀገራዊ ለውጡ ከመምጣቱ በፊት የዋጋ ግሽበት በኢትዮጵያ ውስጥ ከ20 ዓመት ያላነሰ ጊዜ በተከታታይነት እያደገ ሲመጣ ነበር። ከዚህ ችግር ለመውጣት ጥረት በሚደረግበት ወቅት የኮሮና ወረርሽኝ እንዲሁም የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት መከሰቱ ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ሀገራት ለራሳቸው ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረጉን አስታውሰዋል። በሀገሪቱ የተከሰቱ ግጭቶች መንግስትና ህዝብ ሙሉ አቅሙን በኢኮኖሚ ላይ እንዳያውል በማድረግ ችግር ፈጥሯል፡፡

ይህንንም ችግር በምዕራፍ በመከፋፈል፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ በማፍታታት አቧራውን ለማራገፍና እሴት ለመጨመር የመሞከር ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ማንሰራራት እንዳለብን በመግባባት፣ ቀስ ያለው አካሄድ ከነበርንበት ችግር እንደማያወጣ በመገንዘብ ተቋማትን በመገንባት፤ “እንፍጠን” በሚል ውሳኔዎችን በማሳለፍ የተለያዩ ስራዎች መሰራቱን አስታውሰዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) የኑሮ ውድነት ሰራተኛው ላይ የሚያሳድረውን ጫና ለማቃለል መንግስት ከወሰደው እርምጃ ጋር በተያያዘም በሰጡት ማብራሪያ፣ ባላፉት ሰባት ዓመታት በአማካይ የኢትዮጵያ መንግስት ለደመወዝ የሚያወጣው ገንዘብ በየዓመቱ በአማካይ 21 በመቶ ይጨምራል፡፡ ይህ ወጪ ግን ከእያንዳንዱ ሰራተኛ ኪስ ይገባል ማለት አይደለም፡፡ በሀገር ደረጃ የመንግስት ሰራተኛው ቁጥር ከለውጡ በፊት ከነበረበት 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን አካባቢ፤ አሁን ላይ ከ2 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ደርሷል፡፡

ይህም የሆነበት ምክንያት በዘርፍ ብናይ ለምሳሌ ከለውጡ በፊት ከነበረው የመምህራን ቁጥር 36 በመቶ አድጓል። ለመምህራን የሚወጣው ደመወዝ 36 በመቶ ጨምሯል ማለት ነው፡፡ የመምህራን ቁጥር እንዲያድግ የተደረገው ትምህርት ላይ ያለውን ስብራት ለመጠገን ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ቀዳማይ ልጅነት ላይ ስለማይሰራ ትውልዱ ላይ ብዙ ችግሮች አጋጥሟል፡፡ ይህንን ለመቅረፍ ከ35 ሺህ በላይ መዋዕለ ህፃናት መገንባቱንና የመዋዕለ ህፃናት መስፋፋት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በጤናው ዘርፍም ከነበረው የጤና ባለሙያ 53 በመቶ መጨመሩን አንስተዋል፡፡ በዘንድሮው ዓመት ለደመወዝ 91 ቢሊየን ብር ጭማሪ ተደርጓል፡፡ ይህም እጅግ ዝቅተኛ ተከፋዮችን ታሳቢ በማድረግ የተወሰነ እንደነበር ያስታወሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ይህ የሆነው ሀገር የሚበቃት ኖሯት ሳይሆን ካለው ላይ በመቀናነስ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ ሃኪሞች ካነሱት ጥያቄ ጋር በተያያዘም በሰጡት ማብራሪያ፣ አብዛኛው ሀኪም ያነሳው ጥያቄ ተገቢነት ያለው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የደመወዝ ጥያቄ መምህሩንና ሌላውንም ሰራተኛ የሚነካ እንደሆነና ጥያቄውን ለመፍታት ማስተዋል እንደሚጠይቅ አንስተዋል። “...ሁላችንም የደመወዝ ጥያቄ አለብን። በሰከነ መንገድ አቅማችንን እያገናዘብን ምላሽ እየሰጠን መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ... ሰክነን እንወያየለን፤ ሁሉንም አሸናፊ በሚያደርግ ሁኔታና ሀገርን በማይጎዳ መንገድ መፍትሔ እያበጀንለት እንሄዳለን” ሲሉ ተናግረዋል።

“የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ተአምራዊ የሚባል፣ የለውጥ ሀይሉ ካሰበው ጥራትና ፍጥነት በላይ ውጤት የተመዘገበበት ነው፡፡” ያሉት ጠቅላይ

ወደ ገጽ 27 ዞሯል

# የዘመናት ... ከገጽ 1 የዞረ

በማድረግ የሚከናወን ነው፡፡ የሀጂ ሥነ ስርዓት ማካሄድ፣ አላህን ማመስገን፣ እርድ መፈፀም እንዲሁም ከቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመድ ጋር በደስታ ማሳለፍ ሌሎች ከበዓሉ ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ ተግባራት እንደሆኑ ሼህ አብዱልመናን ያነሳሉ፡፡

ነብዩ በስተርጅና ያገኙትን የበኩር ልጃቸውን ለአላህ ለመሰዋት ያሳዩት ቁርጠኝነት፣ ታዛዥነትና ፅናት ትልቅ ቁም ነገር አለው፡፡ ለፈጣሪ መታዘዝ ውጤት ያመጣል፡፡ ነብዩ ኢብራሂም ፈተናውን በመወጣታቸውና በመታዘዛቸው በልጃቸው ምትክ በግ መጥቶላቸው አርደዋል፡፡ አሁን ዓለም ላይ የሚታየው የሰላም እጦት፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሱ የፈጣሪን ትዕዛዝ ካለማክበርና የመታዘዝ እሴት መሸርሸር ጋር ተያይዞ የመጣ እንደሆነ ሼህ አብዱልመናን ይናገራሉ፡፡

ኢትዮጵያም የተለያየ እምነት፣ ቋንቋ፣ ፍላጎት... ያላቸው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተጋምደው የሚኖሩባት ሀገር ናት፡፡ ይሁን እንጂ የአብሮነት እሴቶች እየተሸረሸሩ በመምጣታቸውና የሀሳብ ልዩነቶችን በሰላማዊ አካሄድ የሚፈቱበት ሁኔታ ባለመፈጠሩ ሰላምና አለመረጋጋት እያጋጠመ ሀገርን ወደኋላ ሲጎትቱ ቆይተዋል፡፡ “ስለሰላም አስፈላጊነት ለኢትዮጵያውያን መናገር ለቀባሪ ማርዳት ነው፡፡ የሰላም እጦትን ከማንም በላይ ያውቁታል፡፡” የሚሉት ሼህ አብዱልመናን፣ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ታዛዥነትን፣ መከባበርን፣ መደማመጥን መለማመድ ይገባናል ብለዋል፡፡

የተለያዩ ፍላጎቶችን አጣጥሞ ለመሄድ፣ ህዝቦቿ ተከባብረው፣ በወንድማማችነትና እህትማማችነት መኖር የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር፣ ሀገር እንደ ሀገር እንድትቀጥል መስራት ይገባል፡፡ ይህንን መፍጠር ከተቻለ የአሁኑም ሆነ የወደፊቱ ትውልድ ትኩረት ድህነት ላይ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ምክክሩ ፍሬያማ እንዲሆን ህዝቡ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ፣ የሚገኘውን ግብዓትም ወደ ተግባር ለመቀየር የሚያደርገውን አስተዋፅኦ ማጠናከር እንዳለበት ሼህ አብዱልመናን ያስገነዝባሉ፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባለፈው ዓመት የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በተከበረበት ወቅት ያስተላለፉት መልእክትም የበዓሉ አንድምታ እየተካሄደ ላለው የምክክር ሂደት ብዙ የሚያስጨብጠው ቁም ነገር እንዳለ ያመለክታል፡፡

“በኢትዮጵያ ሳይፈቱ ሲንከባለሉ የመጡና በዘመናችን የተፈጠሩ አሁናዊ ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች በመፍታት ሀገርን ለማዳን፣ የህዝብን ጥቅም ለማስከበር፣ ከዛሬ የተሻለ ነገን ለመፍጠር ልክ እንደ ነብዩ ኢብራሂም ብዙ ነገሮችን መስዋዕት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን ለመፍጠርም ነፍጥን መጣልና የራስን ዋሻ ትቶ ወደ መስክ መውጣትን፣ ምኞትንና ፍላጎትን መተው ይፈልጋል። ከመቀበል በላይ መስጠትን ይሻል፡፡ እንደ ኢብራሂም በጣም የምንሳሳለትን ነገር ለመሠዋት መቁረጥ ይፈልጋል። ሁላችንም ለመሥዋዕትነት ከተዘጋጀን የማይሳካ


ፎቶ- ከገፀ ድር
ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የህዝብ ድጋፍ ወሳኝነት አለው

የሰላም መንገድ የለም፡፡” ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ “ምክክር የሚሳካው የተሻለ ሐሳብና የላቀ እውቀት በማዋጣት ብቻ አይደለም። ሌላ ወሳኝ ነገር ይፈልጋል፡፡ እርሱም መስዋዕትነት ነው፡፡ የራስን ፍላጎት መሰዋት መቻል አለብን፡፡ ለትልቅ ግብ ሲባል ይቅርብኝ ማለት አለብን፡፡ ከእኔ የተሻለ ሐሳብና ልምድ፣ እውቀትና ጥበብ ሊኖር ይችላል ብለን ማመንና መቀበል አለብን፡፡ ለተሻላ መገዛት አለብን፡፡ እንደ ኢብራሂም ያሳደግናቸውን ብቻ ሳይሆን አብረውን ያደጉትን ብዙ ጠባዮች ለመሰዋት መዘጋጀትን ይጠይቃል” ሲሉም አክለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ቃል አቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት፣ ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉን አሳታፊና አካታች እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በሂደቱ ሁሉም አካላት በሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል የሚል፣ በተለያዩ ምክንያቶች ወደኋላ የሚቀር ወገን እንዳይኖር ጊዜ በመስጠት በሩን ክፍት በማድረግ እንዲሳተፉ እያደረገ ነው፡፡ እስከአሁን ባለው ሂደትም ለቀረበው የምክክር ጥሪ ከህዝብ በጎ ምላሽ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

“በምክክር እንደሀገር ያሉ የአለመግባባት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን በጋራ በመለየትና በመመካከር ሀገርን ማሻገር ይቻላል በሚለው ላይ እምነት ከማሳደር ይጀምራል” የሚሉት ቃል አቀባዩ፤ ምክክር አዋጪው መንገድ ነው የሚለው እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መጥቷል፡፡ ለዚህም ኮሚሽኑ በሚያመቻቸው የምክክር መድረኮች ላይ ተሳታፊዎች ሲንከባለሉ ለመጡና አሁናዊ ችግሮች መነሻ ምክንያቶች ናቸው የሚሏቸውን አጀንዳዎች ያለምንም ስጋት በነፃነት ሲሰጡ እየታየ ነው፡፡ የተለያዩ ፍላጎቶችና አመለካከቶች፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የፀጥታ ችግርና ሌሎች ፈታኝ ሁኔታዎች ቢኖሩ እነዚህን በመሻገር በሂደቱ እምነት በመያዝ በቁርጠኝነት አሉ የሚባሉ ችግሮችን እያነሱ ይገኛሉ፡፡

ምክክር በባህሪው ሙሉ ፈቃደኝነትና ትብብርን የሚጠይቅ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን፣ ህዝብን የሚወክሉ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በሂደቱ ላይ እምነት እየጣሉ መምጣታቸው ለምክክሩ ስኬት ወሳኝነት አለው፡፡ ከዚህ ባሻገር ለምክክሩ ስኬታማነት ምክክር ምን ይፈልጋል? የሚለውንም መረዳት ወሳኝ እንደሆነ የኮሚሽኑ ቃል አቀባይ ያነሳሉ፡፡

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የሀሳብ ልዩነት፣ አለመግባባት፣ ግጭት አልፎ ተርፎ የህይወት መጥፋት በሚያጋጥምበት ወቅት ሰላምና እርቅ የሚወርድባቸው የቆዩ ባህልና እሴቶች አሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ባህሎች ጎልብተው ለሀገር በሚጠቅም መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ባለመደረጉ፣ የሀሳብ ልዩነቶችና አለመግባባቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከመፍታት ይልቅ እልህ መጋባት፣ ግጭትንና ጦርነትን አማራጭ በማድረግ ሀገር ዋጋ ስትከፍል ቆይታለች፡፡

ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ልንተዋቸው የሚገቡ በጎ ያልሆኑ ልማዶች አሉ፡፡ ከእነዚህ አንዱ አለመደማመጥ እንደሆነ አቶ ጥበቡ ያነሳሉ፡፡ ብዙ ጊዜ በፖለቲካው መድረክ ከመደማመጥ ይልቅ መናገር፣ ሀሳብን በሀይል ሌላው ላይ ለመጫን የመፈለግ ጉዳይ ይታያል፡፡ ይህ ባህል ሊቀረፍ የሚገባውና ከምክክር ጋር አብሮ የማይሄድ ጠባይ ነው፡፡

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባዬ ኦጋቶ (ዶ/ር) የፌዴራል ተቋማት አጀንዳ የማሰባሰብ መክፈቻ ስነ ስርዓት ወቅት የተናገሩት ንግግርም ይህንን ያጠናክራል፡፡ “ለረጅም ዘመን ፖለቲካችን የሚናገር እንጂ የሚያዳምጥ አልነበረም፡፡ በምክክር ሂደት ፖለቲካችን የተለያዩ ህዝቦችን ፍላጎቶች፣ ብዝሃነቶችን የሚያዳምጥ ይሆናል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል” ነው ያሉት፡፡

አለመከባበር ሌላው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሚታይ በጎ ያልሆነ ባህል እንደሆነ አቶ ጥበቡ ያነሳሉ፡፡ ተከባብሮ መነጋገር ካልተቻለ ትርጉም ወዳለው መግባባት መምጣት ያስቸግራል። አንዱን ዝቅ ሌላውን ከፍ ማድረግ፣ ‘እኔ የተሻልኩ ነኝ’፤ ‘እበልጣለሁ’ አይነት አካሄድ፤ አንዱን ጉዳይ በሌላው ጫማ ውስጥ ሆኖ ያለመመልከት፣ ሆደ ሰፊ ሆኖ ነገሮችን ያለማየት በፖለቲካው ዘንድ ይታያል፡፡ በአብዛኛው የብቻ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት እንጂ ሁሉም አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበትን መካከለኛ መንገድ ይዞ የመሄድ ነገር አይታይም። እነዚህ ልማዶችና ጠባዮች ከምክክር ጋር የሚሄዱ ባለመሆኑ፤ ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበትን ምክክርና ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርጉ መንገዶችን ማየት እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

## ቀጣይስ ምን ይጠበቃል?

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ይፋ ያደረገው መረጃ እንደሚያሳየው፣ እስከ አሁን ከ11 ክልሎች እና ከሁለት ከተማ አስተዳደሮች በድምሩ ከ1 ሺህ 234 ወረዳች ወኪሎች ተለይተው አጀንዳ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም 126 ሺህ 22 የወረዳ ተወካዮች በሂደቱ ተሳትፈዋል። ቀጣይ ከትግራይ ክልልና ዳያስፖራው ማህበረሰብ የአጀንዳ ማሰባሰብ ስራዎች ይቀራሉ፡፡

በሀገራችን ታሪክ በሀገሩ ዕጣ ፈንታ ህብረተሰቡ ብዙም ተሳትፎ ሲያደርግ አይስተዋልም፡፡ በምክክሩ ሂደት ህብረተሰቡ የሚሳተፍበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር አካታች የሆነ ምክክር እንዲሆን ሰፊ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ምሁራንና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በንቃት እየተሳተፉ ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች በምክክሩ ሂደት የማይሳተፉ የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ነፍጥ ያነገቡና ሌሎችም አካላት ወደ ምክክሩ እንዲመጡ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ የኮሚሽኑ ቃል አቀባይ ጠቁመዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በምክክሩ ሂደት የአጀንዳ ማሰባሰቡን ለማጠናቀቅ የተወሰኑ ስራዎች ይቀራሉ። የአጀንዳ ማሰባሰቡ ከተጠናቀቀ በኋላም አጀንዳዎች ተቀርፀው ሀገር አቀፍ የምክክር ጉባኤ ይካሄዳል፡፡ እየተንከባለሉ የመጡ ችግሮችን በአንድ ጊዜ መፍታት አይቻልም፤ መሰረታዊ የሆኑ የአለመግባባት ምክንያት የሆኑ ችግሮች ከተፈቱ ሌሎችም በሂደት እየተፈቱ ይሄዳሉ፡፡ ቀጣይ ትውልድም እየፈታቸው የሚሄድበት እድል እንደሚፈጠርም አቶ ጥበቡ ጠቁመዋል።

ሼህ አብዱልመናን እንደሚሉት፣ “ሀገር ተመካከሩ!” እያለች የምታቀርበውን ጥሪም ህዝቡ በአግባቡ ተረድቶ ምክክሩ ፍሬያማ እንዲሆን፣ የሚገኘውን ግብአት ወደ ተግባር እንዲቀየር የነቃ ተሳትፎ ማድረግ አለበት፡፡ በተለያዩ የመንግስት ስርዓቶች የነበሩ ዕድሎች ነበሩ፤ አምልጠውናል፡፡ አሁን ተቋማዊ በሆነ መልኩ በመመካከር ችግሮችን ለመፍታት የመጣውን ዕድል መጠቀም ይገባል፡፡

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባዬ ኦጋቶ (ዶ/ር) በፌዴራል ደረጃ በተካሄደው የአጀንዳ ማሰባሰቢያ መድረክ በተናገሩት ሀሳብ ጹሑፋችንን እንቋጨው።

“የምክክሩ ሂደት እንዲሳካ ማድረግ የምንችለው እኛው ኢትዮጵያውያን ነን። በዚህ ሂደት ማንም ተመልካች ማንም ታዛቢ የለም፡፡ ባለቤት ነን የምንል ከሆነ ያለንን እውቀት፣ ጊዜና ጥበብ በሂደቱ ላይ ማዋል አለብን፡፡ የሚያጣሉንና የሚከፋፍሉን አካላት ወይም ቡድኖች ድምፅ የሚሰማው በጣም ትክክል ስለሆኑ አይደለም፡፡ ብዙዎቻችን (the Silent majoriry) ዝምታን ስለመረጥን ነው፡፡”

# የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት እንዴት እየተሰጠ ነው?

**በሰገነት አስማማው**

አቶ ብርሃኑ የማታው በየካ ጤና ጣቢያ ለደም ግፊት ህመም በተመላላሽ ህክምና የጤና ክትትል እያደረጉ ይገኛሉ። “ህመሙ እንዳለብኝ ሳላውቅ ድንገት ስመረመር ደም ግፊቴ ከፍ ማለቱ ተነገረኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጤና ጣቢያው ለአንድ ዓመት ያህል ክትትል እያደረግኩ እገኛለሁ፡፡ መድሐኒቴ ሲያልቅ በቀጠሮ እየመጣሁ እወስዳለሁ፡፡ ሳላቋርጥ ሰዓቴን ጠብቄ እየዋጥኩ ነው፡፡ ሀኪሞቹም ጥሩ አገልግሎት ነው እየሰጡ የሚገኙት። ምንም ችግር አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ በዚሁ ይቀጥሉ” ብለዋል ተገልጋዩ፡፡

ሌላኛው ቅኝት ባደረግንበት ማይጨው ጤና ጣቢያ ያነጋገርናቸው አቶ ዳንኤል ታደሰ በተመላላሽ ህክምና ክፍል ለአምስት ዓመታት የስኳር ህመም የጤና ክትትል አድርገዋል፡፡ “የስኳር ህመም መድሐኒት ለመውሰድ በየጊዜው በምሄድበት ጊዜ ሀኪሞቹ በጥሩ ሁኔታ ነው የሚያስተናግዱኝ፡፡ አንዳንዴ መድሐኒት የምወስድበትን ቀጠሮዬን ረስቼ ሳሳልፍ ሐኪሞቹ ደውለው ክትትል እንዳደርግና ማቋረጥ እንደሌለብኝ ይመክሩኛል” ሲሉም በአገልግሎቱ መርካታቸውን ተናግረዋል፡፡

ወጣት ትእዛዙ ተስፋዬም የዛሬ ሦስት ወር ህመም ሲሰማው ወደ ጤና ጣቢያው በመሄድ ተመርምሮ የደም ግፊቱ እንደጨመረና መድሐኒት መጀመር እንዳለበት በሐኪም ተነግሮት ጥሩ ክትትል እያደረገ እንደሚገኝ ተናግሯል፡፡

የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል በየካና በማይጨው ጤና ጣቢያዎች የተመላላሽ ህክምና ክትትል ለሚያደርጉ የህብረተሰብ ክፍሎች እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ምን ይመስላል? ሲል የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች አነጋግሯል።

የየካ ጤና ጣቢያ ምክትል ሜዲካል ዳይሬክተር ዶ/ር መርሻ አስፋው በማብራሪያቸው፤ በጤና ጣቢያው የተለያዩ የውስጥ ደዌ፣ የድንገተኛ፣ የእናቶችና ህጻናት፣ የቅድመ ወሊድ፣ የድህረ ወሊድና ሌሎችም የጤና አገልግሎቶች በሲስተም እየተሰጡ ይገኛል፡፡ በተመላላሽ ህክምና ላይም በቀጠሮ እና አዲስ ታምመው ለሚመጡ አገልግሎቱ ይሰጣል፡፡ ለአብነት፣ የስኳር በሽታ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ)፣ የጥርስ ህመም፣ የቆዳና ሌሎችም ህክምናዎች አገልግሎት በስፔሻሊስት ሀኪሞች ጭምር እየተሰጠ ነው ብለዋል፡፡

በተመላላሽ ህክምና ላይ በተለይ የደም ግፊት፣ የስኳር፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ የቲቢ ታካሚዎች በሀኪም ቀጠሮ መሰረት እየመጡ አገልግሎቱ ሳይቋረጥ እየተሰጣቸው እንደሆነ ነው ዶ/ር መርሻ የሚያስረዱት፡፡ በሚሰጠው ቀጠሮ በወር ወይም በሶስት ወር እንደ ህመሙ አይነት ታካሚዎች መድሐኒታቸውን ሳያቋርጡ እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡ ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልግ ከሆነም ላቦራቶሪ ታዝዞ ውጤቱን ይዘው በቀጠሯቸው መሰረት ሀኪም ጋር ይቀርባሉ፡፡ ታካሚዎች መድሐኒቱን እየወሰዱ ባለበት ወቅት ተጓዳኝ በሽታ ቢያጋጥማቸውም ተጨማሪ ህክምና እንደሚደረግላቸው ዶ/ር መርሻ አስረድተዋል፡፡



ፎቶ በመባፅዮን ሀ/ገብርኤል

በየካ ጤና ጣቢያ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ሲሰጥ

ከዚህ ባለፈ ታካሚዎች በቀጠሮ ቀን ካልመጡ መድሐኒት እንዳያቋርጡ ሲስተም ላይ ክትትል የሚደረግበት አሰራር በመኖሩ ሀኪሞች እየደወሉ መጥተው መድሐኒት እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆነውም በተለይ የደም ግፊት፣ የስኳር፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የቲቢ ህመሞች ለረዥም ጊዜ መድሐኒት ሳይቋረጥ ክትትል የሚደረግባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም አንዳንድ ታካሚዎች በቀጠሮ ዕለት ረስተው ሳይመጡ ከቀሩ ወይም ወደ ሌላ ሀገር ሄደው ከሆነ የህክምና ክትትሉ መቋረጥ ስለሌለበት በአካባቢያቸው ባለው ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ ወይም ፋርማሲ መድሐኒቱን እንዲጠቀሙ እንደሚደረግም አክለዋል፡፡

በተመላላሽ ህክምና ላይ ታካሚዎች የሚወስዱትን መድሐኒት ማቋረጥ እንደሌለባቸው እና ቢያቋርጡ የሚያስከትልባቸውን ጉዳት በነርሶችና በፋርማሲ ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣቸዋል። በዚህም ቀድሞ ያቋርጡ የነበሩ አሁን ከጤና ጣቢያው ርቀው ቢሄዱም እንኳን በአካባቢያቸው ባለ የጤና ተቋም ክትትሉን የማድረግ ሁኔታ መፈጠሩን ምክትል ሜዲካል ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

በጤና ጣቢያው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ 1 ሺህ 700፣ የደም ግፊት 1 ሺህ 518፣ የስኳር 780 እንዲሁም የቲቢ 78 ሰዎች የህክምና ክትትል እያደረጉ ይገኛሉ። በተመላላሽ ህክምና የሚሰጠው አገልግሎት በተገቢው ሁኔታ የሚቀጥል መሆኑን የሚጠቁሙት ምክትል ሜዲካል ዳይሬክተሩ የህክምና ክትትል የሚያደርጉ ታካሚዎች ሀኪም በሚያዘው መሰረት መድሐኒታቸውን ሳያቋርጡ በአግባቡ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይ ደም ግፊትና ስኳር ህመሞች በአመጋገብ ችግር የሚመጡ በመሆናቸው ጨው፣ ስኳርና ቅባት በመቀነስ አመጋገብን በማስተካከል፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ ራስን ከበሽታ መጠበቅ እንደሚገባ ሙያዊ ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

የማይጨው ጤና ጣቢያ ሜዲካል ዳይሬክተር የሆኑት ጤና መኮንን ብርቱካን መኮንን በሰጡት መረጃ፤ ህብረተሰቡ የተመላላሽ ህክምና ላይ በተለይ የማይቋረጡ መድሐኒቶች ስኳር፣ የደም ግፊትና ሌሎችም ላይ መድሐኒቱን ሳያቋርጡ በአግባቡ መውሰድ ላይ ክፍተት ነበር፡፡ በየሶስት ወሩ ህብረተሰቡ ድረስ በመውረድ በተሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እየተሻሻለ መጥቷል። በጤና ጣቢያው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ 256፣ የደም ግፊት 662፣ የስኳር 193 እንዲሁም የቲቢ 28 ሰዎች በተመላላሽ ህክምና ክትትል እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በተመላላሽ ህክምና ታካሚው በቀጠሮው ካልተገኘ በጤናው ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ቀላል የማይባል

ወደ ገጽ 27 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

### የመንገድ መብራትን መግጨት የካሳ ክፍያ እንዳለው ያውቃሉ?

አዲስ አበባ ቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊትም የሚሰራባት፣ ዘመናዊና ስማርት ከተማ ለማድረግ እየተሰሩ ከሚገኙ መሰረተ ልማቶች መካከል የመንገድ ዳር መብራቶች ይጠቀሳሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን የመንገድ ዳር መብራቶችን ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው በመንገድ ዳር የሚተከሉ የመብራት መሰረተ ልማቶች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የሚከፈል የካሳ ክፍያን ለመወሰን መመሪያ ቁጥር 165/2017 በማውጣት ወደ ስራ አስገብቷል፡፡

**በዚህም መሰረት፡-**

⇨ **በመብራት መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው፡-**

- ጉዳት ያደረሰበትን መሰረተ ልማት ወቅታዊ ዋጋ 100 እጅ ይከፍላል፡፡
- ጉዳት የደረሰበትን መሠረተ ልማት መልሶ ለመትከል ወይም ለመጠገን የሚያስፈልገውን ሙሉ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡
- በመብራት መሠረተ ልማት ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው የተቀመጠውን ካሳ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ጉዳዩ በፍትሐ ብሔር ክርክር እንዲደረግበት ለፍትሕ ቢሮ ይላካል፡፡
- ጉዳት አድራሾች የካሳ ክፍያውን በአንድ ጊዜ ለመክፈል አቅም የሌላቸው ከሆነ ይህንን የሚገልፅ ማስረጃ በአምስት ቀን ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለባቸው።

**ምንጭ፡-** በመንገድ ዳር የሚተከሉ የመብራት መሰረተ ልማቶች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የሚከፈል የካሳ ክፍያን ለመደንገግ ከወጣው መመሪያ ቁጥር 165/2017 የተወሰደ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የውል ህግ

## ክፍል ሁለት

በናርዶስ ወርቁ (ዐቃቤ ህግ)

ባለፈው እትማችን በየውል ህግ ርዕስ ስር ምንነቱን እና የውል ህግ አመሰራረት በተመለከተ በዝርዝር አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ በዚህ እትም ቀሪውን ክፍል አዘጋጅተንላችኋል፡፡



### 1.1.3. የፍቃድ ጉድለት

ውል የተዋዋዮቹ የፍቃድ ጉድለት (Defect in consent) ካለው ሊፈርስ ይችላል፡፡ ይህም የፍቃድ ጉድለት በዋነኝነት በሶስት መንገዶች ሊከሰት ይችላል ይህም ከተዋዋዮቹ የአንደኛው ፍቃድ የተገኘው በስህተት፣ በድንገተኛ ተንኮል ወይንም በሀይል ሲሆን ነው፡፡ የፍቃድ ጉድለቱ በስህተት ነው የተገኘው ለማለት ስህተቱ የተፈፀመው በውሉ ፍሬ ነገር ወይንም በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ማንነት ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ በመውሰዱ ምክንያት ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው በስህተት ምክንያት ውሉን ለማፍረስ የሚችለው ወይንም በውሉ ላይ የተቀመጡትን ግዴታዎች አለመፈፀም የሚችለው ስህተቱ ሁለት ነገሮችን ማሟላት ሲችል ነው፡፡

እነዚህም በመጀመሪያ በፍትሐብሔር ህግ አንቀፅ 1698 መሰረት ስህተቱ ለውሉ አስፈላጊ በሆነ አቋም ላይ የተፈፀመ ሲሆን ነው፡፡ ይህ ስህተቱ የተፈፀመው በውሉ ፍሬ ነገር በተለይም በተዋዋይ ወገኖች ዘንድ አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ (በሙብትና ግዴታቸው) ላይ ሊሆን ይችላል ወይንም በተዋዋይ ወገኖች ማንነት ላይ የተፈፀመ ሲሆን ነው፡፡ እንበልና ተዋዋይ ወገኖች የኪራይ ውል ለማድረግ ፈልገው ነገር ግን የፈፀሙት የግዢ ውል ቢሆን ይህ ለውሉ አስፈላጊ በሆነ አቋም ላይ የተፈፀመ ስህተት ነው ሊባል ይችላል፡፡ ሁለተኛው ስህተቱ በፍትሐብሔር ህግ አንቀፅ 1697 በተቀመጠው መሰረት ተሳሳትኩ የሚለው አካል ዕውነቱን ቢያውቅ ኖሮ ፈቅዶ ሊሰራ የማይችለው ስህተት መሆኑን ማስረዳት ሲችል ነው፡፡ ይህ ማለት አንድ ምክንያታዊ ሰው እያወቀ ሊገባበት የማይችለው ውል መሆኑን ማስረዳት ሲችል ነው ማለት ነው፡፡

በተንኮል የተገኘ ፈቃድ ስንል ደግሞ ሆን ተብሎ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን በውሉ ፍሬ ነገር ወይንም በተዋዋዩ ማንነት ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲወስድ ማድረግ ነው፡፡ ውሉ እዲፈርስለት የሚጠይቀው አካል ታድያ ይህ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ ውሉን እንደማይፈፅም መግለፅ አለበት፡፡ እንዲሁም ይህ ተንኮል የደረሰው ከተዋዋዮቹ ውጪ በሆነ በሌላ ወገን ከሆነ ውሉን ለማፍረስ የሚቻለው ሌላኛው ተዋዋይ ወገን የሚያውቅ ከነበረ ፤ሊያውቅ ይገባ ከነበረ ወይንም ጥቅም የሚያገኝበት ከሆነ ነው፡፡ በመገደድ የተደረገ ውልን በተመለከተ አንድ ሰው ውል እንዲፈፅም አካላዊ ወይንም ስነልቦናዊ ጫና ሊደርስበት ይችላል፡፡

በመገደድ የተገኘ ውል ልንለው የምንችለው እና ይህም በሆነ ጊዜ ማገናዘብ ያለብን ሁኔታዎችን በተመለከተ የፍትሐብሔር ህጉ በአንቀጽ 1706 ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል ውል እንዲፈፀም ያስገደደው አካል ከተዋዋዮቹ ውጪ በሆነ በሌላ ወገን ቢሆንም እንኳን ተገዶ ውሉን የፈፀመው አካል ውል እንዲፈርስለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን የሀይል ስራውን አለማወቁ ወይንም ሊያውቅ ይገባ ነበር ባይባልም እንኳን ውሉን ለማፍረስ ይቻላል ነገር ግን በዚህ ምክንያት ለሚደርስበት ኪሳራ ውሉን የሚያፈርሰውን ሰው መጠየቅ ይችላል፡፡

### 2. የውል ውጤት

ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንደ ህግ ያገለግላል፡፡ ይህም ማለት ተዋዋይ ወገኖቹ በውላቸው ላይ ባስቀመጡት ወይም ባለባቸው ግዴታ መሰረት ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ ይህን ሳያደርጉ ቢቀሩ ግን ተጠያቂነት ያስከትልባቸዋል ማለት ነው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት በውል የገቡትን ግዴታ ላይወጡ ወይም ሊጥሱ ይችላሉ። በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1771 ስር የውል ግዴታ የተጣሰበት ሰው የሚከተሉት አማራጮች እንዳሉት ተደንግጓል፡፡

1. እንደውሉ እንዲፈጸምለት መጠየቅ
2. ውሉን ማፍረስ እና
3. እንደውሉ ባለመፈጸሙ ምክንያት የደረሰበትን ኪሳራ መጠየቅ

ባለሙብቱእንደውሉአልተፈጸመልኝም ብሎ ለመጠየቅ መጀመሪያ በውሉ መሰረት ያለበትን ግዴታ እንዲወጣ ባለዕዳውን በማስጠንቀቂያ መጠየቅ ይገባዋል፡፡

### 3. ውል ማፍረስና ውል መሰረዝ

የውል ማፍረስ ከውል አመሰራረት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ሲሆን፤ ውሉ ከአመሰራረቱ በህጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለማሟላቱ ግድፈት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የውል መሰረዝ ጉዳይ ከውል አመሰራረት ችግር የሚነሳ ሳይሆን ከተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታውን ካለመወጣት የሚመነጭ ነው፡፡

አንድ ውል ችሎታ በሌለው ሰው ከተደረገ ወይንም ውሉ የተፈፀመው ጉድለት ባለበት ፍቃድ ከሆነ ውሉ የሚፈርሰው ችሎታ የለኝም ወይንም ፍቃዴ ላይ ጉድለት አለበት የሚለው ወገን እንዲፈርስለት ጥያቄ ሲያቀርብ ነው። ይህ ጥያቄ እስከሚቀርብ ድረስ ውሉ የፀና ነው። እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች ቢስማሙ ውሉን ከመፍረስ ሊያድኑት ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል የውሉ ችግር ያለው በውሉ ፍሬ ነገር ወይንም ፎርም ላይ ከሆነ ግን ውሉ ከጅምሩም ፍርስ ነው ወይንም ከጅምሩም እንዳልተደረገ ይቆጠራል፡፡ ከዚህም ባሻገር ውሉን ወደ ፍርድ ቤት አንደኛው ተዋዋይ ወገን ወይንም ጥቅም አለኝ የሚል ማንኛውም ሰው ሊያቀርበው ይችላል ማለት ነው(ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1706) ፡፡

### 3.1 ውል ማፍረስ

#### 3.1.1 ፍርስ ውል (void contract)

ውሉ ከጅምሩ ፍርስ ነው ወይንም void contract ነው የምንለው ከላይ በተገለፀው መሰረት ግድፈቱ ያለው በውሉ ፍሬ ነገር ወይንም በውሉ ፎርም ላይ ሲሆን ነው፡፡ ለምሳሌ በህጉ ላይ በጽሑፍ እንዲያደርጉ በግልጽ የተቀመጡ የውል አይነቶች ውስጥ አንድ ሰው በቃል ቢዋዋል በህጉ ፊት እንዳልተደረገ ነው የሚቆጠረው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው በህጉ የተከለከለ ነገር ለማድረግ ወይንም ለመከወን ፈፅሞ የማይቻል ነገርም ቢዋዋል ይህም በተመሳሳይ ፍርስ ውል ወይንም ውጤት አልባ ነው የሚሆነው፡፡

#### 3.1.2 የሚፈርስ ውል (voidable contract)

ይህ አይነቱ ውል ደግሞ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ እስካልቀረበበት ድረስ ውሉ ፀንቶ ነው የሚቆየው፡፡ ይህም ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ መቅረብ የሚችለው ችሎታ የለኝም ወይንም ፍቃዴ ላይ ጉድለት አለበት በሚለው አካል ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው ውል ፈፅሞ ቢገኝ እራሱ ወይንም ሞግዚቱ ውል እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ውሉ እንደፀና ይቆያል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ውሉ የሚፈርስበት አካል በቅን ልቦና ተዋውሎ ከነበረ ለሚደርስበት ኪሳራ ካሳ መጠየቅ ይችላል፡፡

ውድ አንባቢዎቻችን ቀጣዩን ክፍል በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን፡፡


ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
ቴሌብር
telebirr
ዒድ
ሙባረክ!
እንኳን ለዒድ አል–አድሃ (አረፋ)
በዓል በሰላም አደረሳችሁ
በፍቅር፣ በደስታ እና በአብሮነት የምታከብሩት መልካም የዒድ አል-አድሃ (አረፋ) በዓል እንዲሆንላችሁ ከልብ እንመኛለን።


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን
ለመላው የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች እንኳን ለ1446ኛው የኢድ- አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ በዓሉ የሰላም፣ የጤና እና የብልፅግና እንዲሆን መልካም ምኞቱን ይገልፃል።
ባለስልጣኑ ከተማችን የጀመረችውን 'ስማርት ሲቲን' እውን የማድረግ ሁለንተናዊ ጥረት ውስጥ የአዳዲስ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶችን ያካተተውን የስማርት ፖል ግንባታ እና የነባሩን የመብራት መሰረተ-ልማት ጥገና በማከናወን ከተማችን የቀን ብቻ ሳትሆን የምሽትም ለማድረግ ከህብረተሰቡና ከከተማ አስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ላይ እንገኛለን።
የመብራት መሰረተ-ልማቱ ባለቤት ህብረተሰቡ በመሆኑ፤ ከጉዳት ከመከላከልና ከመጠበቅ አኳያ የጋራ ኃላፊነታችንን እንወጣ ሲል መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።
መልካም በዓል
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ
CLEANSING MANAGMENT AGENCY
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ለመላው የእስልምና ዕምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለኢድ አል አደሃ (አረፋ) በዓል በሰላም እና በጤና አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ሲገልፅላችሁ በታላቅ ደስታ ነው።

ኤጀንሲው ከተማዋን ጽዱ፣ ውብ፣ ለነዋሪዎቿ ምቹ ከማድረግ ጎን ለጎን ወርሃ ክረምቱን ምክንያት አድርጎ ሊከሰት የሚችለውን የጎርፍ አደጋ አስቀድሞ ለመከላከል ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል።
ህብረተሰቡ ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ እንዲቀንስ፣ እንዲለይ በአግባቡ እንዲይዝ በማድረግ መልሶ ጥቅምና ውደት ላይ እንዲውል ሌት ተቀን እየሰራ ያለ ማዘጋጃ ቤታዊ የመንግስት ተቋም ነው፡፡

በመሆኑም በዓሉን ምክንያት በማድረግ የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻና የእርድ ተረፈ ምርት በአግባቡ እንድንይዝና ክረምቱን ምክንያት በማድረግ "ደረቅ ቆሻሻ የሃብት ምንጭ እንጂ የጎርፍ መንስኤ ሊሆን አይገባም" በሚል መሪ ሀሳብ የተጀመረውን የፍሳሽ ማስተላለፊያና የወንዝ ዳርቻዎችን መሠረት ያደረገ የፅዳት ንቅናቄ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንድንሆን ጥሪውን ያስተላልፋል።

በከተማዋ ፅዳት ዙሪያ የሚከሰት ህገ ወጥነትን በጋራ እንከላከል!
ለጥቆማ በነጻ የስልክ መስመር 6199 በመደወል ኃላፊነትዎን ይወጡ!!

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
**የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ**

**መልካም በዓል**



የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት**

ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል!!

ክቡራን ደንበኞቻችን በዓሉን ስታከብሩ የኃይል አጠቃቀማችሁን ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት ብታደርጉ በአጭር ጊዜ የምትፈልጉትን ነገር ለመስራት የሚያስችላችሁን በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት ትችላላችሁ፤ ጊዜያችሁን፣ ገንዘባችሁን ትቆጥባላችሁ፤ የኃይል መቆራረጥንና የኃይል ብክነትን ለመቀነስም የራሳችሁን አስተዋፅዖ ታበረክታላችሁ!!

ውድ ደንበኞቻችን ብልሹ አሰራር ለሚከተሉ ግለሰቦችና ደላሎች ተባባሪ አይሁኑ! ህገ-ወጥ አሰራር ካስተዋሉ ጥቆማዎን በአዲሱ ቅሬታ ማቅረቢያ መተግበሪያ (https://eeuethics.et)፣ በ905/904 ጥሪ ማዕከል በማሳወቅ ኃላፊነትዎን እንዲወጡ እንጠይቃለን!!
በዚህ አጋጣሚ ከፍተኛ የሀገር ሃብት የፈሰሰባቸውን የኤሌክትሪክ መሰረተ-ልማቶች ከስርቆትና ከውድመት በመጠበቅ የበኩልዎን አስተዋፆኦ እንዲወጡ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን!

**በድጋሚ መልካም የኢድ አል አድሃ አረፋ በዓል!**
**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት**



## ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል-አድሃ (አረፋ) በዓል በሠላም አደረሳችሁ!

በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 39 መሰረት ከከተማው ፍርድ ቤቶች መካከል አንደኛው የሆነው የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ለከተማው ነዋሪ ተደራሽና ቀልጣፋ የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት በነዋሪው ላይ ሊደርስ የሚችለውን የሀብት እና የጊዜ ብክነት ማስቀረት ፍርድ ቤቶቹ የተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቶቹ ግምታቸው ከ5,000 ሺህ ብር ያልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን እንዲሁም ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከአንቀጽ 815 እስከ 862 ውስጥ የሚገኙ 22 የደንብ መተላለፎች መሠረት የሚቀርቡላቸውን አቤቱታዎች ተመልክተው ውሳኔ በመስጠት የዳኝነት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የደንብ ጥሰትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አዲስ በወጡት ደንብ ቁጥር 150/2015 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 167/2016 መሰረት የሚቀርቡለትን ጉዳዮችን አከራክሮ በመወሰን የዳኝነት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በዓሉ የሠላም፣ የጤና እና የብልጽግና እንዲሆንላቹ ይመኛል፡፡

## ኢድ-ሙባረክ!!

**የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ገ/እግዝአብሄር ገ/ማሪያም**

Addis Ababa City Administration Building Permit and Control Authority

## ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ2017 ዓ.ም ለኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

በሀገራችን እና በመዲናችን ለምትኖሩ ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ2017 ዓ.ም ለኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያልን፤ በዓሉ የሠላም፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብ፣ የአንድነት፣ እንዲሁም እጅ ለእጅ ተያይዘን ከተማችንን የምናበለጽግበት እና የምናዘምንበት እንዲሆንልን እንመኛለን፡፡

ውድ የከተማችን ነዋሪዎች የዘንድሮውን በዓል ልዩ የሚያደርገዉ የነዋሪዉን ፍላጎት ባማከለ መልኩ እየተከናወኑ ያሉበት ወቅት ላይ መከበሩ ነው፡፡ ውብ፣ ፅዱና ለነዋሪው ምቹ ከተማ ለማድረግ በሚደረገዉ ርብርብ አስደማሚ ለውጦች እየመጡ ነው፡፡ እንደ ተቋም ደግሞ በከተማችን ለሚሰሩ ግንባታዎች ፈቃድ የመስጠት፤ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የመስጠት፤ በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሰረት በሚገነቡ ግንባታዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ፤ ህንፃዎች ለተፈቀዱለት አላማ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የመጠቀሚያ ፈቃድ የመስጠት፤ በከተማችን የሚሰሩ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች የግንባታ ቅንጅት፣ ፈቃድና ክትትል ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች እንዲሁም የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድና ቁጥጥር አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ከማዕከል እስከ ወረዳ የሚሰሩ ስራዎችን በቀጣይም አጠናክረን የበለጠ የምናገለግላችሁ መሆኑን ስንገልጽላችሁ በዓሉ የሰላም፤ የፍቅርና የደስታ እንዲሆንላችሁ በመመኘት ጭምር ነው፡፡

**አድራሻ:=>**

22 ለም ሆቴል አካባቢ በሚገኘው የማዕከል ቢሯችን እንዲሁም በሁሉም ክ/ከተሞችና ወረዳዎች በተቀመጠው እርከን መሠረት አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ:: ስልክ 0118120078

## መልካም የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል!
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

# የአረፋ በዓል እሴት

- **በአብሮነት እና በማካፈል የሚደምቀው በዓል**

**በይግለጡ ጓዴ**

ዒድ አል አድሃ (አረፋ) በዓለም ዙሪያ በእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ ነው፡፡ በዓሉ የእርድ ወይም የመስዋዕትነት በዓል በመባልም ይታወቃል፡፡ ነብዩ ኢብራሂም ከረጅም ጊዜ በኋላ በአሏህ ፈቃድ ወንድ ልጅ ተቸራቸው፡፡ ልጃቸው ኢስማኤል ለአባቱ ታዛዥ እንደነበርም የኃይማኖቱ አስተምህሮ ያስረዳል፡፡

ይሁን እንጅ ነብዩ ኢብራሂም በደስታቸው ማግስት የእምነታቸው ጽናት የሚፈተንበት ወቅት ተፈጠረ። አንድያ ልጃቸውን መስዋዕት ያደርጉ ዘንድ ከፈጣሪ ታዘዙ፡፡ የልጃቸው ፍቅር ቢያስጨንቃቸውም ትዕዛዙ የፈጣሪያቸው ነውና ሊፈጽሙ ወደ አረፋ ተራራ ወጡ፡፡

ነብዩ ኢብራሂም ልጃቸውን ሊሰው ሲዘጋጁ ከሰማይ በኢስማኤል ምትክ መስዋዕት የሚሆን በግ ወረደላቸው፡፡ ይህንን ኃይማኖታዊ አስተምህሮ መነሻ በማድረግ በዓሉም ኢድ አል አድሃ (አረፋ) እየተባለ በየዓመቱ በድምቀት ይከበራል፡፡

ኡስታዝ መሀመድ ፈረጅ በአዲስ አበባ አየር ጤና አካባቢ በሚገኘው የአንሷር መስጅድ አስተማሪ ናቸው፡፡ ኡስታዙ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ላይ ኃይማኖታዊ ትምህርት በመስጠት እና ሃሳባቸውን በመሰንዘር ይታወቃሉ፡፡



ፎቶ በገነት ወንድሙ

አየር ጤና አካባቢ በሚገኘው የአንሷር መስጅድ አስተማሪ ኡስታዝ መሀመድ ፈረጅ

> **በችግር ምክንያት ማረድ ላልቻሉ ማከፋፈል ይገባል። አንድ አባወራ ካረደ ለሙሉ ቤተሰብ እንዳረደ ይቆጠርለታል**

እንደ ኡስታዝ መሀመድ ፈረጅ ገለጻ የዒድ አል አድሃ በዓል ነብዩ ኢብራሒም ልጃቸውን ኢስማኤልን በአረፋ ተራራ ላይ በአላህ ትዕዛዝ ሊሠውት የነበረበት ቀን ለማስታወስ የሚከበር በዓል ነው ይላሉ። ኡድህያ ወይም እርድ ግዴታ የሆነበት አንደኛው መልዕክትም ወደ አላህ መቃረብ ነው፡፡

ተከታዮቹ ለእሱ ታዛዥ እንዲሆኑ የተለያዩ ትዛዛት ይሰጣል፡፡ ይህም አንዱ ኡድህያ ማዘዙ ነው ብለዋል፡፡ ይህም እረዱ ብሎ ያዘዘው የዙልሂጃ ወር 10ኛው ቀን ላይ ነው ይላሉ፡፡ ይህም በተለምዶ በሀገራችን አረፋ በዓል የሚባለው ነው። ትክክለኛ ስሙም ዒድ አል አድሃ ነው ይላሉ፡፡ የእርድ፣ የመስዋዕትነት በዓል እንደሚባልም ኡስታዝ መሀመድ ይናገራሉ፡፡

እንደ ኡዝታዝ መሀመድ ገለጻ የዒድ አል-አድሃ ታሪካዊ ዳራ ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸውን ለአላህ ለመስዋዕት ያደረጉት ቁርጠኝነት የተሞላበት ውሳኔ እና ለመስዋዕትነት የቀረበው ልጅ ያሳየው የተለየ ጽናት ነው፡፡ ነቢዩ ኢብራሂም የበኩር ልጃቸው የሆነውን ኢስማኤልን ያገኙት በእርጅና ዘመናቸው ነው። ሚስታቸው ሳራ ለፍሬ ባለመብቃቷ አላህ ያለ ዘር አታስቀረኝ፤ እኔን የሚተካ ልጅ ስጠኝ በማለት ዱዓ አደረጉ፡፡ በዚሁ መሰረት በሳራ ፈቃደኝነት ሐጀራ የምትባለውን የቤት ሰራተኛቸውን አገቡ።

ሐጀራም ኢስማኤል የተባለ ልጃቸውን ወለደችላቸው፡፡ ይህ ልጅ በአላህ ፈቃድ በመካ ከተማ እንዲያድግ የተወሰነ ስለነበረ ኢብራሂም ሐጀራን እና ኢስማኢልን ወደ ዐረቢያ ከተማ ወሰዷቸው፡፡ በጣም የሚወዱት ልጃቸው ኢስማኤል ካደገ በኋላ ደግሞ አላህ ልጅህን እንድትሰዋ ታዘሃል የሚል በህልማቸው አሳያቸው፡፡ የነቢያት ህልም ደግሞ ከራዕይ የሚቆጠር ነው፡፡

ስለዚህ ኢብራሂም በህልማቸው ያዩትን በዝምታ አላለፉትም፡፡ በወቅቱ የሆነውን ቅዱስ ቁርአን እንዲህ ይተርካል፡፡ "ከርሱ ጋር ለስራ በደረሰ ጊዜም ልጄ ሆይ! እኔ በህልሜ የማርድህ ሆኜ አይቻለሁ፤ እስቲ አንተም ነገሩን ተመልከት፡፡ ምን ይታይሃል አለው። ልጁም አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ፈጽም፤ አላህ ቢሻ እኔን ከታጋሾቹ ሆኜ ታገኘኛለህ አለው፡፡ የፈጣሪን ትዕዛዝ በትዕግስት ነው የምቀበለው፤ ለዛውም አንተ ታዝዘህ እቀበለዋለሁ አለው፡፡"

አባትና ልጅ በዚህ መንገድ ከአላህ የተላለፈውን ትዕዛዝ ሊፈጽሙ ተነሱ፤ ነቢዩ ኢብራሂም ልጃቸውን እንዲሰው የታዘዙት ከዐረፋት መሬት ብዙም ባልራቀ ቦታ ላይ ስለነበረ ወደዚያው ጉዞ ጀመሩ፡፡

ኢብራሂም ኢስማኤልን ሊያርዱት አጋደሙት፡፡ ልጁም ምንም ሳያንገራግር ከመሬቱ ላይ ተኛ፡፡ ኢብራሂም ልጁን ሊያርዱት ሲሞክሩ ግን ቢላዋው አላርድ አላቸው፡፡ ኢብራሂም እንደገና ቢላዋውን ገዘገዙት፡፡ ነገር ግን ቢላዋው ፈጽሞ ዶለዶመ፡፡ ቢላዋው አልቆርጥ አለ፡፡

ልጁ የሆነው ነገር አልገባውም። አባቱ ቶሎ ስላላረደው ተገረመና አባዬ "ምናልባት የአባትነት ፍቅር ይዞህ ይሆናል በቶሎ ያላረድከኝ፤ እስቲ ዐይኔን በጨርቅ ሸፍነውና እርዱን ሞክር የሚል አስተያየት ሰጠ፡፡ "በዚህን ጊዜ ግን ከወደ ሰማይ ጥሪ መጣ፡፡ የአላህ መልአክ ኢብራሂም ታላቅነትህን አስመስክረሃልና፤ የአላህን ፍቅር ተግብረሃል፤ የታዘዝከውን ትዕዛዝ ፈጽመሃልና እርዱን አቆየው" በማለት አወጀ፡፡

በምትኩም ጅብሪል ከገነት ያመጣውን ሙክት በግ እንዲያርድና ልጁን ወደቤቱ እንዲወስደው ነገረው፡፡ በዚህም መሰረት ሙክት በጉ ታረደ፡፡ ኢብራሂምና ኢስማኤል ወደ መካ ከተማ ተመለሱ፡፡ ሁለቱ ሰዎች ለፈጣሪ መታዘዝን በግልጽ ያሳዩባት ያቺ ዕለት የዒድ አል-አድሃ በዓል ሆና እንድትከበርም ተወሰነ። ኢስማኤል ለመስዋዕትነት የቀረበበት ድርጊት ደግሞ በዚሁ ዕለት የሚታረደው "ኡድሒያ" መነሻ ሆነ በማለት ኡስታዝ መሀመድ ያብራራሉ፡፡ በሂጅራ አቆጣጠር የመጨረሻው ወር ዙል ሂጃህ በ10ኛ ቀን የኢድ ሶላት ከተሰገደ ጀምሮ እስከ 13ኛው ቀን ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ እርድ ማረድ ይቻላል ብለዋል፡፡

ዒድ አል-አድሃ የመስዋዕትነትና የመዳን በዓል ነው፡፡ የሐጅ ጸሎት የሚፈጽም ሰው በዚህ ዕለት ኡድሒያ የማረድ ግዴታ አለበት ይላሉ ኡስታዝ መሀመድ፡፡ ይህ የሚታረደው እርድ መስፈርቱ ጠንካራ ነው የሚሉት ኡስታዝ መሀመድ የሚታረደው በግ፣ ፍየል፣ ከብት አይኑ ሸወርዋራ ያልሆነ፣ አይኑ ያልጠፋ፣ ጆሮው ያልተቆረጠ፣ ቀንዱ ያልተሰበረ፣ እግሩ አንካሳ ያልሆነ፣ በሽተኛ ያልሆነ፣ ያልከሳ መሆን ይኖርበታል፡፡

በችግር ምክንያት ማረድ ላልቻሉ በማረድ ማከፋፈል ይገባል፡፡ አንድ አባወራ ካረደ ለሙሉ ቤተሰብ እንዳረደ ይቆጠርለታል፡፡ በእርድ ወደ አላህ መቃረብ ነው የሚሉት ኡዝታዝ መሀመድ አባወራው ካረደ ልጅ፣ ሚስት እና እሱ የሚያስተዳድራቸው ቤተሰብ በሙሉ ወደ አላህ በዚህ እርድ ተቃርበዋል ማለት ነው ይላሉ፡፡ ቤተሰብን የምታስተዳድረዋ ሴት ከሆነች በእሷ ገንዘብ ተገዝቶ እርዱ ከቀረበ እሷም ምንዳውን ታገኛለች በማለት ያስረዳሉ፡፡ እርድ የሚፈጽሙ ሁሉ ምንዳውን ያገኛሉ ብለዋል፡፡

ይህን እርድ የሚያርደው ሰው ዙልሂጃወር ከገባበት ቀን ጀምሮ ጸጉሩን፣ ጥፍሩን አይቆረጥም፡፡ እርዱን ካረደ በኃላ ነው ጸጉሩን፣ ጥፍሩን የሚቆረጠው ይላሉ፡፡ ይህም ቢላዋውን ይዞ እርድ የሚፈጽመው ሰው ሳይሆን በዋናነት ለእርዱ ወጪ ያወጣውን ለማለት መሆኑን ኡስታዝ መሀመድ ይገልጻሉ፡፡

የቻለ ሁሉ ማረድ እንዳለበት ኃይማኖታዊ አስተምህሮው ያስረዳል። ያልቻለ ሰው ግን ነብዩ አርዶለታል። አንድ ሰው ሁለትና ከዚያ በላይ ማረድ ይጠበቅበታል፣ በማለት ብዙ የእርድ መስዋዕት ባቀረበ ቁጥር ምንዳ ሃጂር እየበዛ ይሄዳል ብለዋል፡፡ በሀገራችን ብዙ ማረድ እምብዛም ባይለመድም በቱርክ ሀገር የሚገኙ ሙስሊሞች ግን ብዙ እርድ እንደሚፈጽሙ ኡስታዝ መሀመድ ይናገራሉ፡፡

እንደ ኡስታዝ መሀመድ ገለጻ ታዲያ ኡድሒያው፣ ኡድሒያ ተብሎ የሚመዘገብልን እርዱም ሆነ አጠቃቀሙ ነቢዩ ያስተማሩትን መንገድ የተከተለ ከሆነ ብቻ ነው ብለዋል፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ፍየሉን ያርዱና ለበዓል የሚሆናቸውን ያህል ካስቀሩለት በኋላ ሌላውን ወደ ፍሪጅ ውስጥ ይከቱታል። ይህ ግን ራስን መጋበዝ ነው እንጂ ኡድሒያ ተብሎ አይመዘገብም፡፡

ነቢዩ እንዳስተማሩት ለኡድሒያ ከታረደው ስጋ አንድ ሶስተኛው በቀጥታ ለድሆች መከፋፈል አለበት። የቀረው ብቻ ነው ለቤተሰብ አገልግሎት የሚውለው፡፡ ስለዚህ በዚህ እለት የሚፈጸመው መስዋዕት ኡድሒያ ሆኖ እንዲመዘገብልን ካሻን ያላቸው ለሌላቸው በመስጠት ትክክለኛውን የአስተምህሮ መንገድ መከተል አለብን ይላሉ ኡስታዝ መሀመድ፡፡

# የመዲናችን ኪነ- ጥበባዊ ዝግጅቶች

በአብርሃም ገብሬ

ባለፉት ቀናት በመዲናችን የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል ዝግጅቶች የተሰናዱ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል የስዕል ዓውደ ርዕይ፣ የመጽሐፍት ውይይቶችና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል መርሃ ግብሮቹን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

ዛሬ ቅዳሜ በደራሲ ልዑል ዮሐንስ በተጻፈው “ከሰሜን ሰማይ ስር” የተሰኘው የድርሰት ሥራ ዙሪያ ውይይት ይደረጋል። መጽሐፉ የኢትዮጵያዊ ማንነት መገለጫ የሆኑ ቅርሶች፣ በተለይም በእምነት ተቋማትና በባህል ልማት ማዕከላት ያሉ የቅርስ እሴቶች አጠባበቅና የቅርስ ጠባቂዎች እያደረጉት ያለው ትልቅ አስተዋጽኦ የሚተነትን ነው ተብሏል። ደራሲው በቱሪዝም እና ቅርስ ልማት የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ ማሳተማቸው ተገልጿል፡፡ የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሥነ ጥበባት ማዕከል ውስጥ በሚደረገው በዚህ ውይይት፣ በነጻ እንዲገኙ የጥበብ አፍቃሪያንና የመጽሐፍ አንባብያን ተጋብዘዋል፡፡

ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠና ደራሲ አበረ አዳሙ በመጽሐፉ ዙሪያ ሂስ የሚያቀርቡ ሲሆን፣ የሙዚቃ ባለሙያው ሰርፀ ፍሬስብሃት ደግሞ ውይይቱን ይመራል ተብሏል፡፡ የውይይት መርሃ-ግብሩ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ የሚደረግ ሲሆን፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል አካባቢ (ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጉለሌ ቅርንጫፍ በኩል ገባ ብሎ) በሚገኘው፣ የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሥነ ጥበባት ማዕከል ውስጥ ይደረጋል፡፡

በሌላ መረጃ፣ “ቅርስ እና ሥነ ጥበብ” በሚል ርዕስ ሙያዊ ገለጻ እና ውይይት ይደረጋል፡፡ ዛሬ ቅዳሜ ከሰዓት በጣይቱ የባህልና የትምህርት ማዕከል ከ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ዕውቁ የሥነ-ሰብዕ ተመራማሪ ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት እና የአለ ሥነ ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሰዓሊ አገኘሁ አዳነ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ሙያዊ ገለጻ እና ውይይት የሚያደርጉ ሲሆን የጥበብ አፍቃሪያንም እንዲታደሙ ተጋብዘዋል፡፡ ቦታው ፒያሳ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ከእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ህንጻ ጎን ይገኛል፡፡

ነገ እሁድ ደግሞ “የትይዩ ዓለም ዲበ- አካላዊነት ሃልዮት” በሚል ርዕስ ፍልስፍናዊ የሃሳብ ውይይት ይደረጋል። መምህር ዮሴፍ ይድነቃቸው በቅርቡ ለንባብ ሊያበቃው ባሰናዳው መጽሐፍ ላይ በመመስረት የውይይቱ መነሻ ሃሳብ እንደሚቀርብም ታውቋል፡፡ የውይይት ፕሮግራሙ የተሰናዳው በኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አዳራሽ (ወመዘክር) ውስጥ ከ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ እንደሚካሄድ ታውቋል፡፡

## ሥነ- ጥበብ

“ከሞቃት ጥላ ሥር” የተሰኘ የሰዓሊ ንጋቱ ሰለሞን የሥዕል አውደ ርዕይ በይፋ መታየት ጀመረ፡፡ ባሳለፍነው ሳምንት ረቡዕ ግንቦት 27 ቀን 2017 ዓ.ም ሀያት ሬጀንሲ ሆቴል ውስጥ በሚገኘው በፈንድቃ የባሕል ማዕከል የተከፈተው ይህ ዓውደ ርዕይ፣ የሰዓሊው ልዩ ልዩ የጥበብ ሥራዎች የቀረቡበት ነው። ዓውደ ርዕዩ እስከ ፊታችን ሰኔ 11 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ለተመልካች ክፍት ሆኖ ይቆያል ተብሏል፡፡

በሌላ መረጃ፣ “ጣይቱ” የተሰኘ ከ24 በላይ የታዋቂ አንጋፋና ወጣት ሰዓሊያን የተሳተፉበት የሥነ ጥበብ ትርኢት የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ማዘጋጃ ቤት በነበረውና በአሁኑ የጣይቱ የባህልና ትምህርት ማዕከል ውስጥ ሲታይ ቆይቷል፡፡ ዛሬ ቅዳሜ የመጨረሻው ቀን ሲሆን፤ እስካሁን ድረስ የስዕል ዓውደ ርዕዩን ያልተመለከቱ የጥበብ አፍቃሪያን መጥተው እንዲመለከቱ ተጋብዘዋል፡፡ በዚህ ዓውደ ርዕይ ላይ ከስዕል በተጨማሪ ልዩና ደረጃቸውን የጠበቁ ኪነ ቅርጾችም መቅረባቸው ታውቋል፡፡ ይኸ አጋጣሚ እንደ አዲስ የታደሰውን ታሪካዊ ቅርስ ቤቱን ለመጎብኘት እድል የሚሰጥ ነው። የሥዕል አውደ ርዕዩ እየታየ ያለው፣ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ከእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ጎን ነው፡፡

በሌላ መረጃ “የተሸመኑ ትውስታዎች” የሥዕል ዓውደ ርዕይ በመታየት ላይ ነው። በወጣቱ ሠዓሊ ብርሃኑ ማናዬ የተዘጋጁ ሥዕሎች የቀረቡበት ይህ ዓውደ ርዕይ ባለፈው ግንቦት 2 ቀን 2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፖስት ዋና መስሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው “The Space Ethiopia” የሥዕል ማሳያ ውስጥ ለእይታ በቅቷል። በዳግም አበበ አጋፋሪነት የተዘጋጀው ይህ ዓውደ ርዕይ የተለያዩ የስዕል አቀራረቦችን እንዲሁም በተለያዩ የአሳሳል ዘይቤ የተሰሩ የስዕል አይነቶችን ያካተተ እንደሆነ ተገልጿል። ዓውደ ርዕዩ እስከ ሰኔ 18 ቀን 2017 ዓ.ም በእይታ ላይ ይቆያል ተብሏል።




ፎቶ- ከገፀ ድር

በመዲናዋ ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የቴአትር መርሃ ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ ከሚታዩ ቴአትሮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ ቅዳሜ 8:00 ሰዓት ባሎች እና ሚስቶች፣ 11፡30 ሰዓት ደግሞ ባቡሩ የተሰኙ ቴአትሮች በብሔራዊ ቴአትር ቤት ይታያሉ፡፡ በዚሁ ቴአትር ቤት እሁድ በ8፡00 ሰዓት 12ቱ እንግዶች፤ 11፡30 ሰዓት ደግሞ እምዬ ብረቷ ቴአትሮች ለተመልካች ይቀርባሉ፡፡ እንዲሁም በቀጣይ ቀናት ማክሰኞ በ11፡30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረቡዕ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ፣ ሐሙስ ቀን 11:30 ሰዓት ሽምጋይ፣ አርብ በ11፡30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ ቴአትሮች እንዲሁም ረቡዕ በ12:00 ሰዓት “ከትዳር በላይ” ተውኔት በብሔራዊ ቴአትር፣ “ጥቁር እንግዳ” ተውኔት ሀሙስ በ12፡00 ሰዓት በዓለም ሲኒማ ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በመጀመሪያ ጎንና ጎን ያሉ ሁለት ቁጥሮችን እናባዛለን፤ ከዚያ በኋላ ከላይ ባለው ቁጥር የታችኛውን ቁጥር እንቀንሳለን፡፡ አባዝተንና ቀንሰን ያገኘናቸውን ቁጥሮች እንደገና በማባዛት የመሀሉ ቁጥር መምጣት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ሰንጠረዥ ላይ ያለውን መልስ አሰራር አብረን እንስራ፡፡ 7 X 6 = 42 እንዲሁም 3 – 2 = 1 ይሆናል፤ 42 X 1= የመሃሉ 42 ይመጣል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ 8 X 2 = 16 ከዚያ በኋላ 14 – 11 = 3 ይሆናል፡፡ አባዝተንና ቀንሰን ያገኘነውን ውጤት እንደገና እናባዛለን፤ በዚህም 16 X 3 = **48** ትክክለኛው የጥያቄው መልስ ይሆናል፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የመታዘዝ ከፍታ - በመንዙማና ነሺዳ

**በጊዜው አማረ**

ትዕዛዝ በብዙ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ዋነኛ ጭብጡ ግን አንድና ግልጽ ነው። ትርጉሙም እነዚህ ነገሮች ይፈቀዳሉ። እነዚህ ነገሮች አይፈቀዱም ማለት ነው። የሚፈቀዱትን ነገሮች ማድረግ፣ የማይፈቀዱ ነገሮችን ደግሞ አለማድረግ ትዕዛዝን ወይም ህግን ማክበር ማለት ይሆናል፡፡ ትዕዛዙ ደግሞ በኃይማኖት፣ በቤተሰብ፣ በሀገር ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ትዕዛዝ ለማህበረሰቡ ለማስተማር ደግሞ ህግ፣ ትምህርት፣ ጥበብ እና ሌሎች ነገሮች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም የዒድ አል አድሃ (አረፋ) በዓልን ምክንያት በማድረግ መታዘዝን እና ጠቀሜታውን የሚያወሱ የመንዙማ እና ነሺዳ ስራዎችን በተመለከተ አጭር ዳሰሳ አድርጓል፡፡

ወጣት አሚር መሐመድ ይባላል። የመንዙማና ነሺዳ ባለሙያ ነው። ስራዎቹን በዲጂታል ሚዲያዎች ላይ በማጋራትም ታዋቂነት እያተረፈ መጥቷል፡፡ ስራዎቹም ሀገርኛ ቅኝት ያላቸው መንዙማዎች እና ነሺዳዎች ናቸው፡፡ አሚር “ነቢ ውዴ” በሚለው ስራው ይበልጥ ይታወቃል፡፡

ወጣቱ መታዘዝ ማለት የፈጣሪን ትዕዛዝ ማክበር ነው፡፡ የፈጣሪን ድንጋጌ፣ የቁራንና ሃዲስን ህጎች በትዕዛዙ መሰረት መተግበር ነው፡፡ በተለያየ መልኩ በውስጣችን ያለውን የፈጣሪ ትዕዛዝ በነፍስም፣ በአካላዊ ስጋችንም መፈጸም ነው ይላል፡፡

የፈጣሪን ህጎች ለአማኞች ለማስተማር ደግሞ መንዙማና ነሺዳ ትልቅ አበርክቶ አላቸው፡፡ የመንዙማና ነሺዳ ባለሙያው አሚር መሐመድ እንደሚለው፣ መንዙማና ነሺዳ የእስልምና እምነት ተከታዮች ስለ ኃይማኖት ህግ፣ ስርዓት፣ መከባበር፣ በእምነት ጸንቶ መቆም እና ትዕዛዝን መፈጸም ስለሚያስገኘው በረከት ለማስተማር ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። እርሱም “ነቢ ውዴ” በተሰኘ የነሺዳ ስራው፡-

ቢዘገይም የጀሊል ፍርዱ
እግሬ አይሰንፍ ለመራመዱ
ትርፉ ናፍቆት ነው ሰው ከወደዱ

ፍቅር ገበያው ይሄው ነው ንግዱ... በማለት በእምነት መጽናትን እና ተስፋ ማድረግን፣ ፍቅርን ፈጣሪ ለሰው ልጅ ያሰበው የሚሆንበትን ቀን በትዕግስት መጠበቅ እንደሚገባ ያስተምራል፡፡

ወጣት አሚር እንደሚለው የመንዙማና ነሺዳ ጥቅሞች በኪታብ ላይ የተጻፉ ነገሮችን ወይም የተለያዩ መጽሐፍት ላይ የተጻፉ ህጎችን፣ ትልልቅ ታሪኮችን ጠቅለል ባለ ሃሳብና በልቦና በሚቀረጽ መልኩ ማስረዳት፣ ማስገንዘብ እና ማስተማር ነው። በነሺዳ እና መንዙማ ትልቅ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ለአብነትም ትዕዛዝ በሚል ርዕስ አንድ ነሺዳ ቢሰራ የሚንጸባረቀው መልዕክት የፈጣሪን ትዕዛዝ መወጣትን፣ የቤተሰብን ሃቅ ማክበርን፣ በህይወት እያሉ የእናትና አባትን አደራ መወጣትን ሊሆን ይችላል።

ሳይነጥቀን መጥቶ አጅሬው ሞት




ፎቶ ከገፀ ድር
አሚር መሐመድና ጓደኞቹ በነሺዳ ስራ ላይ

በቶሎ አድርሱኝ ከሃቢብ ቤት
እየባረከ በማዕዱ እየጠራ
ጽልመት እያራቀ ሌሊቱን እያበራ
አንዴ እያስደሰተ እምባም እያዘራ
ህርምና ዘልቆ አለማቱን ሞላ

እንደ ፍቅር መች ይገኛል መላ... የሚለው በራሱ ስራ ውስጥ የተካተቱት ስንኞች ለፈጣሪ ትዕዛዛት መገዛትን፣ በጽናት መቆምን፣ ከጎረቤት ጋር መረዳዳትን፣ ስለ ይቅርባይነቱ፣ ዓለምን ስለሞላው ምህረቱ ማመንና መረዳትን ያሳያል፡፡

ከዚህ አንጻር መንዙማ እና ነሺዳ መታዘዝን እና ጠቀሜታውን በማስተማርና በቀላል መንገድ በማስገንዘብ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ለምሳሌ “ጎረቤቱ ተርቦ እርሱ ጠግቦ ያደረ እንደሆን ከእኛ አይደለም” ብለዋል ነብዩ መሐመ። ይህም ከእስልምና ኃይማኖት ትዕዛዛት ውስጥ አንዱ ነው። ይህን የተገበረ የፈጣሪውን ትዕዛዝ ያከብራል በረከትም ያገኛል፡፡ ይህንን ትዕዛዝ ማክበርን የሚያስተምሩ፣ ትዕዛዛቱን ማክበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ የሚያንጸባርቁ የነሺዳና የመንዙማ ስራዎች በሀገራችን በብዛት ተሰርተዋል፡፡ ከታዋቂው መሀመድ አወል ሳላህ የነሺዳ ስራዎች ውስጥ “የጎረቤት ሀቅ” በሚል ርዕስ ከተሰራው ስራ ጥቂት ስንኞችን እንቀንጭብ፡፡

የህይወት ተጋሪ ነው ጥሩ ጎረቤት
ለየትም ለምስኪን ለቅርቡ ጎረቤት
እርዱ መልካም አርጉ ሁሌም ድረሱለት

በዘር ባንገናኝ በእምነት ቢለያይ
ቁራኑ ያዘናል ሁሉን እኩል ልናይ
የመጨረሻዋን ቀን አማኝ የአላህ ሰው
ጎረቤቱን ያክብር ይርዳ በተቻለው...፡፡

ይህ የነሺዳ ስራ የእምነቱን ተከታዮች ከራሳቸው አልፈው ጎረቤቶቻቸውን እንዲያግዙ፣ ለሌሎች ሰዎች መልካም እንዲሆኑ ያዝዛል፡፡ ይህን የማያደርግ ግን ትዕዛዙን እንደ ህልም የሚረሳ ነው። ይህ ደግሞ በፍጹም መሆን የሌለበት ተግባር ነው፡፡ ለዚያም ነው ታዋቂው ሙነሽድ፡

ከበደል አልነጻሁ ራሴን ስመረምር

ትዕዛዙን ሳልፈጽም ምንም ለማልፈጠር

ግቢዬን አጽድቼ አቆሸሽኩት ደጁን
ሰላምታ ነፈኩት ዘርግቶልኝ እጁን
የአላህ የእጁን ስራ እድፉን ተጸይፌ
ራሴን አመጻደኩ ሽቶ ተርከፍክፌ
የጎረቤትን ሃቅ ሳታግበሰብሱ

እንደታዘዘው ይሁን በቁራን በሃዲሱ.... በማለት የእስልምና አስተምህሮት ትዕዛዝ ማክበርን፣ መረዳዳትንና አላህ ያዘዘውን፣ የእምነቱ ተከታዮችም ያደርጉት ዘንድ የሚወደው እንደሆነ በተመጠኑ ቃላትና በተጨመቀ ጥልቅ ሃሳብ አስገንዝቧል፡፡

ሌላኛው የመንዙማና ነሺዳ ባለሙያ አብዱልከሪም ጀማል ከዚህ ቀደም ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው ሃሳብ ላይ መንዙማ በባህሪው በጣም ውስን በሆኑ ቃላትና በዜማ ታጅቦ የሚቀርብ ጥበባዊ ስራ ስለሆነ ምዕመኑን በቀላሉ ስለ ዕምነቱ አስተምህሮ ለመረዳት ያስችለዋል፡፡ ነብዩ መሐመድ የከለከሏቸው ድርጊቶችና ምዕመኑ ሊተገብራቸው የሚገቡ መርሆች አሉ፡፡ እነዚህን እስላማዊ ህጎች በመንዙማ አማካይነት እንዲያውቃቸው ሥራዎቹ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። የተከለከሉ እንዲሁም መፈጸም አለባቸው ተብለው በነብዩ የተደነገጉ ህጎች ኃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆኑ ሥነ ምግባራዊና የመልካም ስብዕና ባለቤት እንድንሆን መንገድ የሚያመላክቱ ናቸው በማለት አስረድቷል፡፡

ትኩረቱን መንዙማና ነሺዳ ላይ ያደረገው የሚናራ ፕሮዳክሽን መስራችና ባለቤት ወጣት ሰዒድ መሃመድ እንደሚገልጸው መንዙማ የአላህን ችሎታና ሊቅነት ለመግለጽ ያገለግላል። ነብዩ መሐመድ ታሪክ ከውልደት እስከ ኑሮና ያለፉበት የሚገለጽበት መንገድ ነው፡፡ ለእርሳቸውም ምስጋና የሚቀርብበት ነው፡፡ ነብዩ መሐመድ እንዴት ኖሩ፣ እንዴት አለፉ የሚለውም የሚንጸባረቅበት፣ ትዕዛዛቸውን በተመለከተ ለአማኙ ትምህርት የሚሰጥበት ነው፡፡ እዚህ ጋር እንደማሳያ የኢሳም አህመድን “ሙባረካ” የተሰኘ መንዙማ መጥቀስ እንችላለን፡፡

ውልደት እድገቱ ያማረ አምሮ የፈካ
እኔን የሚወዱ ይከተሉህ አለ ጀሊሉ
ጸባይ ምግባሩ ሙሉ፣ የለው የሚተካ
ሰለላህ አይለካ

ኑረል ሃዲ ያሙባረካ...፡፡

በተጨማሪም መንዙማ በራሱ ማህበራዊ ህይወትን ይዳስሳል። ከጎረቤትና ማህበረሰቡ ጋር መኖር ስለሚገባው ትስስር፣ መረዳዳትና መተጋገዝ ያስተምራል፡፡ መቻቻልና አብሮነቱን ያስገነዝባል፡፡ በህይወታችን መስራት ያሉብንንና የሌሉብንን ነገሮች ያስረዳል፡፡ ስለሞት ያስታውሳል፡፡ የነብዩ መሐመድ ስብዕናና ስነ-ምግባር፣ ማህበራዊ ትስስር በግጥምና በዜማ ተገልጾ ሰዎች በቀላሉ እንዲረዱት ያግዛሉ፡፡ በዚህም መንዙማ ከመቻቻል፣ ከአብሮነት፣ ከይቅርታ ከስነ ምግባር አንጻር ከፍተኛ አበርክቶ አለው ሲልም ሰኢድ ያብራራል፡፡

አሚር መሐመድ ደግሞ መንዙማና ነሺዳ ከኃይማኖትም ያለፈ ፋይዳ አላቸው፡፡ ትልልቅ የሀገር ባለውለታዎችን ለማስታወስ ይረዳሉ፡፡ የሀገር ፍቅርንም ይገልጻሉ፡፡ ኃይማኖቱን በደንብ የሚያከብር ቤተሰቡን፣ ሀገሩን ያከብራል የሚል መልዕክት በመንዙማና ነሺዳ ይተላለፋል ይላል፡፡ ሁሉም ኃይማኖት የሚያዝዙት ደግሞ መከባበርን፣ አብሮነትን፣ መወዳድን፣ ፍቅርንና መረዳዳትን ነው፡፡ ይህን በማንጸባረቅ ረገድ ደግሞ የመንዙማና ነሺዳ ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው በማለት ያስረዳል፡፡

ወጣቱ ሙነሺድ እና የመንዙማ ባለሙያ አሚር መንዙማና ነሽዳን በሚገባ ተጠቅመንባቸዋል ብዬ አላምንም፡፡ ሀገራችን ብዙ ጸጋዎች አሏት፡፡ ለምሳሌ፡- በክርስትና እምነት የያሬድ ዜማ ሀገራዊ እሴትን የሚገልጽና የኢትዮጵያ ኩራት እንደሆነው ሁሉ በእስልምናም መንዙማ ሀገራዊ ቅኝትና የኢትዮጵያ መልክ ነው። ሌላ ሀገር ላይ አይሰማም፡፡ ቅኝቱ የትም ሀገር የለም፡፡ በእኛ ሀገር ነው የሚገኘው። ስለዚህ በብዙ መልኩ ድጋፍ ቢደረግ ሀገራችን ከመንዙማ ብዙ ነገሮችን መጠቀም ትችላለች፡፡ ሀገርኛ እንደመሆኑ መጠን የሀገራችንን ገጽታ ለማስተዋወቅ ይጠቅማል ሲል ሃሳቡን አንስቷል፡፡

በእርግጥ የድሮ ሙነሽዶች እና በመንዙማ ባለሙያዎች የእምነትን፣ የእናትና አባቶች ትዕዛዛትን ስለመፈጸም፣ የሀገርን ህግ ስለማክበር፣ ሀገርን ስለመውደድ፣ ስለመከባበርና መተጋገዝ ብዙ አስተምረውበታል የሚለው ወጣቱ ባለሙያ አሚር መሐመድ፣ ነገር ግን መንዙማና ነሽዳ ማደግ ያለባቸውን ያህል አላደጉም፡፡ በብዛት ያደጉት የአረብ ወይም የሱዳን ቅኝት ያላቸው መንዙማዎች ናቸው፡፡ በተለይ ኢትዮጵያዊ መንዙማ በደንብ ቢሰራበት የሀገራችንን ማንነት በደንብ ሊያሳይ የሚችል፣ ግብረገብ ትውልድም ለመገንባት የራሱን ድርሻ የሚወጣ ነው ሲል በማጠቃለያ ሃሳቡ ላይ አስገንዝቧል፡፡

# ልጆች፤ መታዘዝ ስለሚያስገኘው ጥቅም ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በለይላ መሐመድ**

ልጆች በቅድሚያ እንኳን ለ1446ኛው ዓመተ ሂጅራ የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል አደረሳችሁ፡፡ ልጆች በዓሉ ሲታሰብ በግንባር ቀደምትነት የሚመጣው የነቢዩ ኢብራሂምና የልጃቸው ነብዩ እስማኤል እንዲሁም የእስማኤል እናት ሐጀራ ናቸው፡፡

ልጆች ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ነቢዩ ኢብራሂም በአመሻሽ እድሜያቸው ባለቤታቸው ሳራ ልጅ መውለድ ባለመቻሏ "ያ አላህ ያለ ዘር አታስቀረኝ፤ እኔን የሚተካ መልካም የሆነ ልጅ ስጠኝ" በማለት ዱዓ (ፀሎት) አደረጉ፡፡

ኢብራሂምም በሳራ መልካም ፈቃደኝነት ሐጀራ የምትባለውን አገልጋያቸውን አግብተው እስማኤልን ወለደችላቸው። እስማኤል ካደገ በኋላ አላህ፤ "ልጅህን እንድትሰዋ ታዝሃል" የሚል በህልማቸው አሳያቸው፡፡ ኢብራሂምም፤ "ልጄ ሆይ! እኔ በህልሜ እንዳርድህ ከአላህ ታዝዣለሁ" አሉት፡፡ እስማኤልም፤ "አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ፈጽም" የሚል ምላሽ ሰጣቸው፡፡ ከዚያም ኢብራሂም እስማኤልን ሊያርዱት አጋደሙት።

ልጁም ምንም ሳያንገራግር ከመሬቱ ላይ ተኛ፡፡ ኢብራሂም ልጁን ሊያርዱት ሲሞክሩ በምትኩ ከጀነት የመጣ በግ ወረደላቸው፡፡

የኢብራሂም እና የእስማኤል ታሪክ ለልጆች ብዙ ትምህርት ሊሰጥ እንደሚችል በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት የሴቶችና ወጣቶች ዘርፍ ኃላፊ ኡዝታዛ ፋጡማ ሁሴን ይናገራሉ፡፡ "ልጆችዬ፤ ከላይ ከተጠቀሰው ታሪክ የምንማረው የመጀመሪያው ነገር የእናትና የአባትን ወይንም የልጅን ወይም የምድራዊ ፍላጎትን ብቻ ማሳካት ሳይሆን ለአላህ (ለፈጣሪያችሁ) መገዛት እንዳለባችሁ ነው፡፡ ምንም እንኳን ትዕዛዙ ለአእምሮ ከባድ ቢሆንም አባት ልጁን ለማረድ እና ልጅም ለመታረድ ፍቃደኛ መሆናቸው ለፈጣሪያቸው ታዛዥ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የተላለፈላቸው ትዕዛዝ ከአላህ (ከፈጣሪ) በመሆኑ አባት በስተርጅና የወለድኩትን ልጄን አላርድም አላሉም፤ ልጅም መታረድ የለብኝም አላለም፡፡"



ፎቶ ከገፀ ድር

መታዘዝ የሚያስገኘው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው

ሌላውና ሁለተኛው ከታሪኩ መማር የሚገባው ቁም ነገር እስማኤል የአባቱን ትእዛዝ ምንም ሳያቅማማ መቀበል መቻሉ ወይንም ለመታረድ ራሱን ማዘጋጀቱ ለአባቱ ያለውን ታዛዥነት የሚያሳይ ነው፡፡ ልጆች እናንተም የወላጆቻችሁን ትእዛዝ ተቀብላችሁ መፈጸም እንዳለባችሁ ትምህርት ልትወስዱ ይገባችኋል፡፡

ወላጆቻችሁን ብቻ ሳይሆን ታላላቅ ወንድምና እህቶቻችሁን እንዲሁም የእውቀት አባቶች የሆኑትን መምህራንና የእምነት አባቶችን ማክበርና መታዘዝ ይኖርባችኋል፡፡ ታላላቆቻችሁን ስታከብሩና ስትታዘዙ በቀጥተኛው መንገድ እንድትጓዙ ያደርጋችኋል፡፡

ለምሳሌ በእምነት ተቋማት የምትማሯቸውን ትምህርቶች በሚገባ ማዳመጥና ወደ ተግባር መለወጥ ይጠበቅባችኋል፡፡ እምነቱ ከሚከለክለው ነገር ስትከለከሉ የሚፈቅደውን ስትተገብሩ ነው ሥነ ምግባራችሁ ያማረ የሚሆነው፡፡

ስልክና ቴሌቪዢን ላይ አፍጥጣችሁ ወላጆች ሲጠሯችሁ ዝም ከማለት በፍጥነት አቤት ብላችሁ መነሳትና ለፈለጓችሁ ዓላማ መታዘዝና ማስደሰት ይኖርባችኋል፡፡ በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥም ባለመረበሽ፣ የሚሰጣችሁን የቤት ስራዎች በመስራት እና የተማራችሁትን በሚገባ በማጥናት ታዛዥ መሆናችሁን ማሳየት ይኖርባችኋል። ይህንን ማድረጋችሁ በትምህርታችሁ የተሻለ ደረጃ እንድትደርሱና የነገ ህይወታችሁ የተስተካከለና ያማረ፣ አልፎ ተርፎም ቤተሰቦቻችሁንና ሀገራችሁን የምታስጠሩና የምትጠቅሙ ዜጎች ትሆናላችሁ፤ እሺ፡፡

እስማኤል አባቱን የታዘዘው እስከ ህይወት መስዋዕትነት ነው፡፡ ትዕዛዙ ከባድ ቢመስልም ወላጅን መንቀፍ ደግሞ የባሰ ከባድ መሆኑን የተረዳው እስማኤል በመታዘዙ አተረፈ እንጂ ኪሳራ አላጋጠመውም፤ አይደል ልጆች። ይህን በማድረጉ ውጤቱ ያማረ ነበር። ስለዚህ ልጆች አሁን ላይ ዓለም የደረሰችበት ግሎባላይዜሽን ተፅዕኖው ከባድ ቢሆንባችሁም ትግል ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡

በመልካም ነገር ትዕዛዝ ስትቀበሉ በፈጣሪያችሁ ውዴታ ታገኛላችሁ። በወላጆቻችሁ ፍቅርንና ሙገሳን ታገኛላችሁ፡፡ የእምነት አባቶችንና መምህራንን ስትታዘዙ ሥነ ምግባራችሁ ያማረ ከመሆኑም በላይ የወደፊት ህይወታችሁ የተቃና ይሆናል፡፡ ልጆች ተረዳችሁ አይደል፤ መታዘዝ ብዙ ጥቅም እንዳለው፡፡ ልጆችዬ፤ ከነብዩ ኢብራሂምና ከልጃቸው ነብዩ እስማኤል ታሪክ ትምህርት ወስዳችሁ ታዛዥ ሁኑ፡፡

## 5 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**አንድ ዓይን ያላት ነገር ግን የማታይ**

**መልስ፦** ሐ. መርፌ

## የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**በጠዋት ተነስታ መሬት የምትልስ**

ሀ. መጥረጊያ

ለ. መወልወያ

ሐ. ማሽያ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**



# ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሙሉ

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ!**

እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ በማለት በዓሉ የሰላም፣ የጤና እና የብልጽግና እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቱን በመግለጽ ከይዞታ ማስለቀቅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ አቤቱታዎችን እየመረመረ በፍርድ ሂደት ውሳኔ የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡ ተልዕኳችን ቀልጣፋ ውሳኔ በመስጠት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ በመሆኑ የሁል ጊዜ ጥረታችን በትጋትና በትህትና ማገልገል ነው፡፡

**ጉባኤው መላውን ህዝበ ሙስሊም እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ )
በዓል አደረሳችሁ እያለ
በዓሉ የሰላም፣ የጤናና የብልጽግና እንዲሆንላችሁ
መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ
ሰሚ ጉባኤ ፕሬዝዳንት አቶ ዘገየ የማነብርሃን**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
## ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

**ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ)
በዓል በሰላም አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡**

ኮሚሽኑ የፍትሐዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት እንዲሰፍን፣ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ በኩል የድርሻውን በመወጣት ላይ የሚገኝ የዳኝነት ተቋም ነው፡፡

በዚህም የአገልግሎት አሰጣጣችንን በማዘመን ቀልጣፋ፣ ተገማችና ፍትሐዊ ውሳኔ በመስጠት የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ እና ፍትሐዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት እንዲሰፍን በላቀ ደረጃ በትጋት የሚሰራ ሲሆን በዓሉ የሰላም፣ የጤና እና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡



**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን
ፕሬዘዳንት አቶ ታረቀኝ አስፋው**

# የአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር



አቶ ጌታሁን አበራ
የአራዳ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ

## እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም! አደረሳችሁ

የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነውን እርስ በርስ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባህልን በማስቀጠል በተለይም ህዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ሲያከብር አቅም የሌላቸውን ወገኖች በማካፈልና በመደገፍ በዓሉን በደስታ እንዲያሳልፉ በማድረግ ለሌሎች አርአያ በመሆን በዓሉን በጋራ ማሳለፍ ይገባል።

ሀገራችን የጀመረቻቸው በርካታ የልማት ስራዎች ላይ የነበረውን አብሮነትና መረዳዳት በማስቀጠል በበዓሉ አከባበር ላይ ይህን አጉልቶ በማውጣት በዓሉን ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንድናከብር አደራ እያልኩ በድጋሜ የእንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ ይላል የአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር፡፡

## እንኳን ለኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ!



አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ምገባ ኤጀንሲ
Addis Ababa City Administration
Feeding Agency

## እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ!!

ኤጀንሲያችን ከ840 ሺህ 585 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ (ቁርስ እና ምሳ) ይመግባል።

በአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ሃሳብ አመንጪነት እና አስተባባሪነት መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም ባለሃብቶችን በማወያየትና በማነሳሳት ባለፉት 5 ዓመታት ጀምሮ በ26 ተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት ከ36 ሺህ 600 በላይ የእለት ጉርስ የሌላቸውን አቅመ ደካማ አረጋውያን፣ ጧሪ ደጋፊ የሌላቸውን አካል ጉዳተኞች፤ ለሀገር ውለታ የሰሩ እና አቅም የሌላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች እየመገበ ይገኛል።

ልጆቻቸውን በመንግስት ትምህርት ቤት ለሚያስተምሩ ከ16 ሺህ 400 በላይ መጋቢ እናቶች የስራ እድል ፈጥሯል፤ ከ1,037,500 በላይ ተማሪዎች የደንብ ልብስ እና 9,125,435 የተማሪዎች ደብተር አቅርቧል። ለ43,350 መምህራን ጋወን ተሰጥቷል። ለ16 ሺህ 400 በላይ መጋቢ እናቶች ሸርጥ ቀርቧል ።

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ
## እንኳን ለ1446ኛው የኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ!!

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ



# ስለገላን ጉራ የመኖሪያና የተቀናጀ የልማት መንደር በጥቂቱ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማዋ ለመኖሪያ ምቹ፣ የተዋበችና ፅዱ እንዲሁም ስማርት ከተማ እንድትሆን ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

ከትልልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶች ጀምሮ እስከ ጥቃቅን የውስጥ ለውስጥ መሰረተ ልማት የሚከናወኑ ልማቶች በሙሉ ሰውን ማዕከል ያደረጉ፣ የነዋሪዎችን ህይወት የሚያሻሽሉ እና የዜጎች ተጠቃሚነትን ያረጋገጡ እንዲሆኑ በትኩረት ተሰርቷል።

ለዚህ ትልቅ አብነታዊ ማሳያ ሊሆን የሚችለዉ ካዛንቺስ አካባቢ በኮሪደር ሲለማ ነዋሪዎቹም ከነበሩበት ደሳሳ ጎጆ ወጥተው ወደ ተሻለና መሰረተ ልማቶቹ በጥራት ተገንብተው ወደ ተሟሉለት አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ገላን ጉራ መኖሪያና የተቀናጀ የልማት መንደር እንዲኖሩ መደረጋቸውን ለማሳያነት መመልከት ይቻላል።

በገላን ጉራ መኖሪያና የተቀናጀ የልማት መንደር በ57 ቀን ብቻ ተገንብተዉ ክብርት ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ እና የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት ተመርቀዉ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን በወፍ በረር እናስቃኛችሁ፡፡

- እጅግ ደረጃቸዉን የጠበቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶች (ኮንደሚኒየም)
- 1 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የአስፓልት መንገድ እና ከ20 በላይ አውቶብሶችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል ተርሚናል
- 90 ምጣዶችን የያዘ፣ በ3 ፈረቃ (ሺፍት) ለ270 እናቶች የስራ እድል የሚፈጥር የእንጀራ መጋገሪያ ማዕከል
- ከ500 በላይ አረጋውያን፣ የሀገር ባለውለታዎች፣ አቅመ ደካሞች እና ስራ ዕድል ቢፈጠርላቸው እንኳን ሰርተው መግባት የማይችሉ ነዋሪዎች በቀን 1 ጊዜ የሚመገቡበት 22ኛው የገላን ጉራ ቅርንጫፍ የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል
- በሰዓት 5 ሺህ ዳቦ የማምረት አቅም ያለው፣ ወጣቶችና ሴቶች ተደራጅተዉ እየሰሩበት የሚገኝ፣ በውስጡ ለስራዉ አስፈላጊ ግብዓቶች የተሟሉለት የዳቦ መጋገሪያ ማሽን
- 4 የስራ እድል የፈጠሩ ወፍጮዎች
- ደረጃቸውን የጠበቁ ከ52 በላይ የንግድ ሱቆች እንዲሁም በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ የግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶች የሚቀርቡበት አምራች ከሸማች በቀጥታ የሚገናኝበት
- ከነማ ፋርማሲ
- ደረጃውን የጠበቀ የህፃናት መጫወቻ (outdoor play groud)፣ ወላጆች ልጆቻቸዉ ሲጫወቱ ቁጭ ብለዉ ሻይ ቡና እያሉ የሚጠብቁበት ካፌ እና መቀመጫ ስፍራ እንዲሁም መፀዳጃ የተሟላለት ዘመናዊ የህፃናት መጫወቻ ማዕከል
- ደረጃውን የጠበቀና በውስጡ የህዝብ መቀመጫ፣ አረንጓዴ ስፍራ (greenery) እና የእግረኛ መንገድ (walk way) ያለው ዘመናዊ የስፖርት ማዘውተሪያ
- ከ7 ወር በታች ያሉ 50 ህፃናትን የመያዝ አቅም ያለዉ የህጻናት መጫወቻ እና ማቆያ
- ገላን ጉራ ቁ.2 ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት G+2 ህንፃ ግንባታ 18 መማርያ ክፍሎችን የያዘና 750 ህፃናትን ማስተናገድ የሚችል የመማርያና ማረፍያ ክፍሎች ያሉት፣ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ፣ አረንጓዴ ስፍራ፣ መፀዳጃ፣ አጥርና አስፈላጊው ነገር ሁሉ የተሟላለት የመጫወቻና የልጆች መቦረቂያ
- ገላን ጉራ ቁ.2 የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤት G+4 ህንፃ ግንባታ 30 ክፍሎችን የያዘ 1 ሺህ 500 ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተናገድ የሚችል፣ መመገቢያ አዳራሽ፣ የስፖርት ሜዳ፣ መፀዳጃ፣ ዙርያ አጥር፣ አረንጓዴ ቦታ እና የተማሪዎች መጫወቻ ሰፊ ስፍራን ያካተተ
- ገላን ጉራ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት G+4፣ 30 የመማርያ ክፍሎችን የያዘ፣ 1 ሺህ 200 ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተናገድ የሚችል እንዲሁም የተማሪዎች የስፖርት ሜዳ ግንባታን በውስጡ የሚያካትት አነስተኛና ሁለገብ ስፖርት ስታዲየም፣ (የእጅ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ... በውስጡ የያዘ)

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ዲጂታሉ የመረጃ መስኮት

**በፋንታነሽ ተፈራ**

አቶ ገዛኸኝ እሸቱ በፒያሳ አካባቢ ለረዥም ዓመታት ኖረዋል፡፡ በአካባቢውም ከዚህ በፊት በመንገድ ዳር መብራት ምሰሶ ላይ የስራ፣ የአፋልጉኝ፣ የጉዞና የተለያዩ ማስታወቂያዎች ከወረቀት እስከ ባነር ይለጠፉ፣ ይሰቀሉና ይንጠለጠሉ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ እነዚህ ጉራማይሌ ሆነው የሚተላለፉት ማስታወቂያዎች አንዱን በአንዱ ላይ እየለጠፉበትና እየተደረተ አካባቢውን ለእይታ የማይመቹ ከመሆናቸው ባለፈ፣ በከተማዋ ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደነበራቸው ያስታውሳሉ፡፡

የወረቀትም ሆነ የባነር ማስታወቂያዎቹ ባለቤት አልባ ከመሆናቸው ባለፈ በወቅቱ ከቦታው ላይ ስለማይነሱ በመብራት አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማት ላይ ለመለጠፍ፣ ለመስቀልና ለማንጠልጠል በሚደረገው ጥረት የተለያዩ ጉዳቶች ይደርሱ ነበር፡፡ በተለይም በመንገድ መብራት ምሰሶዎቹ ላይ ያሉ አምፖሎችን በማርገፍና ቀለማቸውን በማሳጣት ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጡና ያለጊዜያቸው ተበላሽተው ከአገልግሎት ውጪ እንዲውሉ በማድረግ አሉታዊ ጫና አሳድረው ቆይተዋል፡፡ በዚህም በፖሎች ላይ የሚለጠፉ ህገ ወጥ ማስታወቂያዎች ከሚሰጡት አገልግሎት ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝን ነበር ሲሉ አቶ ገዛኸኝ ያነሳሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት በከተማዋ እየተሰሩ ካሉ መሰረተ ልማቶች ውስጥ የመንገድ መብራት (ስማርት ፖል) ላይ የተሰሩት የምስል ድምፅ ማሳያዎች (LED Screen) ማስታወቂያዎችን እና መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ለማሰራጨት፣ የመዝናኛ አማራጭ በመሆን እና የከተማዋንም ውበት በማላበስ ጉልህ ሚና እንዳላቸው አክለዋል፡፡

ይህንን ሀሳብ የማስታወቂያ ባለሙያዎችም ይጋሩታል፡፡ የኢሳያስ ማስታወቂያ መስራችና ባለቤት እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የሸገር ከተማ የማስታወቂያ ስራ ማህበር ፕሬዝዳንት አቶ ኢሳያስ ጋሻው እንደሚሉት የውጭ ማስታወቂያ ሲሰራጭ የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ቢኖረውም፤ ከዚህ በፊት በመብራት ፖሎችና ግንቦች ላይ ይለጠፍ የነበረው ማስታወቂያ ይህን የተከተለ አልነበረም፡፡ በፊት የነበረው የውጭ ማስታወቂያ ስርዓት ወጥነት ያልነበረውና የተዥጎረጎረ ነበር። በማንኛውም ቦታና ጊዜ ማስታወቂያ ይለጠፍና ይሰቀል ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ወጥነት ባለው መንገድ እየተሰራበትና የከተማዋንም ገፅታ በእጅጉ የለወጠ ነው።

ከዚህ በፊት የከተማዋ ውበትና ንፅህና እንደ ዛሬው ስላልተጠበቀ የውጭ ማስታወቂያ ላይ የሚወጣው ህግ ተግባራዊ አይደረግም ነበር፡፡ የከተማዋ መዘመን ግን ማህበረሰቡም “ይህ አይመጥነኝም” በማለት የተለያዩ ማስታወቂያዎችን በዘፈቀደ ከመለጠፍና ከመስቀል እንዲቆጠብ ማስቻሉን አያይዘው ነግረውናል፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም ቅኝት ባደረገባቸው የከተማዋ አንዳንድ አካባቢዎች ከዚህ በፊት በስፋት ይታዩ የነበሩ በመብራት ምሰሶ ላይ የሚለጠፉ አካባቢን የሚያቆሽሹ ማስታወቂያዎች አይታዩም፡፡ ከተማዋን በሁለንተናዊ መልኩ እየቀየሩ ያሉት የኮሪደር ልማት አብረው የዘመኑ የመንገድ መብራቶች ወይም ስማርት ፖሎች እንዲሰሩ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ እነዚህ ስማርት ፖሎቹ ደግሞ ስማርት እንዲሆኑ ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ የምስል ድምፅ ማሳያዎች (LED Screen) በላያቸው ላይ የተገጠመላቸው መሆኑ ነው፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በመንገድ መብራት ምሰሶዎች ላይ ሲለጠፉ የነበሩ ማስታወቂያዎች



ፎቶ ከገፀ ድር

በቅርብ የተሰሩ ዘመናዊ የመረጃ ማሰራጫ ስክሪኖች

> ከተማዋ የሚመጥናትን የዲጂታል የመረጃ ማስተላለፊያ መንገድ በስማርት ሲቲ ግንባታ ውስጥ አካትታ መተግበሯ፤ ማስታወቂያዎችን በየቦታው የመስቀል፣ የማንጠልጠል እንዲሁም የመለጠፍ ድርጊቶች እንዲወገዱ አስችሏል

እነዚህ ለከተማዋ ውበት፣ ድምቀት እንዲሁም ለነዋሪዎቿ በሚመች እና ለእይታ በሚማርክ መንገድ ተሰርተዋል። የምስልና ድምፅ ማሳያዎቹ በግለሰብ ወይም በድርጅት ደረጃ የማስታወቂያ አገልግሎት መስጠት ባይጀምሩም በከተማዋ ከተማ አቀፍ፣ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ሲኖሩ መልዕክቶችን ሳቢና ወጥ በሆነ መንገድ በማሰራጨት፣ የኢትዮጵያን፣ የአፍሪካንና የሌሎች ሀገራትን ብሔራዊ ሰንደቅ አላማ በዲጂታል ዘዴ በማድረስ የሀገሪቷን የልማት ስራዎችና ሌሎች የማስታወቂያ ስራዎችን ማስተላለፍ ከጀመሩ ዋል አደር ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰብስብ ሁሴን እንደሚገልፁት፣ የኮሪደር ልማቱ ለከተማዋ እድገትና መዘመን ጥሩ እድል ይዞ መጥቷል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ለሰለጠነ ማህበረሰብ የዘመነች ከተማ የሚገባው መሆኑን በመረዳት ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በእነዚህም ፕሮጀክቶች አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጋት የከተሜነት ደረጃ ላይ ለመድረስ እየገሰገሰች ትገኛለች፡፡ ከተሞችን ስማርት ከሚያሰኛቸው ቁልፍ ጉዳዮች መንገዶችና አብረው የሚገነቡት የመንገድ ዳር መብራቶች ናቸው፡፡

ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ ስማርት የመንገድ መብራት ፖሎች ተሰርተዋል። እነዚህ ፖሎች ስማርት እንዲሆኑ ካደረጓቸው ነገሮች ውስጥ የራሳቸው የሆነ የፋይበር ኬብል እና የገመድ አልባ የኢንተርኔት አገልግሎት(ዋይ ፋይ)፣ ካሜራ እንዲሁም ዲጂታል የምስልና ድምፅ ቅንብር ማሳያዎች (LED Screen) የተገጠመላቸው መሆናቸው እንደሆነ አቶ ሰብስብ ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ ስማርት ፖሎች ላይ የተገጠሙት የምስልና ድምፅ ማሳያዎች ታስቦባቸው የተሰሩና ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን አቶ ሰብስብ ይገልፃሉ። ከዚህ በፊት በነበሩ ፖሎች ላይ ማስታወቂያዎችን በወረቀት፣ በጨርቅ፣ በባነር ህትመትና በሌሎች ዘዴዎች የመለጠፍ፣ የመስቀልና የማንጠልጠል ህገ ወጥ የማስታወቂያ ስራዎችን ይሰሩ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በመሰረተ ልማቱ ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት ባለፈ፣ የከተማዋን ገፅታ ያበላሹ እና ለእይታም ምቹ አልነበሩም፡፡

በአሁኑ ወቅት ከተማዋ የሚመጥናትን የዲጂታል የመረጃ ማስተላለፊያ መንገድ በስማርት ሲቲ ግንባታ ውስጥ አካትታ መተግበሯ፤ ማስታወቂያዎችን በየቦታው የመስቀል፣ የማንጠልጠል እንዲሁም የመለጠፍ ድርጊቶች እንዲወገዱ አስችሏል፡፡ በቀጣይም እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን እየተሰራበት ያለውን በመመሪያ በማስደገፍ ስማርት እየሆነች ያለችውን ከተማ ማህበረሰቡን የሚመጥንና ስክሪኖቹ ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ ነው፡፡

እነዚህ የተዘረጉ የምስልና ድምፅ ማሳያዎች ትላልቅ ጉባኤዎች፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ሲኖሩ ለማስተዋወቅ እያገለገሉ እንደሚገኙ የገለፁልን አቶ ሰብስብ፤ ከዚህ ባለፈ ወደ ህጋዊ መስመር አስገብቶ ማስታወቂያዎችን በማስተላለፍ ገቢ ለመሰብሰብና ተደራሽነቱን ለማስፋት መመሪያዎች ተዘጋጅተው ለማፀደቅ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ መሆኑን ነግረውናል፡፡

የምስልና ድምፅ ማሳያዎቹ ህገ ወጥ የሆነ የማስታወቂያ አሰራርን ያስቀረ፣ የከተማዋን ገፅታ ያበላሸ እና ያቆሸሸ የነበረውን ችግር በሙሉ የቀረፈ እንዲሁም ከተማዋ በጀመረችው ለውጥ ልክ ለህብረተሰቡ ስማርት የመረጃ ማሰራጫ ስርዓትን በመገንባት ወጥ፣ ፈጣንና ለእይታ ማራኪ ማድረግ አስችሏል፡፡

በቀጣይም እንደ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለሥልጣን የምስልና ድምፅ ማሳያዎቹ (LED Screen) ዝርጋታዎችን በጊዜ ሂደት በሁሉም የከተማዋ አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ እቅድ በመያዝ እየተሰራ እንደሆነ አቶ ሰብስብ ጠቁመዋል፡፡

በዋናነት ከቦሌ ቪ. አይ. ፒ እስከ መስቀል አደባባይ፣ ከመስቀል አደባባይ እስከ ሜክሲኮ፣ ሳር ቤት፣ ከሜክሲኮ አደባባይ እስከ ቸርችል፣ ከቸርችል እስከ ዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ አራት ኪሎ እንዲሁም ከአራት ኪሎ እስከ መስቀል አደባባይ እንዲሁም ከፍል ውሃ እስከ ብሔራዊ ድረስ የተሰሩ መሰረተ ልማቶች ዘመናዊና ስማርት ፖሎች የተተከሉባቸው፣ በስማርት ፖሎቹ ላይ ደግሞ ሲሲቲቪ ካሜራዎች፣ ዋይፋይ እና የምስልና ድምፅ ማሳያዎች የተገጠሙላቸው ናቸው፡፡

የለሙ መሰረተ ልማቶች ላይ በተለይም ደግሞ በመንገድ መብራቶች ላይ ስርቆቶች እየደረሱ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ መሰረተ ልማቶች የማህበረሰቡ የራሱ ንብረቶች በመሆናቸው፣ ማህበረሰቡ በመጠበቅና በመንከባከብ ኃላፊነቱን እንዲወጣ አሳስበዋል፡፡

**ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ**

# የሰመረው ምኞት

**በሰገነት አስማማው**

"በምኖርበት አካባቢ የሶፍትዌር ኢንጂኒዬር የሆነ የማውቀው ሰው ነበር፡፡ እሱን በማየቴ ለቴክኖሎጂ ያለኝ ፍቅር እየጨመረ መጣ፡፡ የእሱን አርዓያ የመከተል ፍላጎትም አደረብኝ። ያለምኩትም ደርሶ በምመኘው የትምህርት መስክ እየሰለጠንኩ ነው" ይላል በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በሃርድዌር እና ኔትዎርኪንግ ሰርቪስ (Hardware and Networking Service) ትምህርት ክፍል በደረጃ አራት እየሰለጠነ የሚገኘው ወጣት ዳዊት ፋንታሁን፡፡

ወጣቱ በኮሌጁ ባገኘው እድልም ከሚያዝያ 27 እስከ ግንቦት 2 ቀን 2017 ዓ.ም "ብሩህ አዕምሮዎች፣ በክህሎት የበቁ ዜጎች" በሚል መሪ ሀሳብ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር በአዲስ አበባ ባዘጋጀው አራተኛው ሀገር አቀፍ የተግባራዊ ምርምር፣ የቴክኖሎጂ እና የክህሎት ውድድር ላይ ለመሳተፍ በቅቷል፡፡ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ በሃርድዌር እና ኔትዎርኪንግ ሰርቪስ ላይ በሚያተኩር የክህሎት ውድድር በመሳተፍ በከተማ 1ኛ በሀገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ 3ኛ በመውጣት አሸንፏል፡፡ በሁሉም የሙያ ዘርፍ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል የሰርቨር ቴክኖሎጂ በመስራት የነሐስ ሜዳሊያ፣ 300 ሺህ ብር እና የምስክር ወረቀት ለመሸለም በቅቷል፡፡

"ለዚህ እበቃለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ ደስታና ኩራት ተሰምቶኛል። የተደረገልኝ ሽልማትም የበለጠ እንድነሳሳ ያደርገኛል፡፡ ስልጠናዬን ስጨርስ በሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ የስራ መስክ ላይ የመሰማራት እቅድ አለኝ፡፡ በቴክኖሎጂው ዘርፍም የላቀ ቦታ ላይ በመድረስ ሀገሬን በዓለም መድረክ የማስጠራት ርዕይ አለኝ" ሲል ወጣቱ ይናገራል፡፡

በምወደው የትምህርት መስክ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠናውን በጥሩ ሁኔታ እየተከታተልኩ እገኛለሁ የሚለው ሰልጣኝ ዳዊት፤ ወጣቶች በሚፈልጉት ሙያ ከተማሩና በርትተው ከሰሩ ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ ይችላሉ ብሏል፡፡ ለዚህ በመብቃቱም ኮሌጁን አመስግኗል። በመጪው ሰኔ ወር ስልጠናውን አጠናቅቆ ለመመረቅ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝም ተናግሯል።

በኮሌጁ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የስልጠና ዘርፍ ተጠሪ ወይዘሮ ዘውዲቱ ፀጋዬ በሰጡት መረጃ፣ በዘርፉ ስልጠና መሰጠት የተጀመረው በ1994 ዓ.ም ነው፡፡ የተጀመረውም በአራት ዘርፎች ማለትም በሃርድዌር፣ በኔትዎርኪንግ፣ በዳታቤዝ፣ በዌብ እና መልቲሚዲያ ነበር፡፡ እነዚህ ዘርፎች ተመሳሳይነት ስላላቸው በ2014 ዓ.ም በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሰረት በሁለት መሰረታዊ የስልጠና ዘርፎች እንዲሰጡ ተደረገ፡፡ የመጀመሪያው ሃርድዌር እና ኔትዎርኪንግ ሰርቪስ (Hardware and Networking Service) ሲሆን ይህም ጥገናና ኔትዎርክ ዝርጋታ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ሁለተኛው ዌብ ዴቨሎፕመንት እና ዳታ ቤዝ አድሚኒስትሬሽን (Web Development and Database Administration) ሲሆን ገፀ ድር (ዌብሳይት) መስራትና ሲስተም ማበልፀግ እንዲሁም ማስተዳደር ላይ ያተኮረ ስልጠና ነው። በተጨማሪም ለሌሎች የስልጠና ዘርፎችም እንደ የጋራ (ኮመን ኮርስ) በመሰረታዊ ክህሎት (Basic Skill)፣ ወርድ፣ ኤክስኤል እና አክሰስ ላይ ስልጠና እየተሰጠ መሆኑን ተናግረዋል፡፡



ፎቶ፡-በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ
በክህሎት ውድድር አሸናፊ የሆነው ሰልጣኝ ዳዊት ፋንታሁን

እንደ ወይዘሮ ዘውዲቱ ገለፃ፣ ስልጠናው የሚሰጠው 30 በመቶ በንድፈ ሃሳብና 70 በመቶ በተግባር ልምምድ ነው፡፡ ሰልጣኞች በቴክኖሎጂው ዘርፍ ያላቸውን ተሰጥዖ እንዲያወጡ በዲጂታል አንላይን ይለማመዳሉ፡፡ ለአብነት በኦንላይን ፈተና እንዲፈተኑ ይደረጋል፣ የስራ ልምድ ማስረጃ (ሲቪ) ን በዲጂታል እንዲያዘጋጁ እንዲሁም ሲስተም እንዲያበለፅጉ የማለማመድ ስራ በስፋት እየተሰራ ነው፡፡ በተጨማሪም ሰልጣኞች ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ላይ የሚሰሩ ተቋማት ጋር በመሄድ የተግባር ልምምድ በማድረግ በሙያቸው በቅተው የሚወጡበት ነው።

ኮሌጁ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የስልጠና ዘርፍ ላይ ብቁ የሆኑ ሰልጣኞች የማፍራት ተግባሩ የሚቀጥል ሲሆን፤ በተጨማሪም አሰልጣኞች ባላቸው አቅም የኮሌጁን ስራ የሚያፋጥኑ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሰሩም የማበረታታት ስራ ይሠራል። ለአብነት የሥራ መልቀቂያ ወረቀት እያንዳንዱ ዘርፍ ላይ እየሄዱ ማስፈረም ጊዜን የሚፈጅ በመሆኑ ይህን የሚያስቀር ሶፍትዌር የለማ ሲሆን፤ ተግባር ላይ ለማዋል እንዲሁም ምዘናን ሙሉ በሙሉ በኦንላይን ለማድረግም እቅድ መያዙን ወ/ሮ ዘውዲቱ ጠቁመዋል፡፡

ሰልጣኞች ከትምህርት ባሻገር ያላቸውን ተሰጥዖ እንዲያወጡ፣ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህም ያገኙትን እውቀት የበለጠ እንዲያዳብሩ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች በሚዘጋጁ የክህሎት የውድድር መድረኮች ላይ በዘርፉ ፍላጎትና የተሻለ ውጤት ያላቸው ሰልጣኞች ተሳታፊ እንዲሆኑም ይደረጋል፡፡ ሰልጣኝ ዳዊት ፋንታሁንም በዚህ እድል ተጠቃሚ ከሆኑ ሰልጣኞች አንዱ ነው። በሃርድዌር እና ኔትዎርኪንግ ሰርቪስ ((Hardware and Networking Service) ተወዳድሮ በማሸነፍ ለሽልማት በቅቷል፡፡ ወጣቱ ስልጠናውን ሲያጠናቅቅ የራሱን ስራ በመፍጠር ከመስራት ባለፈ በዲጂታሉ ዓለም ብቃት ያለውና ለሀገር የሚጠቅም ስራ እንደሚሰራም ይታመናል ብለዋል፤ የዘርፉ ተጠሪ ወ/ሮ ዘውዲቱ፡፡

ያለንበት ዘመን የቴክኖሎጂ እንደመሆኑ እንደ ሰልጣኝ ዳዊት አይነት ወጣቶች ለዲጂታል ኢትዮጵያ እውን መሆን ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ወጣት ዳዊትም በቴክኖሎጂው ዘርፍ እያደረገ ያለው ትጋት ለሌሎች አርአያ መሆን የሚችል ተግባር ነው እንላለን፡፡

## ሶፍትዌርን በማበልፀግ ከታወቁ ባለብሩህ እዕምሮዎች በጥቂቱ

**በስንታየሁ ምትኩ**

በየቀኑ የምንጠቀማቸው መተግበሪያዎች፣ በስልክ ወይም በኮምፒዩተር ላይ ገፀ ድሮችን ጨምሮ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ የቴክኖሎጂ መገልገያዎች የሌሉበትን ዓለም ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ዛሬ የሰዎችን ህይወት ከቀየሩ የቴክኖሎጂ ትሩፋቶች ጀርባ ሶፍትዌሮች ይገኛሉ፡፡ ሶፍትዌር የተለያዩ ትዕዛዞች ስብስብ ሲሆን ተጠቃሚዎች ስራዎችን ለማከናወን ወይም ኮምፒዩተሮችን ለማዘዝ የሚያገለግል የፕሮግራም ዓይነት ነው፡፡

ተጠቃሚዎች አንድ ስራ ለማከናወን የሚያስችሉ መተግበሪያዎችንና ሲስተሞችን የሚፈጥሩ ባለሙያዎች የሶፍትዌር አበልፃጊዎች ይባላሉ፡፡ የሶፍትዌር አበልፃጊዎች ለገሀዱ ዓለም ፍላጎቶች ወይም ችግሮች የዲጂታል መፍትሔዎችን የሚተልሙ፣ የሚነድፉ፣ የሚያረቅቁና የሚገነቡ ናቸው፡፡ በየእለቱ ለምንጠቀማቸው ቴክኖሎጂዎች ፈጠራ መሰረት ከጣሉ ባለብሩህ አእምሮ የሶፍትዌር ባለሙያዎችና ስራዎቻቸው መካከል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

**ቢል ጌትስ፡-** ታዋቂው አሜሪካዊ ቢሊየነር ቢል ጌትስ ከጓደኛው ፖል አለን ጋር በመሆን፣ ለግል ኮምፒዩተሮች አገልግሎት የሚውሉ ሶፍትዌሮችን የሚያመርተው ማይክሮሶፍት የተሰኘ በዓለማችን ግዙፍ የቴክኖሎጂ ኩባንያ ባለቤት ነው፡፡ ኩባንያው ኮምፒዩተር ውስጥ ያሉ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ ሲስተሞች በአግባቡ እንዲሰሩ ለማስተዳደር የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያመርታል፡፡ የጌትስ ፈጠራ ኮምፒዩተሮች ለሁሉም በሚመች መልኩ ለሚሊዮኖች መዳረስ የሚችሉበትን ዕድል ፈጥሯል፡፡

**ቪንት ሰርፍ እና ሮበርት ካህን፡-** አሁን የምንጠቀምበት ኢንተርኔትን ያለ እነዚህ ሰዎች ማሰብ ይከብዳል፡፡ በኢንተርኔት የኔትዎርክ መሳሪያዎች መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር መሰረት የሆኑት "TCP/IP Protocols" የተሰኙ የመግባቢያ ማዕቀፎችን አበልጽገዋል። ስራቸውም በዓለም አቀፍ ደረጃ ኮምፒዩተሮች እንዲተሳሰሩ አድርጓል፤ የመረጃ ልውውጥንም በከፍተኛ ሁኔታ ቀይሯል፡፡

**ስቲቭ ጆብስ፡-** ከስቲቭ ወዚኒያክ ጋር በመሆን አይፎን የተሰኙ ዘመናዊና ተወዳጅነትን ያተረፉ፣ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ ስማርት ስልኮች ፈጠራ ጀርባ ይጠቀሳል። አይፓድ፣ ማክቡክ የተሰኙ ደረጃቸው ከፍ ያሉ፣ ለአጠቃቀም ምቹና በልዩ ሁኔታ የተነደፉ ታብሌቶችና ኮምፒዩተሮች ባለብሩህ አዕምሮው ካፈለቃቸው የፈጠራ ስራዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

ምንጭ፡- litslink.com፣ www.simplilearn.com ገፀ ድሮችና ሌሎች

ከጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# በፈተና ያልተደናቀፈው ሕይወት

**በሄለን ጥላሁን**

ወጣት ዮርዳኖስ ዘሪሁን ትባላለች። በጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት ክፍል ውስጥ የድህረ ገጽ ማበልፀጊያ እና የመረጃ ማዕከል አስተዳደር የደረጃ ሁለት ሰልጣኝ ነች፡፡ “ህይወት በመልክ ብዙ ፈተናዎች ስትታጀብ ወዴት መሄድ እንዳለብን እንኳን መረዳቱ አይኖረንም” የምትለው ወጣቷ፤ የገጠማት ፈተና አይደለም ትምህርቷን ልትማር ይቅርና በህይወት ለመኖር በእጅጉ ፈትኗት እንደነበር ትናገራለች፡፡

በብዙ ግራ መጋባት ውስጥ እያለች ነበር፤ የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች ፎረም (Forum for African women Educationalist - FAWE) ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ስለሚያደርገው የትምህርትና ስልጠና ድጋፍ ፕሮግራም ግንዛቤ ማግኘት የቻለችው እና ተጠቃሚ ለመሆን የበቃችው፡፡ ከዚህ ቀደም ትምህርት ለመማር ብትፈልግም የምትከፍለው ገንዘብ ባለመኖሩ ምክንያት ችግር ውስጥ ገብታ እንደነበር ታስታውሳለች፡፡

“በቤተሰቦቼ መካከል የተፈጠረ አለመግባባት፤ በትምህርቴ ላይ አደጋ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ የቱንም ያክል ትምህርቴን ለመማር ብፈልግም ከቤተሰብ ችግር የመነጨው መልካም ያልሆነ ሁኔታ ወደ ኋላ የሚጎትቱኝ ነገሮች እንዲበዙ ምክንያት ሆኖኛል፡፡ ትምህርቴን በትኩረት ለመማርም አእምሮዬ መረጋጋት ነበረበት፡፡ በብዙ ጉድለቶች ውስጥ ሆኜ የትምህርቴ ነገር ያሳስበኝ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ነበር የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች ፎረም ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ስለሚያደርገው የትምህርትና ስልጠና ድጋፍ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሚያደርገኝን ዕድል ያገኘሁት፡፡ እኔም ይህንን ወርቃማ ዕድል በደስታ ተቀበልኩት፡፡ እኔን ከችግር ትምህርቴንም ከተንገበበት አደጋ ታድጎናል” ብላለች፡፡

ከፕሮግራሙ ያገኘችውን ጥቅም እንዲህ ትገልፃለች፤ “የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች ፎረም በመረጥኩት የትምህርት ክፍል እንድማር ሙሉ ወጪዬን ችሎኛል፡፡ በተለይም የትምህርት ቁሳቁስ በማሟላት እንዲሁም የኪስ ገንዘብ (ለትራንስፖርት፣ ለስልክ እና መሰል ወጪዎች) በመስጠት ለትምህርቴ የሚያስፈልገኝን ነገሮች አሟልተውልኛል። እኔና መሰሎቼ ለችግሮቻችን እጅ ሳንሰጥ በተፈጠረልን ጥሩ እድል አማካኝነት ትምህርታችንን ከዳር ማድረስ እንዳለብን በደንብ አስገንዝቦናል። ይህም በቀጣይ ስኬታማ ወጣት የመሆን ህልሜን ለማሳካት ትልቅ አቅም ፈጥሮልኛል፡፡”

አቶ ለገሰ ደበሌ፤ በጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የጥራት ማኔጅመንት አስተባባሪ፣ መምህር፣ በጀነራል ዊንጌት የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች ፎረም ተጠሪ እና በአዲስ አበባ ቴክኒካል ኮሚቴ የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች ፎረም ሰብሳቢ ናቸው። የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች ፎረም፤ በዝቅተኛ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ላይ የሚገኙ ነገር ግን በትምህርት ክህሎታቸው የተሻለ ውጤት ያላቸውን ወጣቶች በተለይም ሴቶችን በቴክኒክ እና ሙያ ስልጠና ተደራሽ ማድረግ ብሎም ወደ ስራው አለም ገብተው ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል ቀዳሚ አጀንዳው አድርጎ ለመስራት የተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክቱ የተገበረባቸው ጀነራል ዊንጌት እና አዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፓሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ሲሆኑ፤ በሁለቱ ተቋማት እየሰለጠኑ ለሚገኙ ሰልጣኞች የተለያዩ ድጋፎችን እየሰጠ ይገኛል። ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር እና ፋዌ አፍሪካ ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር የሃርድ ስኪል አይነኬ የተባሉ እንደ ኮንስትራክሽን፣ ፊዚኮ ኬሚካል፣ ጋርመንት፣ አውቶሞቲቭ፣ አይ ሲቲ እና መሰል የትምህርት ዘርፎች ስልጠና ለሚከታተሉ ሰልጣኞች የትምህርትና ስልጠና ድጋፍ እያደረጉ ይገኛል። በፕሮግራሙ 80 ከመቶ ሴቶችን ተጠቃሚ ያደረገ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ከ5 እስከ 10 በመቶ ለአካል ጉዳተኛ እንዲሁም ከ10 እስከ 15 በመቶ ደግሞ ለሀገር ውስጥ ተፈናቃይ ዜጎች ዕድል ተሰጥቷል፡፡ የፕሮጀክቱ ትግበራ ለሰባት ዓመት ቆይታ እንደሚኖረው ጭምር አስታውቀዋል፡፡

የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አማራጮችን በመጠቀም ትምህርት መማር የሚፈልጉ ተማሪዎች እንዲመዘገቡ ለማድረግ እንደተቻለ የሚናገሩት አቶ ለገሰ፤ የምልመላው ሂደትም መክፈል ያልቻሉ እንዲሁም በከፍተኛ የኑሮ ፈተና ውስጥ የሚገኙትን የቅድሚያ ቅድሚያ ለመስጠት ችሏል። የትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው የመቁረጫ ነጥብ ያሟሉ ሆነው በዝቅተኛ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ላይ የሚገኙት ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ ሴት ተማሪዎች በተለያየ የኑሮ ፈተና ውስጥ ይገኙ እንጂ በውጤታቸው ጎበዝ የሆኑ ናቸው፡፡ በአዲስ አበባ ደረጃ 50 የሚሆኑ ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ በተለይ አይነኬ የተባሉ እንደ ኮንስትራክሽን፣ ፊዚኮ ኬሚካል፣ ጋርመንት፣ አውቶሞቲቭ፣ አይ ሲቲ እና መሰል የትምህርት ዘርፎችን የሚማሩ ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት 22 ሴት እና 5 ወንዶች በስልጠና ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

ለተማሪዎቹ የሚደረግላቸውን ድጋፍ በተመለከተ አቶ ለገሰ ሲያስረዱ በየወሩ የኪስ ገንዘብ፣ የትራንስፖርት፣ የቤት ኪራይ፣ የመማሪያ ቁሳቁስ፣ የዓመቱን የትምህርት ክፍያ በመሸፈን አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ገልፀዋል። በአስከፊ የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ያለፈ ተማሪ ፈተናው ዳግም እንዳይገጥመው የተመቻቸውን እድል መጠቀም እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ሴቶችን ማብቃት ብሎም መደገፍ በሀገር ግንባታ ላይ ትልቅ አሻራ እንደማስቀመጥ ነውም ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ለገሰ ገለጻ፤ የጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በዚህ ተግባር ላይ ያለው ሀላፊነት ከፋዌ ድርጅት ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ሰልጣኞቹን በየትምህርት ዘርፋቸው ክትትል የሚያደርጉላቸው መምህራን በመመደብ በትምህርት ውጤታቸው እንዳይቀንሱ ተገቢውን ድጋፍና ምክር ይሰጣቸዋል። ተሞክሮ ያላቸውን ሰዎች በማቅረብ የህይወት ልምድ ተሞክሯቸውን እንዲያጋሯቸው መድረክ ይመቻቻል፡፡

ሰልጣኞች በሚኖራቸው የትምህርት ቆይታ በአመርቂ ውጤት ለሚጨርሱ ድርጅቱ ማቋቋሚያ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው እንዲሰሩ በማድረግ ገበያው የሚፈልገውን ችሎታ እና አቅም አጎልብተው እንዲወጡ ማስቻል ላይ ትኩረቱን አድርጎ እየሰራ ይገኛልም ብለዋል፡፡

የፋዌ ኢትዮጵያ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰላማዊት አድማሱ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት ድርጅቱ ሲቋቋም አላማ ያደረገው የፆታ እኩልነትን፣ ጥራት ያለው ትምህርት ለሴቶች እና ለልጃገረዶች በመስጠት ሃላፊነቱን መወጣት የሚፈልግ ድርጅት ነው፡፡ ፋዌ በ33 የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ እየሰራ ይገኛል፡፡ ዛሬ ላይ በተለያየ አግባብ ድጋፍ የተደረገላቸው ወጣቶቹ ነገ ላይ ቤተሰባቸውን፣ እራሳቸውን እንዲሁም ሀገርን የሚጠቅሙ እንደሚሆኑ ገልጸዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሰላማዊት ገለፃ፤ የድርጅቱ አላማ የስርዓተ ፆታ እኩልነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሴቶች በተለያየ ጫና ውስጥ ህይወታቸውን እንዲያሳልፉ ይገደዳሉ። ታድያ በብዙ ጭንቅና ችግር ውስጥ የምታሳልፍ ሴት ከትምህርቷ እንዳትሰናከል ከህልሟ እንዳትለያይ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ላይ ትኩረቱን ያደረገ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑት ሁለት የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች አሉ፡፡

እንደ ጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅም ለሰልጣኞች የሚሰጡ ስልጠናዎችን የተግባር ላይ ልምምዶችን የሚያዘወትሩ መሆኑን ተከትሎ ሰልጣኞች ሙሉ ትኩረታቸውን ወደ ትምህርታቸው እንዲሆን ያግዛቸዋል። ምንም አይነት በአእምሯቸው ቀረ ብለው የሚጨነቁለት ጉዳይ እንዳይኖር የሚያስፈልጋቸውን ድጋፎች በማሟላት ካለምንም ችግር ትምህርታቸው ላይ በማተኮር ብቻ እንዲሰለጥኑ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አካል ጉዳተኞችን፣ ተፈናቃዮችን፣ ስደተኞችን እንዲሁም በዝቅተኛ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን በምንለይበት ወቅት ጥንቃቄ በተሞላው አግባብ ትክክለኛውን ችግረኛ የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ለሚገኙ ሁለት የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች 50 ለሚሆኑት ሰልጣኞች እድሉን በማመቻቸት ወደ ስራ ስለመግባቱ አክለዋል፡፡


ፎቶ በገነት ወንድሙ
ሰልጣኝ ወጣት ዮርዳኖስ ዘሪሁን




## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን
## ADDIS ABABA ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITH

**ለመላዉ የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ።**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብ፣ ፅዱ፣ ማራኪና ከአካባቢ ብክለት የፀዳች ለማድረግና እየተከናወኑ ካሉ የኮሪደር እና የወንዝ እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎች ጋር ተጣጣሚ እንዲሆን፣ በአካባቢ ብክለት መከላከል ላይ ያተኮረ ሰፊ ስራ እየሰራ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከአረፋ በዓል ጋር ተያይዞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የዓለም የአካባቢ ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ52ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ32ኛ ጊዜ ግንቦት 28 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ "የፕላስቲክ ብክለትን በጋራ እንከላከል" በሚል መሪ ሀሳብ በደመቀ ሁኔታ በከተማችን እየተከበረ ይገኛል፡፡ በዚህም ለመላዉ የከተማችን ማህበረሰብ እንኳን ለዓለም የአካባቢ ቀን አደረሳቸሁ እያለ ከተማችንን ከፕላስቲክ ብክለት እንድንጠብቅ እና እንድንከላከል ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ፡፡

የአረፋ በዓልን ስናከብርም በተለይ እርድ በሚከናወንበት ሰዓት አካባቢ እንዳይበከል ጥንቃቄ ማድረግ፣ በተገቢ ሁኔታ ቆሻሻዎችን ማስወገድ ያስፈልጋል የሚል መልዕክታችንን እናስተላልፋለን፡፡

**መልካም በዓል**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን**


በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ውስጥ በካርታ ቁጥር 079/6/15 በሴሪ ቁጥር 0259376 በ ገ/ጊዮርጊስ ሀ/ሚካኤል የተመዘገበ ይዞታ ዋናው ካርታ ከማህደር ክፍላችን የጠፋባቸው ስለሆነ ካርታውን የያዘ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የካርታ ቁጥር ቦ/ሳሚ/42/6509/01 የሆነው ሰርተፍኬት በፅፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው በቤት ባለቤትነት ዘምዘም ኡስማን አብደላ ካርታ በሴሪ ቁጥር 022720 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቼዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደምንሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ሙባረክ ከድር ኡመር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061007267670110 ሴሪ C239400 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ መንገሻ ቦጋለ መታፈሪያ ስም የተመዘገበ ይዞታ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 04 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090405566 ሴሪ ቁጥር L 0118683 የሆነ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት(ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በ21/09/2017 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አብደላ አወል ሸሪፍ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 09 ነዋሪ የሆነው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100903484 የሴሪ ቁጥር 081093 በቀን 10/12/2014 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋላው /ይዤዋለው/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደምንሰጣቸው እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የካርታ ቁጥር ቦሌ/48/06/19/4856/00 የሆነው ሰርተፍኬት በጽፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው በቤት ባለቤትነት ሙሉጌታ ዘውዴ በሻህ ካርታ በሴሪ ቁጥር 037473 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቸዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደምንሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት አዳነች አስፋው ቁምላቸው በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀድሞ ቀበሌ.... በአሁኑ ወረዳ 07 ቤት ቁጥር ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር ወ7/ውዝ01/1680/31399/00 በሴሪ ቁጥር - 0704189 ኦርጅናሉ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በዕዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ 30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ሌላ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የኮ/ቀ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ውስጥ በካርታ ቁጥር 028415 በሴሪ ቁጥር 013518 አቶ ፋሩቅ ጀማል በተጋሪ ራህመት ገብሩ የተመዘገበ ይዞታ ዋናው ካርታ የጠፋባቸው ስለሆነ ካርታውን የያዘ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ አበባ ዘርዓይ አስፍሀ አድራሻው በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥር 1434 ካርታ ቁጥር ል/1/6/31717/31106/19750/19842/03 ሴሪ ቁጥር 0689308 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት / ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ከዚህ በታች በተገለፀው ክፍት የስራ መደብ ላይ ሥራ ፈላጊዎችን አወዳድሮ በኮንትራት ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | ተፈላጊ የትምህርት ዓይነትና ደረጃ | | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የትምህርት ዓይነት | የትምህርት ደረጃ | | | |
| 1 | ፎርማን | X | 7,934 | ሲቪል ኢንጂነሪንግና አቻ፣ ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና አቻ፣ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንትና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 4 አመት | 1 | በዋናው መ/ቤት |
| 2 | የቀለም ማሽን ዋና ኦፕሬተር | IX | 7,424 | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 4 አመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 3 | የቀለም ማሽን ረዳት ኦፕሬተር | VIII | 6,940 | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 አመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 4 | የቦይለር ማሽን ዋና ኦፕሬተር | IX | 7,424 | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማሽን ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 4 አመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 5 | የቦይለር ማሽን ረዳት ኦፕሬተር | VIII | 6,940 | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 አመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 6 | ዋና የቅየሳ ባለሙያ | VIII | 6,940 | ሰርቬይንግ ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 አመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 7 | ረዳት የቅየሳ ባለሙያ | VII | 6,485 | ሰርቬይንግ ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 0 አመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 8 | የመንገድ ብሎወር ማሽን ኦፕሬተር | IX | 7,424 | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማሽን ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 አመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |

**ማሳሰቢያ**

- አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 /አስር/ ተከታታይ የሥራ ቀናቶች ውስጥ ብቻ ማመልከት ይችላሉ፡፡
- የምዝገባ ቦታና ሰዓት ከ 22 ወደ መገናኛ በሚወስደው መንገድ መከሊት ህንፃ 10ኛ ፎቅ የሰው ኃይል አስተዳዳር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 10-06 በሥራ ሰዓት ጠዋት ከ2፡30 - 6፡30 ከሰዓት ከ7፡30 - 11፡30 ድረስ
- በምዝገባ ወቅት አመልካቾች ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ኦረጅናልና ከማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚቀርብ የሥራ ልምድ ማስረጃ የሥራ ግብር የተከፈለበት መሆኑን የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡
- የሥራ ቦታ አዲስ አበባ በዋናው መ/ቤት

**ስልክ ቁጥር 0913045587**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር MK-98-02-3666 በወ/ሪት ኤልሳቤጥ መላኩ ገዛኸኝ ስም የተመዘገበው የይዞታ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/15/16/546/26/2001 ሴሪ ቁጥር 024556 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 27/09/2017 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ ጽ/ቤት**

---

ጅማ ዩኒቨርሲቲ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060502550 ሴሪ ቁጥር L0105200 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታኘ ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ አለማየሁ መንገሻ ወልደአረጋይ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 03 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) AA000080301269 የሆነው ካርታ የሴሪ ቁጥሩ 084369 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሪት ትርሀስ ገ/ጊዮርጊስ ወልዱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 027779/1 የሴሪ ቁጥር 067279 የይዞታ ስፋት 94.64 ካ.ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር 8029/02 በቀን 07/09/2017 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**



CRRSA
የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ
የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ነን!
ተቋማችን በሰለጠነ የማንነት አስተዳደር ስርዓት የተገነባች ስማርት አዲስ አበባችንን እውን ለማድረግ እየተጋ ይገኛል! አዲስ አበባችን የሚከሰቱ ኩነቶችን መዝግባ የተሟላ መረጃ ማመንጨት ትችል ዘንድ የወሳኝ ኩነት አገልግሎትን ከመደበኛ ጽህፈት ቤቶቹ በተጨማሪ፡
* በ147 የግል እና የመንግስት የጤና ተቋማት፣
* በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲሁም
* በጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤት የአንድ መስኮት አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን።
ህፃናት ስም የማግኘት፣ ወላጆቻቸውን የማወቅ እና ዜግነት የመጎናፀፍ መብት አላቸው፤ ይህም በልደት ምዝገባ ይረጋገጣል። እኛም እዚሁ በአንድ መስኮት በጤና ማዕከል ቢሮ ከፍተን እንደተወለዱ መዝግበን ማስረጃ እንሰጣለን።
ውድ የከተማችን ነዋሪዎች
* የ2018 ዓ.ም የተማሪዎች የትምህርት ቤት ምዝገባ የሚከናወነው በልደት ምዝገባ ማስረጃ እና በፋይዳ የምዝገባ ቁጥር በመሆኑ አቅራቢያዎ ባሉ ጽህፈት ቤቶቻችን በመምጣት ለተማሪ ልጆቻችሁ ቅደመ ሁኔታዎችን ያሟሉ!
እንኳን ለኢድ አል አድሃ (አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
ለበለጠ መረጃ፡- በ7533 ይደውሉልን ድክመቶቻችንን አርመን የተመሰከረለት ተቋም እንገነባለን!
የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ
Eid-Al-Adha
Mubarak




1990
GIFT
REAL ESTATE
ልዩ የበዓል ቅናሽ
ከጊፍት ሪል ስቴት!
ጊፍት ሪል ስቴት የኢድ አል-አድሃ/አረፋ በዓልን ምክንያት በማድረግ ለአምስት ቀናት የሚቆይ በአፓርትመንቶች እና በንግድ ሱቆች ልዩ የበዓል ቅናሽ አድርጓል።
ለበዓሉ እስከ 15% በሚደርስ ቅናሽ በ9% ቅድመ ክፍያ በለገሃር፣ በተክለሃይማኖት፣ በሲኤምሲ እና በ22 ማዞሪያ መንደሮቻችን ልዩ የበዓል ቅናሽ ማድረጋችንን ስንገልጽ በደስታ ነው።
ኢድ ሙባረክ!
ጊፍት ሪል ስቴት
ማህበረሰብን እንገነባለን!
ለበለጠ መረጃ፡- Call: +251979 65 65 65 /+251984 65 65 65 Short code: 8055
8555

## የባህር ... ከገጽ 4 የዞረ

ወንዞች በኩል የቼኮዝሎቫኪያ የባህር ንግድ እንዲኖር አስችሏል።

በፖለቲካ ድርድርና ውይይት አማራጭን ስንመለከት ደግሞ በደቡብ እስያ የምትገኘውን አነስተኛዋን ወደብ አልባ ከተማ ቡታንን እናገኛለን፡፡ በሶስት ጎን ከህንድ እና በሰሜን ከቻይና ጋር ድንበር ትጋራለች። ነገር ግን ደግሞ በሀገራቱ መካከል በተደረገ ውይይትና ድርድር መነሻነት የባህር ድንበር በመጋራት አገራቱ የንግድ፣ ቱሪዝም እና የባህር ውስጥ ሃብትን በጋራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዳስቻላቸው የቢቢሲ ዘገባ ያትታል፡፡

አፍሪካ ውስጥም ለምሳሌ ኮንጎ ኪንሻሳና ኮንጎ ብራዛቪልን ማንሳት ይቻላል፡፡ ኮንጎ ኪንሻሳ የቤልጂየም ግዛት ነበር፡፡ ብራዛቪል ደግሞ የፈረንሣዮች ነበር፡፡ ኮንጎ ብራዛቪል ወደብ አልነበረውም፡፡ ሁለቱም ተስማምተው ከኮንጎ ኪንሻሳ የተወሰነ መሬት ወስደው ኮንጎ ብራዛቪል ወደ ባህር እንድትዘልቅ ተደረገ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የዓለም አቀፍ ህግጋትና ተግባራዊ ማሳያዎች እንደሚያሳዩት የባህር በር ያለው ሀገር የባህር በር የሌለውን ሀገር የባህር ንግድ እንቅስቃሴ ማወክ እንደማይችል ማረጋገጫ የሚሰጥ ነው፡፡ የወደብና ትራንዚት አገልግሎት ላይ ሆን ብሎ መጓተት መፍጠር፣ ያልተመጣጠነ ክፍያ መጠየቅ እንደዚሁም ሆነ ከስምምነት ውጪ የሆኑ ነገሮችን ካላስፈጸምኩ ማለት የተከለከለ መሆኑንም ያመለክታል፡፡ ሕጉ የባህር በር ያላቸው ሀገሮች የባህር በር የሌላቸው ሀገሮችን ህልውናና ብሔራዊ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል እንቅስቃሴ ከማድረግ መቆጠብ እንዳለባቸውም ያስታውቃል።

## “ሪፎርሙ ... ከገጽ 7 የዞረ

ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ የዘንድሮውን ዓመት ዓይነት እድገት በተከታታይ አምስት ዓመታት ማስመዝገብ ከተቻለ ሀገሪቱን በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የወጪ ንግዱን አፈፃፀም ማየት በቂ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከ1984 ዓ.ም እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ ባሉት 15 ዓመታት ውስጥ ለዓለም ገበያ ምርቶቿን በመላክ ያገኘችው አጠቃላይ ገቢ 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ነበር፡፡ በአንፃሩ ዘንድሮ በአንድ ዓመት ብቻ ከ8 ቢሊየን ዶላር በላይ ታገኛለች፡፡ ይህን በአግባቡ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

ለውጭ ከተላኩ ምርቶች መካከል የቡና እና ወርቅ ምርት የወጪ ንግድ አፈጻጸምንም ለአብነት ያክላሉ፡፡ ከቡና ከ1984 ዓ.ም እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ ባሉት 15 ዓመታት ውስጥ 3 ነጥብ 5 ቢሊየን ዶላር የተገኘ ሲሆን፣ ዘንድሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ከ2 ነጥብ 5 ቢሊየን ዶላር በላይ ተገኝቷል፡፡ ይህ በብዙ ድካም የተገኘ መሆኑን ጠቁመው ለዚህም የአረንጓዴ አሻራው ትልቅ አስተዋፅዖ ማበርከቱን አንስተዋል፡፡

ሌላው በ15 ዓመት ውስጥ ለውጭ ከተላከ የወርቅ ምርት 508 ሚሊየን ዶላር ገቢ ብቻ ነበር የተገኘው፡፡ በአንፃሩ በዘንድሮ ዓመት በ6 እጥፍ በማደግ 3 ነጥብ 2 ቢሊየን ዶላር ተገኝቷል፡፡ በአንድ ዓመት ብቻ የተመዘገበው ውጤት በተከታታይ አራት እና አምስት ዓመታት ማስመዝገብ ከተቻለ ውጤቱን መገመት ቀላል ይሆናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በከፍተኛ ሁኔታ የሚታይና የሚዳሰስ ለውጥ መምጣቱንም ተናግረዋል፡፡

አሁን ላይ በኢትዮጵያ ከ30 በመቶ በላይ የነበረው የዋጋ ግሽበት ወደ 13 ነጥብ 5 በመቶ ወርዷል፡፡ የወጪ ንግድ ገቢ መጨመር፣ የድህነት ቅነሳ ስራው፣ የዕዳ ክምችት መቀነስ ኢትዮጵያ ከዋጋ ግሽበት በማገገም ላይ መሆኗን ያሳያል፡፡ ያሳካናቸው፣ የልጆቻችንን እዳ የቀነስንበት ልክ ኢትዮጵያ በመዳን ላይ እንዳለች ማንም ሰው ሊገነዘበው የሚችል ሀቅ ነው፡፡

ልማት ባለበት ሀገር የዋጋ ግሽበት ተንቀሳቃሽ ፈተና በመሆኑ ይህን ሊከላከል የሚችል ጠንካራ ሥራ እየሠሩ መቀጠል ወሳኝነት አለው ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው በውጭ ጫና የተወሰደ ነው በሚል ስለሚነሳውም፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ “ለገበያ ክፍት ይሁን፣ የተሳሰረው ይፍታታ” የሚለው ሀሳብ ከዓለም ባንክ ወይም ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ጋር ንግግር ከመጀመሩ በፊት የተያዘ አቋም ነው፡፡ ኢኮኖሚው ለውጭ ገበያ እንዲከፈት ሲወሰንም ይህንን መንገድ ከተከተሉ ሀገሮች ትምህርት መወሰዱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጠቁመዋል፡፡

የኢኮኖሚ ሪፎርሙ ሲተገበር የሚያስከትለውን ጫና ለመቀነስ መንግስት ባለፈው ዓመት ለነዳጅ፣ ማዳበሪያ፣ መድኃኒት፣ ሴፍቲኔትና ሌሎች አገልግሎቶች 350 ቢሊዮን ብር ገደማ ድጎማ አድርጓል፡፡ ሀገሪቱ ያለባት እዳም እንዲሸጋሸግ ድርድር ተደርጓል፡፡ በቅርቡ የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ተቋም ባደረጉት ስብሰባ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሪፎርም ውጤታማነት ተወድሷል፡፡ ይህም ሪፎርሙ በምክክር፣ በእውቀትና ጥበብ የተመራ ለመሆኑ ማሳያ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሊሂቃን ጃፓንን ሄደው ካዩ በኋላ “ጃፓን እንደምን ሰለጠነች?” ይላሉ፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ ለምን ደኸየች? የሚለውን በጥልቀት መርምረን እስካልመለስን ድረስ ውጤት ማምጣት አይቻልም፡፡ ክፍተት የነበረውና እኛ ልንሞላ የሞከርነው “ኢትዮጵያ ለምን ደኸየች ?”፤ በዓመት ሁለት ጊዜ ለምን ማረስ አልተቻለም? ለምን እንለምናለን? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ከውጭ የተገኘውንና የራስን በማዋሀድ መስራት በመጀመራችን የሚታይ ውጤት እያየን ነው፡፡

ሪፎርሙ ከኢትዮጵያ ሁኔታ የተነሳ፣ ከሌሎች ትምህርት የተወሰደበትና በእኛ ልክ የተሰፋ ነው፡፡ በዚህም ውጤታማ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡

የመንግስት ትኩረት ለአገልግሎት እንጂ ለአምራች ዘርፉ አይደለም በሚል የሚቀርቡ ሀሳቦችም ተጨባጭነት ያላቸው እንዳልሆኑ ተናግረዋል፡፡ በአንድ ዘርፍ ላይ ጥገኛ የሆነ ኢኮኖሚ የኢትዮጵያን ስብራት እንደማይጠግን በመረዳት ኢኮኖሚው ብዝሃ ዘርፍ፣ ብዝሃ ተዋንያንና ብዙሃኑን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንዲሆን ተሰርቷል፡፡

ከኢንዱስትሪ ልማት ጋር በተያያዘም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ፋብሪካዎች ካላቸው አቅም 48 በመቶ ብቻ ነበር የሚያመርቱት፡፡ የመሬት፣ የሃይል፣ የፋይናንስና የግብአት አቅርቦት ችግሮች ነበሩባቸው፡፡ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄም ለችግሮቹ ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ አሁን ላይ የማምረት አቅማቸውን ወደ 65 በመቶ ማድረስ መቻሉን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡

## የተመላላሽ ... ከገጽ 9 የዞረ

ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የሚመለከታቸው አካላት የክትትልና ድጋፍ አግባባቸውን አጠናክረው ማስቀጠል ይጠበቅባቸዋል።

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ሙሉጌታ እንዳለ ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል በሰጡት መረጃ፣ ለህብረተሰቡ እየተሰጡ ከሚገኙ የጤና አገልግሎቶች መካከል በዋናነት የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ይጠቀሳል፡፡ ከክትባት ጀምሮ የተለያዩ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት በከተማዋ ለህፃናትና ለአዋቂዎች በመንግስት ሆስፒታሎች እና በ96 ጤና ጣቢያዎች እየተሰጠ ነው፡፡ በ57 ጤና ጣቢያዎች ደግሞ አገልግሎቱ በሲስተም ተደግፎ እየተሰጠ እንደሚገኝ አንስተዋል፡፡

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ማብራሪያ፣ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎቱን ተደራሽነት ለማስፋት የጤና ተቋማትን ከማስፋት ባለፈ የጤና ባለሙያዎችን ቁጥር ማሳደግ ላይም ትኩረት ተደርጎ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ ቀደም ጤና ጣቢያዎች ላይ ጠቅላላ ሀኪም አይመደብም ነበር፡፡ የሚሰጠው የህክምና አገልግሎትም ውስን በመሆኑ “ጤና ጣቢያ ላይ መታከም የማይችሉ” በሚል ወደ ሆስፒታል እንዲሄዱ ይደረግ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ሆስፒታሎች ላይ ጫና ይፈጥር ነበር፡፡ እንደ አዲስ አበባ በተሰራው የሪፎርም ስራ በሁሉም ጤና ጣቢያዎች በአማካኝ እስከ አምስት ጠቅላላ ሀኪሞች እንዲሁም የጤና መኮንኖችና ሌሎች የጤና ባለሙያዎችን በመመደብ የሚሰጠውን አገልግሎት ደረጃውን ከፍ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር ሙሉጌታ እንዳስረዱት፤ ቀድሞ በነበረው አሰራር አንድ ታካሚ ወደ ሆስፒታል በሪፈር ተልኮ የተመላላሽ ህክምና ክትትል ከጀመረ ከ30 ዓመት በላይ ቢሆን ለክትትሉ ወደ ሆስፒታል ብቻ ነው የሚሄደው፡፡ በዚህም ተገልጋዮች ሆስፒታል ለማግኘት ረዥም ወረፋ የሚጠብቁበት ሁኔታ ነበር፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍም አገልግሎቱን ሰፋ በማድረግ ሆስፒታሎችን ከጤና ጣቢያዎች ጋር ትስስር በመፍጠር አገልግሎቱን በጤና ጣቢያ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው፡፡ በጤና ጣቢያ መስጠት የሚችለው አገልግሎት ሆስፒታሎች ላይ ጫና እንዳይፈጥር ከሆስፒታል ወደ ጤና ጣቢያዎች ሪፈር የማድረግ ስራ እንደሚሰራም ነው የገለፁት፡፡

በጤና ተቋማቱ ቀልጣፋ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለመስጠት ሃያ አራት ሰዓት የተሰራውን የጤና አገልግሎት ስራ በየቀኑ ጠዋት እየገመገሙ መሻሻል ያለበትን እያስተካከሉ የሚሄዱበት አሰራር ተተግብሯል፡፡ በጤና ተቋማቱ ቀልጣፋ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለመስጠት ሃያ አራት ሰዓት የተሰራውን የጤና አገልግሎት ስራ በየቀኑ ጠዋት እየገመገሙ መሻሻል ያለበትን እያስተካከሉ የሚሄዱበት አሰራር ተተግብሯል፡፡ እንዲሁም ተገልጋዩ በጠዋት የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለክትባት 1:30 ላይ፣ መደበኛ የጤና አገልግሎት ደግሞ 2:00 ሰዓት ላይ እንዲጀምር እንዲሁም የጤና ባለሙያዎች ምሳ ሰዓትን ጨምሮ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ህዝቡን በተገቢው ሁኔታ የማገልገል ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ለአብነት ጃንሜዳ፣ አዲሱ ገበያ፣ ቀበና፣ ገርጂ፣ አፍንጮ በር፣ አዋሬ፣ በአታ፣ ኮተቤ፣ ባሻ ወልዴ፣ ቸርችል፣ ራስ እምሩ፣ ኮልፌ እና በርካታ ጤና ጣቢያዎች አገልግሎቱን እየሰጡ ሲሆን በቀጣይ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚደረግ ዶ/ር ሙሉጌታ ገልፀዋል፡፡

የጤና ጣቢያዎችን ደረጃ በሰው ሃይልና በግብዓት በማሻሻል ደረጃውን የጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ ነው፡፡ በዚህም የካንሰር፣ የዓይን፣ የቆዳ፣ የጥርስና ሌሎችም የህክምና አገልግሎቶች የመስጠት ሁኔታ መጀመሩንም ዶ/ር ሙሉጌታ ገልጸዋል፡፡

ስኳር፣ የደም ግፊት፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ሌሎችም ህመሞች የማይቋረጥ ክትትል የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው ክትትል የሚያደርጉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ሁሉ አልፎ አልፎ ድንገት ትዝ ሲላቸው ወይም ህመም ሲሰማቸው ብቻ ክትትል የሚያደርጉ፣ ቀጠሮ የሚያቋርጡ፣ ቀጠሮ የሚያሳልፉ፣ የተሰጣቸውን የሀኪም ትእዛዝ መሰረት አድርገው መድሐኒትን በትክክል የማይወስዱም አሉ። በመሆኑም በተመላላሽ ህክምናም ይሁን በሌሎችም የጤና አገልግሎቶች ህብረተሰቡ በጤና ባለሙያ የሚሰጠውን ትእዛዝ በመቀበል መድሐኒትን በአግባቡ በመውሰድና በቀጠሮ መሰረት ሳያቋርጡ ክትትል በማድረግ ራሳቸውን ከተጨማሪ ተጓዳኝ በሽታ መጠበቅ እንዳለባቸው ዶ/ር ሙሉጌታ አፅንኦት ሰጥተው አስገንዝበዋል፡፡

በሁለቱም ጤና ጣቢያዎች ባደረግነው ቅኝት የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ታካሚዎች ያለምንም መጨናነቅ በአግባቡ ሲስተናገዱና አገልግሎት ሲያገኙ ተመልክተናል፡፡ መድሐኒት በቀጠሯቸው እለት ሳይወስዱ የቀሩ ተመላላሽ ታካሚዎች ሲስተሙ ላይ መውሰድ ወይም አለመውሰዳቸውን በመከታተል፤ ሀኪሞች ስልክ በመደወል የሚያደርጉት እገዛ አገልግሎቱ ተገልጋዩን የሚያረካ እንዲሆን የሚደረገው ጥረት አካል በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥል ለማለት እንወዳለን፡፡

# ስፖርት ለቱሪዝም እድገት ምን ያህል አቅም አለው?

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የስፖርት ቱሪዝም በዓለም ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣ የገቢ ምንጭ፣ የሀገር ገፅታ መገንቢያና የዲፕሎማሲ መሳሪያ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። የስፖርት ፌስቲቫሎችና ውድድሮች ማለትም እንደ ማራቶን፣ እንደ ኦሎምፒክ ጨዋታዎች ወይም የዓለም ዋንጫ አይነት ውድድሮች እንደዚሁ የአንድን ሀገር ወይም ከተማ መሠረተ ልማት፣ ባህል እና አጠቃላይ መስህብ በማጉላት ከተማን ከዓለም ጋር በማስተዋወቅ ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

በዓለም አትሌቲክስ ውድድር የፕላቲኒየም ደረጃ ያለው የለንደን ማራቶን፣ የዱባይ ማራቶን፣ የቫሌንሺያ ማራቶን ከጀርባቸው ያነገቡት ዓላማ ከስፖርታዊ ውድድር የሚሻግር ሲሆን በተለይም እነዚህ ከተሞች ያሏቸውን ገፀበረከቶች ለዓለም በማስተዋወቅ በዘላቂነት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ‹The Economic Effects of a Marathon as a Sport Tourism Event› ጥናታዊ ጽሑፍ ፀሀፊው ግሪጎሪ ፓፓኒኮስ በተለይም ባለፉት አሥርት ዓመታት እንደ ማራቶን ያሉ ስፖርታዊ ፌስቲቫሎች ብዙ ጎብኝዎችን ከመሳባቸው በተጨማሪ ሀገርን ማስተዋወቂያ መሳሪያ በመሆን ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው ይላሉ፡፡

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ መለያ ውድድር እውቅና የተሰጠው የዱባይ ማራቶን ውድድር ለዱባይ ዋና የቱሪዝም አሽከርካሪነት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለውም በምሳሌነት ይጠቅሱታል፡፡ ውድድሩ ዱባይን እንደ መሪ የቱሪስት እና የስፖርት ማዕከል በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወትና አትሌቲክስ አፍሪካ የተሰኘው ሚዲያም ባወጣው መረጃ በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ አማተር ሯጮችን ይስባል ሲል ዘግቧል።

በእንግሊዝ በካንተርበሪ ዩኒቨርሲቲ ስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ፕሮፌሰሩ ማይክ ዊድ ስፖርት በራሱ እንደቱሪዝም መስህብነት ገቢ ከማስገኘቱም በላይ ስፖርቱን ራሱን ተጠቅሞ ደግሞ ከተሞችን በማስተዋወቅ ከቱሪዝም ዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ያነሳሉ፡፡

የማራቶን ዝግጅቶችና ውድድሮች ሰፊ ቦታና ርቀትን ስለሚፈልጉ በከተማ ልማት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለቱሪዝም እና ለብራንድ ማሻሻያ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። እንዲሁም የመሠረተ ልማት ማሻሻያዎችን ማበረታታት እና በነዋሪዎች መካከል የአካል ብቃት ግንዛቤን ማሳደግ ያስችላሉ። በተጨማሪም የአደባባይ ስፖርታዊ ውደድሮች ኢንቬስትመንትን ሊስቡና ለአስተናጋጅ ከተማ መልካም ገጽታ መፍጠር ያስችላል። እንደዚሁም ዓለም አቀፍ ትኩረትን ወደ ከተማው ከማምጣታቸው በተጨማሪም


ፎቶ ከገፀ ድር
በመዲናዋ እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት ለስፖርቱም ዘርፍ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው

ማህበረሰቡ በስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ተሳትፎውን እንዲያሳድግ ያበረታታል፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ያስተዋውቃል እንደዚሁም ለአዎንታዊ የከተማ ገጽታ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ የሚያብራራው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ አሰልጣኙ ዳንኤል ሙሉጌታ ነው፡፡

የቱሪስት መስህቦችን ለማስተዋወቅ ያለመውና በዛሬው ዕለት የሚካሄደው የ 5 ኪሎ ሜትር ሩጫ ውድድርም ከዚህ አንጻር የሚመዘን ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የቱሪስት መስህቦችን ለማስተዋወቅ ያለመው የ 5 ኪሎ ሜትር ሩጫ የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ አዘጋጅነት የሚካሄድ ነው፡፡ መነሻዉን ከሴቶች አደባባይ አድርጎ እስከ ሸራተን አዲሱ አስፓልት በሚዘልቀዉ በዚህ ሩጫ ላይ በኮሪደር ልማት የተሰሩ መዝናኛዎችን፣ ፓርኮች እና ሙዚየሞችን የማስተዋወቅ ስራ እንደሚሰራ የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ማርኬቲንግ እና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር ፍሬህይወት ገብረመድን ገልፀዋል።

ከ1 ሺህ እስከ 1 ሺህ 5 መቶ የሚሆኑ ሰዎች እንደሚሳተፉበት በሚጠበቀው የሩጫ ውድድር፣ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ለሚወጡ አሸናፊዎች እንደየ ደረጃቸዉ ከ30 እስከ 20 ሺህ ብር የገንዘብ ሽልማት እንደሚበረከትላቸዉ የአፍላንድ የምሽት ሩጫ ጀነራል ማናጀር አርቲስት ኢሳያስ መለሰ ጠቁመዋል፡፡ “እኔም አሻራዬን ላኑር” በሚል መሪ ሀሳብ የሚካሄደው የምሽት ሩጫ የመዲናዋን የልማት ስራዎች እና የመስህብ መዳረሻዎች በስፋት ያሳያል ተብሏል። ሩጫዉ ዛሬ ግንቦት 30 ቀን ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል ተብሏል።

አዲስ አበባ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በተሰሩና እየተሰሩ ባሉ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ፓርኮች፣ አደባባዮችና ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መልኳ እየተቀየረ መጥቷል፡፡ በዚህ ረገድ ከአራት ዓመታት ወዲህ የተሰሩ ስራዎች ለስፖርቱ ቤተሰብና አካል ብቃት እንቅስቃሴ የማድረግ ልምድ ላላቸው የመዲናዋ ነዋሪዎች ይዞት የመጣው ገጸ በረከት ቀላል አይደለም፡፡

ማህበረሰብ አቀፍ የስፖርት እንቅስቃሴውን ለጤናማ ማህበረሰብ ከመፍጠሪያነት ባለፈ ለሁሉም የስፖርት አይነቶች ሁሉ ምንጭነት እንደሚጠቅም ባለሙያዎች ያስረዳሉ። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ አሰልጣኙ ዳንኤል ሙሉጌታም እንደሚገልጸው የስፖርት እንቅስቃሴውን ማህበረሰቡ ባህል እንዲያደርገው ምቹ መስሪያ ቦታዎች መስፋፋት እንደሚኖርባቸውና በዚህ ረገድ አዲስ አበባ እየሰራች ያለው ስራ የሚበረታታ ስለመሆኑ ያነሳል፡፡ የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርትን በማጠናከር ለሁሉም የስፖርት አይነቶች ተወዳዳሪዎች ምንጭ መሆን በሚችልበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ጨምሮ ገልጿል፡፡

በእርግጥ አዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ታላላቅ ስፖርታዊ ውድድሮች እየተከናወኑባት ያለች መዲና ሆናለች፡፡ ለማሳያ ያህል ጥቂቶቹን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በየጊዜው ከሚያካሂዳቸው የማስ ስፖርት እንቅስቃሴ በተጨማሪ ከ14 ክለቦች የተውጣጡ 330 ተወዳዳሪዎች በሁለቱም ጾታ የተሳተፉበት ማራቶን ውድድር፣ የአዲስ አበባ ከተማ ብስክሌት ፌዴሬሽን ከኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ሼር ካምፓኒ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት የብስክሌት ውድድር እንደዚሁም ከቸርቸል ጎዳና እስከ ለገሀር በተሰራው የኮሪደር ልማት የተከናወነው ዓመታዊ የኮካ ኮላ የብስክሌት ውድድር ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርት ማስፋፊያና ተሳትፎ ዳይሬክተር አቶ እንግዳወርቅ ዳንኤልም ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት ከተማዋ አሁን ላይ በቀንም ይሁን ምሽት ላይ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚዘወተርባት ከተማ ሆናለች፡፡ ይህ ደግሞ ለማህበራዊ ትስስር፤ ለጤና እና ትውልድን ከመገንባት እና በስነ-ምግባር የታነጸ ዜጋ ከመፍጠር አንጻር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ማስ ስፖርት ለጤና ከሚሰጠው ጠቀሜታ

> **“እኔም አሻራዬን ላኑር” በሚል መሪ ሀሳብ የሚካሄደው የምሽት ሩጫ ዛሬ ግንቦት 30 ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል**

ባሻገር በህዝቦች መካከል መቀራረብንና ወዳጅነትን በመፍጠር ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተሰሩ ስራዎችም ሰፋፊ ስፖርታዊ ሁነቶችንና ውድድሮችን ለማዘጋጀት አዲስ አበባም ምሽት ላይ ጭምር ብርሃናማ የሆነችና የተስተካከለች ከተማ እየሆነች ስለመምጣቷ ያስረዳሉ፡፡

በከተማዋ ልዩ ቀለም ያለው ለሩጫ ብቻ ተብሎ በተዘጋጀው በርካታ ኪሎ ሜትሮችን በሚሸፍነው መንገድ ላይ የውጭ ሀገር ዜጎችን ጨምሮ በርካታ የመዲናዋ ነዋሪዎች በየቀኑ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ሲያደርጉ መመልከት የተለመደ ነው፡፡ ከእንደዚህ አይነት ዘወትርአዊ እንቅስቃሴዎች በተጨማሪ ዛሬ እንደሚካሄደው አይነት የምሽት የማራቶን ስፖርታዊ ውድድሮች ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም አቅም ከማስተዋወቃቸው በተጨማሪ መዲናዋ በምሽት ስላላት ድባብና እንቅስቃሴ ለማስተዋወቅ በር ይከፍታል ይላሉ የምሽት ሩጫ ጀነራል ማናጀር አርቲስት ኢሳያስ መለሰ፡፡

ስፖርት ቱሪዝም ማለት የስፖርት ውድድሮችን /ዝግጅቶችን/ ለመመልከት ወይም በውድድሩ ላይ ለመሳተፍ ወደ አንድ የዝግጅት መዳረሻ መሄድ ነው፡፡ ይኸም በተለያዩ የስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ለመሳተፍ ወይም ለመመልከት መሔድን ጨምሮ፣ የስፖርት ሙዚየሞችን፣ ስታዲየሞችና ሌሎች ልማቶችን መጎብኘትን ሁሉ ያጠቃልላል። በአላይድ የገበያ ጥናት /Allied Market Research/ ሪፖርት መሰረት የዓለም ስፖርት ቱሪዝም ኢንደስትሪ ከሶስት ዓመት በፊት በወጣ መረጃ 323 ነጥብ 42 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር፡፡ በ2030 ደግሞ 1 ነጥብ 8 ትሪሊዮን ዶላር ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል፡፡